# በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የተገኙ የግድግዳ ጽሑፎች ይዘት ትንተና

በ

አስቴር ወልዴ

የአርት ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለትምህርት
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የካቲት 1999 ዓ.ም.

# በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የተገኙ የግድግዳ ጽሑፎች ይዘት ትንተና

በ

አስቴር ወልዴ

የአርት ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለትምህርት
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የጥናቱ አማካሪ፡-
ወንድወሰን አዳነ

የካቲት 1999 ዓ.ም.

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# መታሰቢያ

ዘውትር ከህሊናዬ ለማይፋቀው፣ የትምህርት ውጥኔን እዳር አደርስ ዘንድ ያልተቆጠበ ድጋፉና ማበረታታቱ ሳይለየኝ ቆይቶ መኖርን ሳይወድ እንዲያቋርጥ ለተገደደው፤ የደስታዬ ተቋዳሽ ለመሆን ትልቅ ምኞት ለነበረውና ይህን ሳያይ ያለዕድሜው ለተቀጨው ታናሽ ወንድሜ ኤፍሬም ወልዴ መታሰቢያ ይሁንልኝ።

# ምስጋና

ከሁሉም በፊት÷ አስጀምሮ ላስጨረሰኝ አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው፡፡ በመቀጠልም እጅግ በጣም ለማከብረው አማካሪዬ አቶ ወንድወሰን አዳነ ካለበት ትልቅ የስራ ሀላፊነትና ድርሻ አኳያ ወርቃማ ጊዜውን ሰውቶ የሚቻለውን ሁሉ ደክመኝ ሰለቸኝ ሳይል ያልተቆጠበ ድጋፉንና ገንቢ አስተያየቱን ሳይነፍገኝ በማረምና በማስተካከል ስራዬን ከዳር እንዳደርስ በእጅጉ ረድቶኛል፡፡ በዚህም ሂደት ውስጥ ከጥንካሬው ብርታትን ከጥንቃቄው የስራ ክቡርነትን እንድማርና እንድጠቀምበት ስላደረገ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

ፍሬዬን እንድታይና እንድትደሰት የምመኝላት እናቴ ለዚህ እንድበቃ ሁሉን ነገሬን በመሸፈን ላልተለየኝ የእናትነት ፍቅሯ አመስግናታለሁ፤ እንዲሁም ድጋፋቸውና አይዞሽ ባይነታቸው ላልተለየኝ እህቶቼና ልጆቼ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ቃላት ሊገልፁት ከሚችሉት በላይ ማበረታታቷና እርዳታዋ ያልተለየኝ እህቴ አዳነች ካሳ ከመንፈስ ጥንካሬዋ ጥንካሬን እንድማር ያደረገች በመሆኗ የውለታዋን ዕዳ የምሸክምበት ጫንቃም የለኝና እሱ ይርዳልኝ እላለሁ፡፡

ጥናቴን ስጀምር የመረጃ ምንጭ በማፈላለግና በመስጠት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ወንድማዊ ድጋፉን ላደረገልኝ ወንድሜ ብርሀኑ ገ/ማሪያምና አይዞሽ ባይነቷ ላልተለየኝ ባለቤቱ አዲሴ ታከለ ምስጋናዬን ባቀርብ እንኳን በቂ አይመስለኝም፡፡

በተጨማሪ ሙሉፀሀይ ካሴና ገዳምነሽ ስንሻው የመንፈስ ምግብ የሆነው ምክርና ማበረታታቻቸው ሳይለየኝ ለኔ ምኞት መሳካት ያልጣሩት የለምና እግዚአብሔር ይስጥልኝ እላለሁ፡፡

# ማውጫ


**አርዕስት** **ገፅ**

ምስጋና

መግቢያ ------------------------------------------------------------ 1

## ምዕራፍ አንድ

### የጥናቱ መቅድሞችና ክለሳ ድርሳን

1.1 የጥናቱ መቅድሞች

1.1.1 የጥናቱ ዳራ------------------------------------------------ 2

1.1.2 የጥናቱ ዓላማ---------------------------------------------- 2

1.1.3 የጥናቱ ዘዴ------------------------------------------------ 2

1.1.4 የጥናቱ ወሰን---------------------------------------------- 3

1.1.5 የጥናቱ ፋይዳ---------------------------------------------- 3

1.2. ክለሳ ድርሳን

1.2.1 የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት-------------------------- 4

1.2.2 ንድፈሀሳባዊ ዳራ--------------------------------------------- 5

1.2.2.1 የግድግዳ ጽሁፍ አጀማመር --------------------- 5

1.2.2.2 የግድግዳ ላይ ጽሁፎች ምንነት ------------------ 6

1.2.2.3 የግድግዳ ጽሁፍ አይነት፣የአፃፃፍ ቅርፅና የአፃፃፍ ዘዴዎች ------------------------ 8

## ምዕራፍ ሁለት

### የግድግዳ ጽሑፎቹ ይዘት ትንተና

2.1 ፍቅር ነክ ጽሑፎች---------------------------------------------- 16

2.2 ትምህርት ነክ ጽሑፎች------------------------------------------ 19

2.3 ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ጽሑፎች------------------- 23

2.4 ወቅታዊና ፓለቲካ ነክ ጽሁፎች---------------------------- 31

## ምዕራፍ ሦስት

### የግድግዳ ጽሑፎቹ የአቀራረብ ዘዴ ትንተና

3.1. በምልልስ መልክ የቀረቡ ------------------------------------ 35

3.2. በመፈክር መልክ የቀረቡ ------------------------------------ 38

3.3. በማስታወቂያ መልክ የቀረቡ -------------------------------- 40

3.4. በግጥም መልክ የቀረቡ -------------------------------------- 42

3.5 በስዕል መልክ የቀረቡ ---------------------------------------- 45

- ማጠቃለያ ---------------------------------------------------- 48
- ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ---------------------------------- 50
- ዋቢ ጽሑፎች/የተጠቀሱ ምንጮች/ ------------------------ 53
- አባሪ፡- - የተሰበሰቡ የግድግዳ ጽሁፎች በፊደል ተራ
  - ፎቶ ግራፍ

# መግቢያ

የሰው ልጅ በህይወት መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በተለያዩ የመግባቢያ ዘዴዎች በመጠቀም በአዕምሮው የሚምሰለሰለውን ማንኛውንም ሀሳብ፣ አውጣው ጠይቅ እያለ የሚጐተጉተውንና የሚያስጨንቀውን ምላሽ ያጣለትን ጥያቄውን፣ ልውጣ ልቅር እያለ የሚሞግተውን በደሉን ከመሰሉ ጋራ ከሚጋራባቸው የኪነጥበብ ውጤቶች ዋነኛው ስነቃል ነው፡፡

በስነቃል ስዎች ያላቸውን እምነት፣ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አመለካከታቸውን፣ የህይወት ፍልስፍናቸውን ይገልፃሉ፡፡ በአጠቃላይ በስነቃል የማይገለፅ የሰው የሆነ ነገር ባለመኖሩም የሰው ልጅ ከመነሻው አንስቶ አሁን እስካለበት ጊዜ ድረስ በቋንቋው አማካይነት ያገዘፋቸውንና ያንቋሸሻቸውን፣የደገፋቸውንና የተቃወማቸውን፣ጥላቻና ውዴታውን የቸራቸውን ሀሳቦቹን፣ ታሪኩን የምንገነዘብበት ክፍል ቃላዊ ቅርሱ መሆኑ ከፍተኛ የማወቅ ጉጉት ያሳድራል፡፡ እኔም በዚህ ጥናቴ ከዚሁ ከስነቃል ዝርያ ውስጥ አንዱ በሆነው የግድግዳ ጽሁፍ ላይ ያተኮርኩት በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ስለዚህም ይህ ጥናት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በተፃፉ የግድግዳ ጽሁፎች አማካይነት ከላይ የተጠቀሱትን ሀቆች ለመመርመር ይሞክራል፡፡

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ ጥበብ እንዲናገር ወይም በጋራ ቋንቋ እንዲያናግር፣ እንዲያወራ ወይም ያሰቡትንና ያዩትን እንዲያስወራ፣ ስሜትን እንዲያጋራ ወይም ተቃውሞና ድጋፍን እንዲያቀብል፣ ድብቁን ገሀድ እንዲያወጣ እንዲፈክር ወይም እንዲያስፈክር፣ እንዲገጥም ወይም ሰንኝ እንዲያስቋጥር ተደርጐ የሚፃፍ፣ ወይም የሚሞነጫጨር ወይም የሚሳል ነው፡፡ ብመሆኑም የዚህን ነፃ መድረክ ባለቤቶች በዓይነ ህሊናችን በመሳል እንድንቀርባቸውና ትሩፋቶቻቸውን በንባብ እንድንቋደስ እጋብዛለሁ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# የጥናቱ መቅድሞችና ክለሣ ድርሳን

## 1.1. የጥናቱ መቅድሞች

### 1.1.1 የጥናቱ ዳራ

በዚህ ርዕስ ላይ ጥናት እንዳደርግ ካነሳሱኝ ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛው በዩኒቨርሲቲው ቆይታዬ ያገኘሁት "የፎክሎር መግቢያ" የተባለ ኮርስ ስነቃል የማህበረሰቡን ማንነት፣ ቁሳዊ፣ ባህላዊና መንፈሳዊ ሀብቱን ከደቂቅ እስከ ልሂቅ ለማወቅ የሚያስችል ኪነጥበብ መሆኑን መረዳቴ ነው:: ይኸው ግንዛቤ በይበልጥ እንድረዳውና እንድመረምረው ከፍተኛ ጉጉት አሳድሮብኛል:: ሁለተኛው ምክንያት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የተደረጉት ጥናቶች በቂ አለመሆናቸው ነው:: ይህም ችግር የፈጠረውን ክፍተት ለመድፈን ብሞክር የበኩሌን ትንሽ ድርሻ ለማበርከት ያስችለኛል በሚል እምነት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ጥናት ለማካሄድ ወሰንኩ::

### 1.1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ የሚገኙትን የግድግዳ ጽሁፎችን ይዛትና የአቀራረብ ዘዴዎችን መተንተን ነው:: የግድግዳ ጽሁፎቹ ይዘቶች የህብረተሰቡ አመለካከት ነፀብራቆች ናቸውና ምን ይላሉ የሚለውን ማየትና ያለውን የዘመን አሻራ ማሳየት ነው::

ከዚህ በተጨማሪም በአፃፃፍ ዘዴያቸው ውስጥ የሚታዩትን የየፀሀፊዎቹን አመለካከት፣ የጋራ ስሜቶች ፍላጎቶችና የየትኩረት አቅጣጫቸውን መርምሮ ጥቆማ ይሰጣል::

### 1.1.3 የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ጥናት በመጀመሪያ በምልከታ ዘዴ በአካል በቦታው ላይ በመገኘት የግድግዳ ጽሁፎቹን በጽሁፍ ማስታወሻ በማስቀረት፣ በፎቶና ቪዲዮ በመታገዝና በመቅረፅ ጽሁፎቹን መሰብሰብ ተችሏል:: በመቀጠልም ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ በርዕሱ ዙሪያ ከተዘጋጁ መፃህፍትና የጥናት ወረቀቶች፣ እንዲሁም ከኢንተርኔት መረጃዎችን በመውሰድ ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ ጥልቅ ምልከታዎች ተደርገዋል::



9

ከዚህ በመቀጠል ጽሁፎቹን በመደብ መደባቸውና በየፈርጃቸው በመከፋፈልና በመለየት ለናሙና የተመረጡ የግድግዳ ጽሁፎች ተደራጅተዋል:: የተደራጁትንም የግድግዳ ጽሁፎች ሀሳብ በመመርመር ትንታኔ ተደርጓል::

ትንታኔ የተሰጠባቸው የግድግዳ ጽሁፎችን ከይዘታቸው አኳያ በመመርመር ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም ከግድግዳ ጽሁፎቹ አቀራረብ ዘዴ አንፃር ነው:: ከአቀራረብ ዘዴዎቻቸው ውስጥ ፀሀፊዎቹ ካተኮሩባቸው ሀሳቦችና ከምልልሳቸውም የማፈነጥቁትን ሀሳብ በመመርመር ትንተና ተሰጥቷል::

ባጠቃላይ ጥናቱ በምልከታ ዘዴ(observation method) ና በትንተና ዘዴ(Analysis) ላይ ተመስርቶ የተሠራ ነው::

### 1.1.4. የጥናቱ ወሰን

እንደሚታወቀው ሁሉ የግድግዳ ጽሁፎቹ በተለያዩ ቦታዎች ማለትም በየትምህርት ቤቶች፣ በተለያዩ የመሰብሰቢያ አዳራሾች፣ ለእይታ ቅርብ በሆኑ አደባባዩች፣ በታላላቅ ጎዳናዎች፣ ህዝብ በብዛት በሚሰበሰብባቸው ማንኛውም ቦታዎች . . . ወዘተ ተፅፈው አሻራቸው በተለያየ ቦታ የሚገኝ ቢሆንም ይህ ጥናት ግን ከኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ በተፃፉ የግድግዳ ጽሁፎች ይዘት ላይ ብቻ የተገደበ ነው:: በተጨማሪም በኮሌጁ ውስጥ የተፃፉትን የግድግዳ ጽሁፎች በሙሉ በዝርዝር በአባሪነት ያቀረብኩ ሲሆን በናሙናነት ከቀረቡት ሰባ አራት የግድግዳ ጽሁፎች ከዓይነት አኳያ በ4 /አራት/ ፈርጅ በመመደብ በአርባ ሰባት የግድግዳ ጽሁፎች አማካይነት የይዘት ትንተና ተደርጓል:: በቀሪዎቹ ሀያ ሰባቱ የግድግዳ ጽሁፎች ደግሞ የአቀራረብ ዘዴ ትንተና ላይ ተወስኖ የተሠራ ነው::

### 1.1.5. የጥናቱ ፋይዳ

የዚህ ጥናት ፋይዳ የግድግዳ ጽሁፎቹን ሰብስቦ በመልክ በመልካቸው፣ በአቀራረብ ዘዴያቸውና ሁኔታቸው በጽሁፍ በመመዝገብ፣ በፎቶ ግራፍ በማንሳትና በማስቀመጥ ይዘታቸውን ለመረዳትና ለመመርመር ማስቻሉ ነው:: ሌላው የህብረተሰቡን ቁሳዊና ባህላዊ ሀብቶች ከመጠበቅና የየዘመናቱን የትውልድ የህይወት አሻራዎች በቅርስነት አቆይቶ ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችል መረጃ ማስገኘቱ ነው:: ከግድግዳ ጽሁፎቹ ይዘትም የህብረተሰቡን አመለካከት ለመረዳት የበኩሉን ትንሽ ድርሻ ከማበርከቱም ሌላ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ለሚያደርጉ ሰዎች እንደመነሻ ሊያገለግል ይችላል የሚል እምነት አለኝ::

## 1.2 ክለሳ ድርሳን

### 1.2.1 የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህን ጥናት ስጀምር ለመነሻ እንዲሆነኝ በግድግዳ ጽሁፎች ላይ የተሠሩ ቀደምት ጥናቶች መኖራቸውን ለማየት ከፍተኛ ጥረት አድርጌአለሁ:: ሆኖም ግን ርዕሱ በዋናነት ተወስዶ ጥናት የተደረገባቸው ስራዎች በብዛት ለማግኘት አልቻልኩም:: በዚህ ርዕስ ዙሪያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ወ/ት ሙሉእመቤት ዘነበ «ግራፊቲ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ» በሚል በ10ኛው የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዓመታዊ ሴሚናር ላይ በሚያዚያ 1990 ዓ.ም. ያቀረቡት ጥናት እንደነበር ብጠቆምም የሴሚናር ወረቀቱን ለማግኘት የግቢውን አብያተ መፃህፍት በሙሉ ፈትሼ ላገኘው አልቻልኩም:: የጥናቱን ባለቤትም በአካል ለማግኘት ያደረግኩት ጥረት በአጥኚዋ አለመኖር ሊሳካ አልቻለም:: በተጨማሪም በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህር የነበሩት ወ/ሮ ሰሚራም «ግራፊቲ ከስነ-ልቦና አኳያ» በሚል የሠሩትና ለሴሚናር የቀረበ ጥናት የነበራቸው መሆኑን ተጠቁሜ ነበር:: ነገር ግን ከብዙ ጥረት በኋላ የጥናቱን ባለቤት አሁን ከሚገኙበት የስራ ቦታ ድረስ በመሄድ በአካል በማግኘትና በማነጋገር የተሠራው የጥናት ወረቀት ጥቂት ዓመታትን ያስቆጠረ በመሆኑ ባለቤቷም ራሳቸው ሊያገኙልኝ ባለመቻላቸው ጥረቱ ከንቱ ሆኗል::

ሆኖም ግን በ1991 ዓ.ም. ማይገነት አፈወርቅ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ «በግራፊቲ ስለሴቶች ያለ አተያይ» በሚል ርዕስ በዋናው ግቢ፣ ቴክኖሎጂ ፋኩልቲና በሳይንስ ፋኩልቲ የሚገኙ የግዳግዳ ጽሁፎችን በመሰብሰብ በሴቶች ላይ ያለውን አተያይ ያጠናችበትን ጽሁፍ አግኝቼ አንብቤያለሁ:: በጥናቷ ዋና አካል ሴቶችን የሚያንቋሽሹ የግድግዳ ጽሁፎች ገፅታ፣ሴቶችን የሚክቡና እኩልነታቸውን የሚደግፉ የግድግዳ ጽሁፎችን ገፅታ ስትተነትን ለሴቶች መብት የሚቆረቆሩ፣ የሴቶች ተሳትፎን የሚያበረታቱ የግድግዳ ጽሁፎችን በምሳሌ አስደግፋ አሳይታለች:: በዚሁ የጥናት ጽሁፏ ዋና አካል ውስጥ የግድግዳ ጽሁፉ የቀረበበትን መንገድ በመዘርዘር ገልፃለች::

የማይገነት አፈወርቅ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰልባቸው መንገዶች የግድግዳ ጽሁፎቹን ከዚሁ ከመዲናችን ከአዲስ አበባ ሳንወጣ በአንድ ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታ ውስጥ ማካሄዳችን ነው:: ሁለተኛው ተመሳስሎ የሁለታችንም የግድግዳ ጽሀፎች ስብስብ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መሰብሰቡ ነው:: ልዩነቶቻችን ደግሞ የእኔ ጥናት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ላይ ብቻ መወሰኑ ነው:: የእሷ ጥናት ግን ሁለት ፋኩልቲዎችን በተጨማሪ የያዘ መሆኑ ነው:: ከዚህም ሌላ የማይገነት ጥናት የሚያተኩርበት ዋና ጉዳይ የግድዳግ ጽሁፍ በሴቶች ላይ ያለውን አተያይ መተንተን ሲሆን የእኔ ጥናት በአጠቃላዩ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ ተፅፈው በተገኙት የግድግዳ ጽሁፎች ይዘት ትንተና ላይ የሚያተኩር ነው::

በአጠቃላይ ይህን ጥናት ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው ከዚህ በፊት ትኩረት ያልተሰጠውና በዘርፉ በሀገር አቀፍ ደረጃም ጥናቱ ገና ብዙ ያልተሠራበት መሆኑና ለግድግዳ ጽሁፍና ሽኖኞች(latrinalia) ፋይዳ ትኩረት ስጥቶ የሚተነትን መሆኑ ነው፡፡ በመጨረሻም ለመግለፅ የምወደው በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በቀጥታ የተደረጉ ጥናቶች የሌሉ በመሆናቸው ከዚህ የተሻለና ሰፋ ያለ ክለሳ ድርሳን ማዘጋጀት አለመቻሌን ነው፡፡

### 1.2.2. ንድፈሀሳባዊ ዳራ

#### 1.2.2.1. የግድግዳ ጽሑፍ አጀማመር

የግድግዳ ጽሁፍ አጀማመር በድንጋይ ዘመን የነበረውን ዘገምተኛ ለውጥ ያልጨረሰው ጥንታዊው ሰው በዋሻ ውስጥ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን ሬዝነር ያስረዳል፡፡ እንደ ሬዝነር /1971፣23/ ገለፃ በዛ ዘመን የነበረው ጥንታዊው ሰው ምግቡን በሚፈልግበት ሂደት ፍራፍሬ ለመፈንከት የሰነዘረው ትልቅ አለት ዒላማውን ስቶ ፍሬው ያረፈበትን አለት ሲመታ የፈጠራቸው በርካታ የአለት ላይ ጭረቶች ቀልቡን የሳቡ ክስተቶች ነበሩ፡፡ ይህም የጥንታዊውን ሰው የመሳል ስሜት ያጫረ ነበር፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮም የሰው ልጅ ደስ ያለውን ቅርፅ በመሳ በዋሻው ግድግዳዎች ላይ መሞነጫጨር ጀመረ፡፡ ይህም ሰው ከጽሁፍ በፊት በስዕል መልክ ሀሳቡን መግለፅ እንደጀመረ ያመለክታል፡፡ ከቀላል የግድግዳ ላይ መጫጫር እስከ ማራኪ ስዕሎችና ጽሁፎች ያሉት የቅድመ - ታሪክ የግድግዳ ላይ ጽሁፎች በመላው አውሮፓ በሚገኙ ዋሻዎች ውስጥ መገኘት ከላይ ለተገለፀው እውነታ ምስክር ነው፡፡

እንደ ሬዝነር አባባል የመጀመሪያዎቹ የቅድመ-ታሪክ የግድግዳ ላይ ፀሀፊዎች «አውሪጋናንሺያንስ» በመባል የሚታወቁ ህዝቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ህዝቦች በአካባቢያቸው በሚገኙ አጥንቶችና አለቶች/ድንጋዮች/ በመጠቀም ፖይሬኔንስ የተባለችውን የደቡብ ፈረንሳይ ከተማ ያስጌጡ ነበር፡፡ ለጽሁፍ የሚጠቀሙት ጣታቸውን ቀይ ቀለም በመቀባት፣በነጭ ጠመኔ፣ በከሰል ጥላሸትና ደም በመቀባት ሆኖ የጣት አሻራቸውን በየዋሻው ግድግዳ ላይ ያኖሩ ነበር፡፡ እነዚህ የእጅ አሻራዎች የሰው ልጅ ለሚቀጥለው ትውልድ ምልክቱን ትቶ በማለፍ ህያው ለመሆን ለሚያደርገው ጥረት ቋሚ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ምልክትን በግድግዳ ላይ የመተው ባህል እስከ አሁንም ድረስ ይተገበራል፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምሳሌ ታዋቂ የፊልም ተዋናዮች በሆሊውድ ውስጥ በሚገኘው የቻይና ቲያትር ስሚንቶ ላይ የጣት አሻራቸውን በህብረ ቀለማት ማኖራቸው ነው፡፡ /ሬዝነር፣24/

ጥንታዊው ሰው የግድግዳ ስዕሎቹንና ጽሁፎቹን ሲፅፍ ለቀልድ፣ ለጨዋታና ጊዜ ለማሳለፊያ ሳይሆን የራሱ የሆነ ዓላማ ነበረው፡፡ ይህም የአደን ክህሎቱን ወይም ችሎታውን ለማዳበር እንደነበር አያሌ ምሁራን ትንታኔ ስጥተዋል፡፡ ሰው በመጀመሪያ እንስሳትን እንዴት እንደሚያድንና እንደሚይዝ ልምምድ ያደርጋል፡፡ ከዚያም ሀሳቡንና

ምኞቱን በተግባር ይተረጉም ነበር:: ስዕሎቹም አብዛኛውን ጊዜ አጋዘን፣አውራሪስ፣ ፈረስና የመሳሰሉ እንስሳትን የሚወክሉ ነበሩ:: በዚህም የሰው ልጅ ህያው እንስሶች ከዋሻው እንዲገኙ የነበረውን ምኞት ገልጿል:: ከዚህም ባሻገር የመሳል ውስጣዊ ስሜቱን ሲያረካ የየዕለት ገጠመኙን ለመጪው ትውልድ አስተላልፎበታል:: ቀዳሚዎቹ የግድግዳ ጽሁፎቹም ለተፈጥሮና ለህይወት መልካም እይታ ነበራቸው፡

በአዝጋሚ ለውጥ ሂደት የሰው ልጅ በኒላውያን ዘመን የግድግዳ ጽሁፎቹ ከተፈጥሮና ነባራዊ ይዘቶች ይልቅ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ጀመሩ:: በዚህ ጊዜ ነበር ጥንታዊው ሰው በአግባቡና በወጉ ለመፃፍ የመጀመሪያውን ርምጃ ያሳየውና ወደ ረቂቅ ደረጃ የተሸጋገረው:: በጊዜ ሂደትም ሰው የሞትን አይቀሬነት በመረዳት የአስተሳሰብ ለውጥ አድርጓል:: በጊዜ፣ በአደጋ፣ በተፈጥሮ መቅሰፍቶችና በበሽታ ገደብ የተደረገበት ህይወቱን ለማሻሻል ከፍተኛ የፈጠራ ስራ አካሂዷል:: ጥሩ የሰነምግባር ደንብ ለማውጣትም ሀይማኖት ፈጥሯል:: ከሞት በኋላ ህይወት እንዳለ ተስፋ በማድረግ አማልክትን ፈጥሯል:: ለአማልክቱ ያለውን አክብሮት ለመግለፅ ሀውልት አቁሟል:: የአምልኮቱን ጥልቀትና ስፋት ለመግለፅ በድንጋይ ሀውልቶቹ ላይ ምልክቱን ቀርጿል፤ ፅፏል:: በዚህ ሂደት ውስጥ የግድግዳ ጽሁፎች ተፈጥረዋል፤ ወይም ተጀምረዋል:: ለዚህም ነው ሪቻርድ ፍሪማን የተባለ እንግሊዛዊ ፀሀፊ «የግድግዳ ላይ ጽሁፎች» በሚል መፅሀፉ በጥንታዊው የግድግዳ ላይ ጽሁፎችና በለንደን ከተማ የዘመናዊ ስዕሎችና የግድግዳ ጽሁፎች መሀከል ያለውን ተዛማጅነት ሲገልፅ "መቃብሮች፣ መፀዳጃ ቤቶችና እስር ቤቶች የሚጋሩት መመሳሰል አላቸው:: ይኸውም የሰው ልጅ በእነርሱ ላይ ውስጣዊና የተደበቀ ስሜቱን ይገልፅባቸዋል::"[1] ብሏል በማለት ምንጭ ጠቅሶ ሬዝነር ዝኒ ከማሁ /28/ የስዕል ስራ የግድግዳ ጽሁፍ ጅማሬ መሠረት መሆኑን ያስረዳው::

#### 1.2.2.2. የግድግዳ ላይ ጽሁፎች ምንነት

የግድግዳ ላይ ጽሁፍ ስያሜ እንደ PAMELA, DENNANT, (URBAN EXPRESSION, UKREALL@ hot mail.com,1997) ገለፃ ወሽለርን ጠቅሶ እንደሚከተለው ዘርዝሯል::

> «ግራፊቲ» የሚለው ስያሜ የመጣው «ግራፊን» ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም «መፃፍ» ማለት ነው:: በሌላ በኩልም «ግራፊቲ» የሚለው «ግራፊቶ» ከሚለው የጣልያንኛ ቃል ብዜት የመጣ ነው:: ትርጓሜውም «መጫር» ማለት ነው:: ታሪኩም ከቅድመ ታሪክ በፊት ይኖር የነበረው የጥንታዊው ሰው በዋሻ ግድግዳዎች ውስጥ ከሚስላቸው ስዕሎች ይጀምራል:: ጥበቡ የሰው ልጅ እርስ በርስ ለመገናኘት ያለውን ፍላጎት ያሳያል:: «የግድግዳ ላይ ጽሁፍ» የሰው ልጅ እርስ በርስ ለመገናኘት ያለውን መሻት ይገልፃል::[2]

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ስለ ስያሜው Ilse Scheepers (Graffiti and urban space. htm.2004) እንደሚከተለው ዘርዝሯል፡፡ ፀሀፊው የአሜሪካን ሔሪቴጅ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላትን ዋቢ አድርጎ ስለቃሉ አመጣጥ የሚከተለውን አስፍሯል፡፡

> ስያሜው የተገኘው ከጣልያንኛው ቃል «ግራፊቶ» ነው፤ ትርጓሜውም «ቡጭር» ወይም «መጫር» ነው፡፡ በተጨማሪ እንደ አሜሪካ ሔሪቴጅ መዝገበ ቃል ምናልባትም ሠርካዊ የላቲን ቃል «ግራፋየር» ከሚለው ሲሆን ትርጓሜውም «ስልታዊ ወይም ዘዴያዊ አፃፃፍ» እና «ግራፊየን» ከሚለው የግሪክ ቃል ሆኖ ትርጉሙም «መፃፍ» ማለት ነው፡፡[3]

ስለዚህም ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ተቀራራቢ ትርጓሜዎች እንደምንረዳው የግድግዳ ጽሁፍ በማንኛውም ቦታ ለሚፃፉ፣ ለሚጫሩና ለረጅም ጊዜያት ለሚኖሩ ፅሁፎች የተሰጠ ስያሜ መሆኑን ነው፡፡

Ilse Scheepers, (file A: Graffiti and urban Space: htm. 7/20/2006) የተለያዩ ፀሀፊዎችን ጠቅሶ ለምሳሌ ኤሪካሽን ፣ ፓሜላ ዴናንት፣ ኪሊያን ቶቢንና ኬቪን፣ ናንሲ ማክዶናልድና ቲም ክሪስዌን ሁሉም የግድግዳ ጽሁፍን ከጥንታዊው ሰው የዋሻ ግድግዳዎች ስዕልና ጽሁፍ ጀምሮ የሰው የሀሳብ መለዋወጫና መገናኛ ዘዴ፣ በባዶ ቦታዎች ላይ ወይም በግድግዳዎች ላይ የሚፃፉ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶች መሆናቸውን እንደገለፁ አስፍሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቀለም ያሸበረቁ የግድግዳ ጽሁፎች፤ ያለፈቃድ፣ ያለአጀንዳ የተለየዩ ሀሳቦች የሚገለፁባቸው፣ አንዳንዴ ፀያፍና ስድ ለሆኑ በተለያየ ዘዴ ለሚፃፉ ጽሁፎች የተሰጠ ስያሜና ድርጊቱ የሚታወቅበት መጠሪያ እንደሆነ ፀሀፊዎቹ በየራሳቸው ገለፃ እንደሚጠቁሙ ይገልፃል፡፡

ስለዚህም የግድግዳ ጽሁፍ በየትኛውም ቦታ፣ በማንኛውም ጊዜ በየግድግዳዎች፣ በየመሰብሰቢያ አዳራሾች፣ በቤተመፃህፍት ጠረጴዛዎችና መደገፊያዎች፣ በምድር ውስጥ ለውስጥ በሚጓዙ መኪናዎች፣ የጉዳና ምሰሶዎች፣ በየመፀዳጃ ቤቶች ፣ የአውቶቡስና የባቡር መቀመጫዎች፣ በእግረኛ መንገዶች፣ በህዝብ ስልክ መደወያዎች፣ በጭነት መኪና ጉኖች፣ በማስታወቂያ ስሌዳዎች፣ በማስታወሻ ደብተሮች፣ በመማሪያ ክፍሎች፣ በመፃህፍት ላይና ፖስተሮች ላይ . . . ለሚፃፉ ውስጣዊ ስሜቶችና ሀሳቦች ሌላ ሰው ሳያይ ለመግለፅ ለሚያስችሉ ጽሁፎችና ስዕሎች የሚሰጥ ስም ነው፡፡

የግድግዳ ጽሁፍ የመፃፍ ዓላማዎችና ምክንያቶች ናቸው፤ ብሎ /ፓሜላ ዴናንት፣5/ ስሚዝ፣ ቻልፋንትና ፕሪጉፍን ጠቅሶ «ዋናው የግድግዳ ላይ ፀሀፊዎች ዓላማ ከሌሎች ፀሀፊዎች ጋር ለመገናኘት ነው»[4]ሲል ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም ዕውቅናን ለማትረፍ ከሚያስጨንቃቸው ሀሳብና ስሜት እፎይታ ለማግኘት ካላቸው ጉጉትና መረጃን ከሌሎች ለመካፈል በመፈለጋቸው ነው፡፡ ይህንኑ አባባልም /ፊዝ 2/ የተባለ ፀሀፊ በሚከተለው

መልኩ ያጠናክረዋል:: «የእኛ ትልቁ እርካታ ከሌሎች በተመሳሳይ የግድግዳ ላይ ፅሁፍ ስራ ከተሰማሩ አጋሮቻቸቸውን እውቅናን ማግኘት ነበር:: ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ተቀባይነትን ማግኘት ብዙም የሚያጣድፈን ጉዳይ አልነበረም::»[5] /ፌዝ 2፣ገፅ 55/:: ከዚህ ገለፃ እንደምንረዳው እያንዳንዱ የግድግዳ ፀሀፊ ከአራቱ ምክንያቶች በአንዱ ወይም በተወሰኑት ምክንያቶች መነሻነት ለመፃፍ እንደሚነሳሳ እናስተውላለን:: በተለይም ዝናን ማግኘት እንደሚያረካና ከምክንያቶቹ ሁሉ ሚዛን የሚደፉና እንደ መገናኛ ኮድ የሚያገለግል መሆኑን እንረዳለን::

ከዚህ ከመፃፍ ምክንያት ጋር በተያያዘም የተለያዩ አጥኚዎች የሰጧቸውን አስተያየቶች ፓሜላ ዴናንት ምንጭ እየጠቀሰ ሲዘረዝር የግድግዳ ጽሁፍ የሚፃፍበት ምክንያት የተለያየ ነው ይላል:: ለምሳሌ በዕድሜ ለገፉ ፀሀፊዎች የግድግዳ ላይ ጽሁፍ «የየዕለት ተዕለት የሀሳባቸው አካልና የኑሮ ፍልስፍናቸው ነው::»[6] /ዋልሽ፣12/፤ ሌላው የግድግዳ ጽሁፍን ያጠናው ታዋቂ የማህበረሰብ አጥኚ /ሶሾሎጂስት/ ዲሽን ዲ ብሪወሪ የደረሰበትን ድምዳሜ እንዲህ ይገልፃል «የሂኘሆፕ የግድግዳ ፀሀፊዎች በጥበቡ እንዲሰማሩ የሚገፋፋአቸው አራት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ:: እነሱም ዝና፣ የስዕል ወይም የጽሁፍ ፍቅር፣ ስልጣንና አመፅ ናቸው::»[7] /188/ እንዲሁም የግድግዳ ጽሁፍን ያጠኑ የሰነ አዕምሮ ተማራማሪዎች /ሳይኮሎጂስቶች/ ለጥበቡ መፈጠር የሰጡት መላምት «ይህ ጥበብ የተፈጠረው ምናልባት የሰው ልጅ ለመታወቅ ካለው ፍላጐትና ከጫና ነፃ ለመውጣት ከሚያደርገው ትግል ነው::»[8] /ሌጀንደሪ፣730/ የሚሉ ይገኙ ባቸዋል በማለት ያስገነዝባል::

ስለዚህም ከላይ ከተገለፁት ገለፃዎች እንደምንረዳው የግድግዳ ጽሁፍ ጥበብ ነው:: የመነጨውም የሰው ልጅ ሀሳቡን በነፃነት ለመግለፅ ካለው ተፈጥሮአዊ ጥማትና ጉጉት ነው፤ እንዲሁም ጥበቡ የራስን ማንነት መግለጫ፣ ከሌሎች ጋር ሀሳብ የመለዋወጫ ዘዴ ነው:: ሰዎች የታፈነ ስሜታቸውን አውጥተው ጨኸታቸውን የሚገልጡበትና የሚያሳዩበት ምቹ መድረክ ነው:: የግድግዳ ላይ ጽሁፍ የሰው ልጅ በምናቡ የፈጠረው ሌላ የመግባቢያ ዘዴ ነው:: ጥበቡ የተለያዩ አስተሳሰቦች ለእይታ የሚቀርቡበት በመሆኑ የአንድነት መግለጫ ስለሆነ በየዘመኑ የሚኖሩትን ባህሎች ለመግለፅ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ያለው ነው:: በህዝቦች መካከል የዓላማ መመሳሰልንና አንድነትን ያጐለብታል::

### 1.2.2.3 የግድግዳ ጽሁፍ ዓይነት፣ የአፃፃፍ ቅርፅና የአፃፃፍ ዘዴዎች

#### ሀ. የግድግዳ ጽሁፍ ዓይነቶች

የግድግዳ ጽሁፍ ዓይነቶች ወይም ክፍሎች ሁለት እንደሆኑ http:/www.graffiti.org/faq/graffiti-is-part-of-us.html የተባለ ድረገፅ ሱዛን ፊሊኘስ ያቀረበችውን መግለጫ እንዲህ ይገልፀዋል::

የግድግዳ ጽሁፍ ዓይነቶች ወይም ክፍሎች ሁለት ናቸው:: እነሱም ህዝባዊ ወይም ታዋዊ የግድግዳ ጽሁፍ (Popular Graffiti)ና ማህበረሰብ ተኮር ወይም የተወሰነ አካባቢ የግድግዳ ጽሁፎች(Community based graffiti) ናቸው:: እነዚህ ጽሁፎች ወይም ስዕሎች በይዘታቸው፣ በፀሀፊዎቻቸውና በተመልካቾቻቸው ይለያያሉ:: ልዩነቶቻቸው እንደተጠበቁ ሆነው የግድግዳ ጽሁፎቹ ዓይነቶች በጋራ የሚጋሩት አንድ ነገር አለ:: እሱም የህዝብ ቦታ ነው::[9]

ከዚህ ገለፃ እንደምንረዳው ሁለት አበይት የግድግዳ ጽሁፍ ዓይነቶች መኖራቸውንና በየራሳቸው ባህሪያትና ይዘት ሁኔታ የተለያዩ መሆናቸውን ነው:: ልዩነቶቻቸው እንደተጠበቁም የጋራ ባህሪያቸው የህዝብ ቦታን መያዛቸው ነው:: በውስጣቸው የሚያቅፏቸው የጽሁፍ መልኮች ሲዘረዘሩም የሚከተሉትን ይመስላሉ::

የመጀመሪያ እስከ አሁንም ያለው /የማይለወጠው/ «የህዝብ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ» አለ:: ከዚህም ውስጥ ለምሳሌ የወሲብ የሰውነት ክፍሎች፣ ቀልዶች፣ ተረቦች፣ የሚነበቡ ስነቃላዊ የግድግዳ ጽሁፍ አካሎች፣ የደንዲስ ሽኖዎች፣ ወሲባዊ ስዕሎች፣ እከሌ ለሆነ ጊዜ ብንገናኝ ዓይነት ጽሁፎች፣ «ብሉኝ፣ ተበዳ፣ እወድሀለሁ/እወድሻለሁ፣ እነ እከሌ እዚህ ነበሩ . .» የሚሉ ጽሁፎች ይገኙበታል:: እንደዚህ ያሉ የግድግዳ ላይ ጽሁፎች የሚፃፉት አብዛኛውን ጊዜ በብሔራዊ ቋንቋ ነው:: ይህም የሚሆንበት ምክንያት ሌሎች ጽሁፉ እንዲገባቸውና ከፈለጉ በቀልዱ ውስጥ ራሳቸው እንዲሳተፉና ምላሽም እንዲሰጡ ለማድረግ ነው::[10]

/ፊሊኘስ በፓሜላ ፣ 1999፣ 47/

እንደዚህ ያሉት የግድግዳ ጽሁፎች ማንኛውም ሰው በየቀኑ ወይም ዕለት በዕለት ሊያገኛቸው ይችላል:: ጽሁፎቹ በመፀዳጃ ቤት ግድግዳ፣ በማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ በእግረኛ መንገዶችና በዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ ሊፃፉ ይችላሉ:: ፊሊኘስ /እ.ኤ.አ.በ1999፣በፖሜላ/ እንደገለፀቸው:-

ሁለተኛው የግድግዳ ጽሁፍ ዓይነት ደግሞ ማህበረሰብ ተኮር /የተወሰነ አካባቢ የግድግዳ ጽሁፍ (Community based Graffiti)ነው:: ይህ የጽሁፍ ዓይነት አብዛኛውን ዜጋ ሊያናድድ

> የሚችል ዓይነት ነው፤ ምክንያቱም ጽሁፎቹ ጠካንራና ብልግና አዘል ቃላትን የያዙ ናቸውና:: ጽሁፎች የሚፃፉት በትላልቅ ፊደላት ቀለም በሚተፋ የፍሊት ቆርቆሮዎች ነው:: አንዳንድ ጊዜ ወሰብስብና ለመረዳት አዳጋች ናቸው:: በዚህ የግድግዳ ጽሁፍ ስር የሚመደብ በርካታ ንዑሳን ክፍሎች አሉ:: ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ «ሂኘሆኘ የማህበረበብ ተኮር የግድግዳ ጽሁፍ»ና «ጋንግ /የቡድን/ ማህበረሰብ ተኮር የግድግዳ ጽሁፍ» ናቸው:: ከነዚሁ የግዳግዳ ጽሁፎች ውስጥ በአብዛኛው የዓለም ክፍል ተዘወታሪው «ሂኘሆኘ ማህበረሰብ ተኮር የግድግዳ ጽሁፍ» ነው:: ይህም የቅርብ ጊዜው የሂኘሆኘ ሙዚቃ እንቅስቃሴ ውጤት ነው::«ሂኘሆኘ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ» የአጠቃላይ የሂኘሆኘ ንዑስ ባህል አንድ ክፍል ነው:: «ሂኘሆኘ» ከአራት ንዑሳን ባህሎች ከስዕል ጥበብ፣ ከራኘ ሙዚቃ፣ በጁዲንግና በብሬክ ዳንስ ጥምር ውህደት የተገኘ ነው:: የሂኘሆኘ ጠንካራ ባህል በአይን የሚታይ ሲሆን በዘፈን፣ በአለባበስና በአነጋገር ስልትም ይገለፃል:: «ሂኘሆኘ» የተባለው ፅንሰ ሀሳብ የድሀ ህብረተሰብ ክፍሎችና ወጣቶች የሀሳብ መግለጫ ስልት ነው::[11]

ከዚህ መግለጫ እንደምንረዳው ማህበረሰብ ተኮር የግድግዳ ጽሁፍ በአብዛኛው በፀያፍ ቃላት የሚገለፅ ዓይነት ነው:: ይህ ክፍል ብዙ ዘርፎች ቢኖሩትም ዋና ዋናዎቹ «ሂኘሆኘ» ና«የጋንግ» ወይም «ቡድን» የግድግዳ ጽሁፍ ዓይነት ናቸው:: ሂኘሆኘ በተለይም ስራአጥ የሆነው ደሀ ማህበረሰብ ተሳታፊ የሚሆንበት ነው:: እነዚህ ጽሁፎች ብዙውን ጊዜ በነባራዊው እውነታ ላይ ስለሚመሠረቱ ብዙም ቀልድና ቧልት የማይነበብባቸው ደረቅ ስለሆኑ ዜጐችን ሊያበሳጩ የሚችሉ ዓይነት ናቸው:: ይህንኑ ሀሳብ ፊሊኘስ /1999፣ 49-56፣በፖሜላ/ ስታጠናክረው እንደሚከተለው ገልፃለች::

> «ሂኘሆኘ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ» ይህ የግድግዳ ጽሁፍ ቀለም በሚተፉ የፊሊት ቆርቆሮዎች፣ በምድር ውስጥ ለውስጥ በሚሄዱ ባቡሮችና የባቡር ጣቢያ ግድግዳዎች፣ በማስታወቂያ ሰሌዳዎችና በህንፃዎች የጐን ግድግዳዎች ሊፃፍ ይችላል:: «ሂኘሆኘ» የግድግዳ ጽሁፍ አብዛኛውን ጊዜ ስሜት የሚያነሳሱ /የሚያጓጉ/ና ውስብስብ ወይም አስቸጋሪ ናቸው:: ይህ ንዑስ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ ህጋዊ ያልሆኑ አገላለፆች ያሉት ቢሆንም ጥበቡ አለም አቀፋዊ መግባቢያ እየሆነ የመጣና፤ የመገናኛ ብዙሀንንም ትኩረት ለማግኘት የበቃ ነው::[12]

ሂኽሆኝ የግድግዳ ጽሁፍ የሚፅፉ የህብረተሰብ ክፍሎች በአብዘኛው ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ናቸው:: ሆኖም በጥበቡ ወግ አጥባቂ የተባሉ የከፍተኛው መደብ አባለትም እየተሳቡ በመምጣታቸው ማህበረሰቡን ሁሉ ወደ አንድ ጐራ በማሰባሰብ ሊያቅፍ በመቻሉ የዘር፣የጐሳና ሌሎች ልዩነቶችን በመሻርና በማጥበብ የህዝቦችን አንድነት ሊፈጥር የሚችል ሆኗል::

ሌላው ንዑስ ክፍል «ጋንግ» የወንበዴዎች ቡድን ወይም የድርጅዎች ቡድን ማህበረሰብ ተኮር የግድግዳ ጽሁፍ ነው:: ይህ የጽሁፍ ክፍል አብዛኛውን ጊዜ የፖለቲካ ይዘት ያለው ነው:: የግል ፀብ ወይም ጥላቻን ለመግለፅ ጥቅም ላይ ይውላል:: የፖለቲካ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ የሚፃፈው በምልክት ሲሆን ምልክቱ አፍራሽ ይዘት አለው:: እንደዚህ ዓይነት ጽሁፎች በአብዛኛው የሚዘወተሩት የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ባሉበት ወቅት ነው፤ በመሆኑም ህብረተሰቡን ለድርጊት የማነቃቃት ችሎታ ወይም ሀይል አላቸው:: ድርጊቱ አፍራሽ ወይም ገንቢ ሊሆን ይችላል::

ከዚህ እንደምንረዳው እያንዳንዱ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ ዓይነት፣ የሚፃፍበትን ቦታ ወይም ሀገር፣ የተፃፈበትን ጊዜ ወይም ወቅት ባህል ገላጭ መሆኑን ነው::

### ለ. የግድግዳ ጽሁፍ የአፃፃፍ ቅርፅ (Forms of writing)

እንደ ዴናንት ፖሜላ የቀደመ ምንጭ ሰባት ዋና ዋና የግድግዳ ላይ ጽሁፍ ቅርፆች አሉ:: ቅርፆቹ ባላቸው ውስብስብነት አቀማመጥና ስፋት ይለያያሉ:: እነዚህ ቅርፆች የሚከተሉት ናቸው::

1. <u>ምልክታዊ ቅርፅ /አሻራ/ "Tags":-</u> የመጀመሪያው ቅርፅ ሲሆን «ታግ» ማለት የፀሀፊው ቅፅል ስም፣ የብዕር ስም ወይም ፊርማ ነው:: ይህ ቀላል የሚባለው የግድግዳ ላይ ጽሁፍ ቅርፅ ነው:: የታግስ /አሻራ/ ጠቀሜታ የፀሀፊውን ስም ማሳወቅና ከተቻለም ዝናን ማስገኘት ነው:: ለማንኛውም ሰው «ታግስ» አንድ ዓይነት ሊመስሉ ቢችሉም ለንዑስ ባህሉ አባላት ግን ልክ እንደጣት አሻራ የተለያዩ ናቸው:: አለሁ ወይም እዚህ ነኝ የሚል መልዕክት ለማስተላለፍም ያገለግላል:: ይህ ዓይነት ስልት በተደጋጋሚ መጠቀምም በጥበቡ አፍቃሪ ፀሀፊዎች ዘንድ ዝቅተኛ ግምት ከማሰጠቱም በላይ «አሻንጉሊት» የሚል ቅፅል ስም ሊያስጥ እንደሚችል ዴናንት ይገልፃል::

2. <u>አሳጥሮ የመፃፍ ቅርፅ (Throw Ups):-</u> ይህ ያደገ ወይም የተሻሻለ «የታግስ» ዓይነት ቅርፅ ሲሆን የሚፃፈውም ቀለም በሚነፋ የፍሊት ቆርቆሮ በባቡሮች ውጫዊ አካል ላይ ወይም ግድግዳ ላይ . . . ወዘተ ነው፡፡ ፀሀፊዎች ትላልቅ ፊደላትን በመጠቀም በሁለት ወይም በሶስት ፊደላት ስማቸውን ይፅፋሉ:: በአብዛኛ

ው ሁለት ዓይነት ቀለማትን ይጠቀማሉ:: ትላልቅ ጽሁፍን በፍጥነት መፃፍን ይመርጣሉ::

3. <u>**የቁርጥራጭ ጥንቅር ቅርፅ (Pieces) :-**</u> እነዚህ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ ቅርፆች የሂን ሆኘ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ ዋነኛ የዕድገት መገለጫዎች ናቸው:: ጽሁፎቹ ከአሳጥሮ የመፃፍ ቅርፅ ጋር ሲነፃፀሩ በርካታ ፊደላትን ይይዛሉ:: የተብራሩ ናቸው:: ይህ ዓይነት የጽሁፍ ቅርፅ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈለሰፈው ሱፐር ኩል 223 በተባለ ግለሰብ እ.ኤ.አ በ1972 ነበር:: ግለሰቡ የሚነፋ አረፋ /ስኘሬይ አረፋ/ በመጠቀም በሰፊ ቦታ ላይ በፍጥነት የመፃፍን ዘዴ ፈልስፏል::

4. <u>**ከላይ ወደ ታች የሚፃፍ ቅርፅ (Top to bottom) :-**</u> እነዚህ የጽሁፍ ቅርፆች በምድር ውስጥ ለውስጥ በሚሄድ ባቡር ወይም መኪና ላይ ከላይ ወደታች የሚፃፍ የጽሁፉ ቅርፆችን ይይዛል::

5. <u>**ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚፃፍ ቅርፅ (End to End) :-**</u> እነዚህ የጽሁፍ ቅርፆች በምድር ውስጥ ለውስጥ በሚሄድ ባቡር ወይም መኪና ላይ በቁመት ከላይ እስከታችና በአግድመት ከጥግ እስከ ጥግ የሚፃፉ ናቸው::

6. <u>**በመኪናዎች ሙሉ አካል ላይ የሚፃፍ ቅርፅ (Whole cars):-**</u> እነዚህ የጽሁፍ ቅርፆች በምድር ውስጥ ለውስጥ በሚሄድ መኪና ላይ በቁመት ከላይ እስከታችና በአግድመት ከጥግ እስከ ጥግ የሚፃፉ ናቸው:: ሙሉ አካሉ የተፃፈበት መኪና ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው እ.ኤ.አ በ1973 ነው:: ፀሀፊው ፍሊንት 707 በመባል ይታወቃል:: ግለሰቡ መኪናውን ሙሉ ለሙሉ በጽሁፍ ለማስዋብ ሀያ ቀለም የሚረጩ የፍሊት ቆርቆሮዎችን በመጠቀም 20 ጫማ ስፋትና 12 ጫማ ቁመት ያላት መኪናውን ለመቀባት 8 ሰዓታት ፈጅቶበታል:: በ1970ዎቹ ይህ ስራ በጣም ተስፋፍቶ በተለያዩ ህብረቀለማት በመጠቀም ማህበራዊ ሂስን ጨምሮ የተለያዩ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ውሏል::

7. <u>**በባቡር ሙሉ አካል ላይ የሚፃፍ ቅርፅ (Whole trains):-**</u> እነዚህ የጽሁፍ ቅርፆች በምድር ውስጥ ለውስጥ በሚሄድ ባቡር ሙሉ አካል የሸፈነ የጽሁፍ ቅርፅ ነው:: የመጀመሪያው «የነፃነት ባቡር በመባል የሚታወቀው ባቡር በ1976 ኬን በተባለው ፀሀፊ የተፃፈውና ለአጭር ቀናት በስራ ላይ የቆየው ባቡር ነው:: ሁለተኛው ሙሉ አካሉ በጽሁፍ ያሸበረቀው ባቡር በ1977 የታየው «የገና ባቡር» በመባል የሚታወቀውና "The Fabulous Five" በተባለ ቡድን አባላት የተፃፈው ነው::

### ሐ. የግድግዳ ላይ ጽሁፎች የአፃፃፍ ዘዴ(Writing styles)

በግድግዳ ላይ ስምን ወይም ቅፅል ስምን መፃፍ በበርካታ ወጣቶች እየተለመደ መምጣት የተለየ ዘዴ የመፍጠርን አስፈላጊነት አጉልቶታል:: የአንዱን ስራ ከሌላኛው ለመለየት የተለያዩ የፊደል ቅርፆችና ቀለሞች መጠቀምን አስፋፍቷል:: ዘዴን ወይም ስልትን በተመለከተ ቮልካን የተባለ ፀሀፊ "The Style under ground" በሚለው መፅሀፉ ገፅ5፣ እንዲህ ብሏል ሲል ዴናንት ይገልፃል:: «የአፃፃፍ ስልት(Style) እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፤ አንተነትህን ይገልፅልሀል::»[13] የተለያዩ የአፃፃፍ ስልቶች መስፋፋት የጀመሩት «ቲ 90 ኤፒካት 126» የተባለ የፊላደልፊያ ፀሀፊ ከንደኛው ኮርንብሬድ የወረሰውን «ረጅም፣ ቀጭንና የተጠጋጉ ፊደላትን በጠባብ ስሌዳ ላይ» የመፃፍ ስልት ወደ ማንሀታን ከተማ ካመጣበት ጊዜ ጀምሮ ነበር:: ሌሎች ፀሀፊዎችም የየራሳቸውን የአፃፃፍ ስልት መከተል እየጀመሩ መጡ::

አንዳንዴም አሻሽሎ አዲስ ስልት በመፍጠር መጠቀም ዕውን ሆነ:: ለምሳሌ «ኮል 223» ያስተዋወቀውን ስልት ፌዝ 2 በራሱ መንገድ አሻሽሎ ተጠቀሞበታል:: በዚህም መሠረት አብዛኞቹ ፀሀፊዎች ከሚጠቀሙባቸው ስልቶችና ቴክኒኮች የሚከተሉትን ዴናንት አስፍሯል::

1. **"Wild style"**:- የማይነበቡ እርስ በርስ የተቆላለፉ አቅጣጫና እንቅስቃሴን የሚያመለክቱ ፊደላትን የመፃፍ ስልት ነው::
2. **"3D"**:- በደብዛዛና በተደባለቁ ቀለማት የሚፃፉ ፊደላት የመፃፍ ስልት ነው::
3. **"kase 2"**:- የተሰባበሩ የኮምፒውተር በሚመስሉ ፊደላት የመፃፍ ስልት ነው::
4. **"3-DS"**:- በተሻሻሉ የድሮ አፃፃፍ ስልቶች የመጠቀም ስልት ነው::

ከነዚህ የአፃፃፍ ሰልቶች በመጀመሪያው"Wild style" በሚባለው ስልት የሚፃፉ የግድግዳ ላይ ጽሁፎች ከንዑስ ባህሉ ውጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች አይነበቡም፤ ወይም ግልፅ አይሆኑም:: ዶንዲ የተባለ ፀሀፊ ስለዚሁ ጉዳይ /ቻልፋንትና ክፐር፣ 70-71/ ጠቅሶ ሲገልፅ እንዲህ ይላል:: «ፀሀፊው ለሌሎች ፀሀፊዎች ሲፅፍ ዋይልድ ስታይልን ይጠቀማል:: ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል ሲፅፍ ደግሞ መደበኛ ሊባሉ የሚችሉ ቃላትን ይጠቀማል::»[14]

በዚህ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ስር የግድግዳ ላይ ጽሁፍ አጀማመር፣ ምንነት፣ የጽሁፎቹ ዓይነቶች፣የአፃፃፍ ቅርፅና የአፃፃፍ ስልት ወይም ዘዴ ለመተንተን እንደተሞከረው ጥበቡ ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ሊሳተፍበት የሚችል፣ ስራው ድንበር የለሽ፣ ፆታና ሀይማኖት፣ የዘርና የጉሳ ልዩነት ሳይገድበው የሰው ልጆች የሀሳብ መለዋወጫና የመግባቢያ ዘዴ ነው:: የህብረተሰቡን የኑሮ ዘይቤ ፣ የህይወት ልምዱን፣ ጥሩና መጥሮ የሆኑ ገጠመኞቹን የማንም አስገዳጅነት በሌለበት በምናቡ ምሪት የተሰማውን ስሜት

ያስገደብ ከሰው እይታ ተከልሎ ሊተነፍስ የሚችልበት የስነቃል ንዑስ ክፍል ነው። ስዚህም እንደ አስረጅ የብራድሊ ጀ ባርቶሎሚኦ፣ በአንትሮፖሎጂ ሆነር ጥናቱ /2001/ ላይ ሱዛን ፊሊኘስ «ዋልባንጊንግ» በሚለው መጽሀፏ ስለግድግዳ ላይ ጽሁፍ ጥበብ የሚከተለውን ማብራሪያ እንደሰጠች ምንጭ ጠቅሶ ያስፈረውን ማስታወስ ተገቢ ነው።

> የግድግዳ ላይ ጽሁፍ የሰዎችን ህይወት የምረዳበትን ዕድል ስጥቶኛል። ይህ ዕድል ጉጂ በተባለ ነገር ውስጥ ጠቃሚ የሆነ ነገር፣ ፀያፍ በተባለ ነገር ግብረገብነትን እንድመለከትና ለምኖርበት ጊዜና ቦታ ምስጋና እንዲኖረኝ የሚያደርግ የፈጠራ ችሎታና የታሪክ እውቀት እንዳገኝ አስችሎኛል።[15]
>
> /ፊሊኘስ በብራድሊ.ጄ.ብ፣ 1999፣351 /

ለማጠቃለል እንደ ፓሜላ ዴናንት የቀደመ ምንጭ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ ጥበብ ሲነሳ ኒዎርክ ከተማ የመጀመሪያዋ ተጠቃሽ ናት፤ ምክንያቱም ጥበቡ ተፀንሶ የተወለደው በኒዎርክ ከተማ ነው። ኒዎርክ የጥበቡ መዲናና የባህል ማዕከልም ናት። የግድግዳ ላይ ጽሁፍ በኒዎርክ ከተማ የተጀመረው በ1960ዎቹ መገባደጃ ላይ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የተስፋፋው በከተማዋ 204ኛ ጐዳና ይኖር የነበረ ጁልዩ የተባለ ወጣት ስሙንና መለያውን የባቡር መሄጃ ግድግዳ ላይ «ጁልዩ 204» ብሎ እ.ኤ.አ በ1968 ከፃፈ በኋላ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በከተማዋ ህንፃዎች በብዙ ቦታ በመነበቡ ነበር። በመቀጠልም ዲሚጥሮስ የተባለ ግሪካዊ ወጣት «ታኪ 183» የሚል ጽሁፍ በኒዎርክ ግድግዳዎች መፃፍ ከጀመረ አንስቶ ጉዳዩ ያስገረመው «የኒዎርክ ታይምስ ጋዜጣ» ሪፖርተር /ዘጋቢ/ «ታኪ 183 የብዕር ጓደኛ እየሳበ ነው።» በሚል ከፃፈ በኋላ በርካታ ወጣቶች ሀሳባቸውን በየግድግዳው መግለፅ ጀመሩ። ይህም «ሂኘሆኘ ግራፊቲ» የሚባል በግድግዳ ላይ የመፃፍ የህዝብ እንቅስቃሴ እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኗል።

እ.ኤ.አ. በ1970ዎቹ ጥበቡ የተስፋፋበትና ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ያሳየበት ጊዜ ነበር። የሂኘሆኘ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ የተወለደው በአሜሪካ በወቅቱ በነበረው ማህበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ መድልዎ ምክንያት ነበር። ወቅቱ የፖለቲካ አለመረጋጋት የሰፈነበት፣በርካታ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱበት ነበር። በሌላ በኩልም ድህነት፣ ቤት አልባነት፣ ስራ አጥነት፣ ዘረኝነትና ወንጀል ከቬትናም ጦርነት በኋላ የተፈጠረው ቀውስ የህብረተሰቡን ኑሮና የሀብት ልዩነት ያራራቀበት ጊዜ እንደመሆኑ ወጣቶቹ የግድግዳ ጽሁፍን የጭቆናቸውን አስከፊነት መግለጫ፣ የተነፈጉትን መብት መተንፈሻና ብሶት ማውጫ አድርገው እንዲጠቀሙበት ማስገደዱ ጥበቡ የአሜሪካ ባህል ሂኘሆኘ ንዑስ ባህል እንዲሆን አድርጐታል።

የግድግዳ ጽሁፍ ጥበብ ዕድገት እያሳየ መጥቷል:: በዝቅተኛው፣ በመካከለኛውና የወግ አጥባቂው የላይኛው መደብ ህዝቦች ሳይቀር ዘልቆ የገባ የመግባቢያ ዘዴ ሆኗል፤ ነገር ግን ጥበቡ አያሌ ችግሮችና ፈተናዎች በዕድገት ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲያሳድሩበት ቆይተዋል:: ከነዚህም ችግሮች ውስጥ አንዱ የጥበቡ ፀሀፊዎች በሚጠቀሙአቸው ፀያፍና የብልግና ቃላት ምክንያት ጥበቡ ሆን ተብሎ የህዝብ ንብረትን የማጥፋት ዘመቻ ነው የሚል ተቃውሞ ገጥሞታል:: ከዚህ በተጨማሪም የከተማ መዝቀጥ ምክንያት ተደርጎ ከመወሰዱም በላይ ወጣት አጥፊነትን ያስፋፋል የሚል ተቃውሞም ገጥሞት ነበር:: ነገር ግን ጥበቡ ራሱ በሚያሳየው ባህሪና ልምድ እንዲሁም በጥበቡ ሰዎች ከፍተኛ የማስተማርና የማሳወቅ ትግል የግድግዳ ጽሁፍ ጥበብ የከተማ ባህል መዝቀጥ ምክንያት ሳይሆን ውጤት መሆኑን፤ ጥበቡ የህዝብ ንብረት ማጥፊያ ሳይሆን ለጭቆና አሻፈረኝ ባይነት በትክክል የሚገለፅበት የሰው ልጅ ምናብ የወለደው ድንቅ የመግባቢያ ዘዴ መሆኑን አስመስክሯል:: ማንኛውም ሰብአዊ ግንኙነት ተናጋሪና አድማጭ እንዳለው ሁሉ በግድግዳ ጽሁፍ ጥበብ ውስጥም ፀሀፊዎቹ ተናጋሪዎች ሲሆኑ ህብረተሰቡ ደግሞ አድማጭ ነው:: የኪነጥበብ ስራዎች ደግሞ አድማጭ ወይም ተመልካች ካላቸው ማህበራዊ ፋይዳቸው የጐላ እንደሆነ የተለያዩ ምንጮችን በመጥቀስ ዴናንት ፅፏል::

ከዚህ በተጨማሪም በ21ኛው ክፍለ ዘመን የግድግዳ ጽሁፍ የባህል ማስተዋወቂያ መድረክ ሆኗል:: ወደ ተወዳጅ የኪነጥበብ ክፍልነት ተቀይሯል:: ዕድገቱ በከፍተኛ ደረጃ እመርታ እያሳየ የመጣና ጥበቡ ወደ አውደ-ርእይ ማሳያ ቦታዎች መሄዱን ቀጥሏል:: ለቱሪስቶች መስህብ በመሆንም በሚያልፉባቸው ጐዳናዎች የነዋሪዎቹን እውነተኛ የህይወት ገፅታ ሊመለከቱ የሚችሉበትን መነሻ ሀሳብ ያስጨብጣል:: ይህ ጥበብ እጅግ ሰፊና ጥልቅ በመሆኑም በምልዐት ለማብራራት በሰፊው መጠናት ያለበት ጥበብ መሆኑን እንረዳለን::

ከዚህ ቀጥለን በኢትዮጵያ መዲና ውስጥ በሚገኘው የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ የተፃፉ የግድግዳ ጽሁፎችን ይዘት እናያለን::

# ምዕራፍ ሁለት

# የግድግዳ ጽሁፎች ይዘት ትንተና

## 2.1 ፍቅር ነክ ጽሁፎች

የግድግዳ ጽሁፍ የሰው ልጅ በአእምሮው የሚመላለሰውን ማንኛውም አይነት ውስጣዊ ስሜት (ብሶቱን፣ደስታውን፣የሚያዝንበትን ጉዳይ) በፊት ለፊት ማለት የማይሻውን ድብቅ ጉዳይ ሁሉ በአንደበቱ የሚገልፅበት የስነቃል ዘርፍ ነው። በመሆኑም የሰው ልጆች በጥበቡ አማካይነት የማህበራዊ ህይወታቸውን ገፅታ፣የትምህርት ሁኔታቸውን፣የፍቅር ህይወትና ሁነቶቻቸውን፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ላይ ያሏቸውን አመለካከቶች ያሳዩበታል። ከዚህ በተጨማሪም እንዲሆን የሚሹትን ለመጠቆም ፣ለመምከር ፣ ለመገሰፅ ፣ ለማሳሰብና ለማስጠንቀቅ ይጠቀሙበታል።

ከዚህም ሌላ ስለ ፍቅር በሚያነሷቸው ውስን የግድግዳ ጽሁፎች ውስጥ የፍቅራቸውን ፅናት፣ ሃያልነት ፣ ያደረባቸውን የጥላቻ ፣የቅናት፣ የበቀል፣የቁጭት፣ የአድናቆትና የንቀት ሁኔታዎች እንዲሁም በገሀድ በሰዎች መካከል ሊናገሯቸውና ሊገልጿቸው ያልደፈሩ ሀሳቦችን አይነኬ ወይም ሀራም ቃላትን በመጠቀም ሲገለፁ ይስተዋላል።

ስለ ፍቅር ነክ ጽሁፎቹ ከማየታችን በፊት የፍቅርን ምንነት የተለያዩ ታላላቅ ፈላስፎች የተለያዩ ትንታኔዎችን በመስጠት ይገልፁታል። ለምሳሌ ሊዎ ቶልስቶይ፣ «የታሪክ ምሁራን ደንቆሮዎች ናቸው። ማንም ሰው ያልጠየቀውን ጥያቄ ይመልሳሉ። ማንም ሰው በፍቅር እንጂ ራሱን ስለተንከባከበ መኖር እንደማይችል ተገንዝቤያለሁ።»[16] ዮሀናን፣ (1996፣37) ይላል። ከዚህ አባባል እንደምንረዳው ፍቅር ህይወት ነው። ፍቅር የጥሩ ኑሮና ህይወት ምክንያት መሆኑንና ፍቅር ከሌለ ምንም አይነት እንክብካቤ ቢኖረን ህይወትና ኑሮ የተረጋጋ ነው ማለት አለመቻሉን እንገነዘባለን። ይህም የፍቅርን ሀያልነት ያበስረናል። በሌላ አባባል ለመደገፍም ዮሐናን ኤመርሰን የተባለውን ፈላስፋ ጠቅሶ "ገነት ማለት ሁል ጊዜ ፍቅር ያለበት ቦታ ነው።"[17] (1996፣31)ይለናል። ይህም አባባል የሚገልፀው ዘላለማዊ ህይወት ያላቸው ፃድቃን የሚቀመጡበት ቦታ ሰማያዊው ገነት የፍቅር መገኛ ተምሳሌት መሆኑን ነው። ስለዚህም ከአባባሉ የምንረዳው ፍቅር የምድራዊው ገነት መገኛ መሆኑን ነው። ይህም የፍቅርን ሃያልነት የበለጠ ያገዝፈዋል። ከላይ እንዳየነው የተለያዩ ፈላስፎች ስለፍቅር ብዙ ቢሉም ሰዎች ደግሞ እንደየገጠመኞቻቸው በተለያየ መልኩ ይገልፁታል። ከዚህ ቀጥሎ ስለፍቅር ነክ የግድግዳ ጽሁፎች ጥቂት ምሳሌዎች እንመልከት።

<u>ምሳሌ 1፡-</u> «ፍቅር ነፍጉኛል» ስትል

መላሽ ደግሞ «ፍርድ ቤት ክሰሺው»

በሚል የፌዝ ምላሽ የሰጠበት ጽሁፍ የተገኘው ከላይኛው ቤተመፃህፍት ነው። የጽሁፉ ይዘት ፀሀፊዋ የፍቅር ተጓዳኟ ፍቅሩን የቀነሰባትና ቸልተኛ መስሎ የታየበት ሁኔታ እንዳጋጠማት ያሳያል፣ ወይም በሌላ መልኩ ደግሞ ገና ያልተጀመረ የአይን ፍቅር ገጥሟት ውዴታዋን ለማሳየት ያደረገቻቸው ሙከራዎች ሁሉ ሳይሳኩ ቀርተው ፍቅሩን አፍቃሪዋ በምትፈልገው መልኩ መስጠት ያልቻለ አንድ ሰው መኖሩን ጽሁፏ ይጠቁማል። ይህንኑ ሀሳቧን በግልፅ ለተፈቃሪው ልትነግረው ወይም ለሌላ ሰው ልታካፍለው ወይም ልታዋየው ያልቻለችውን ሀሳቧን በግድግዳው በመፃፍ የውስጧን የሀሳብ ጭንቀት የተነፈሰችበትን ሁኔታ ያሳያል። ምላሽ ሰጪው/ዋ/ ደግሞ በፌዝ መልክ ክሰሺው የሚል መፍትሔ የለሽ ምላሽ ስጥቶ/ታ/ ስናይ ፍቅር በመፈቃቀድ መሆኑ ቀርቶ በክስና ግዴታ መፍትሔ የሚያገኝ ቀላል ጉዳይ ተደርጐ የታየበት ሁኔታን ያሳያል። ፍቅር ስሜት፣ መቀራረብ፣ መለማመድና መጣጣም መሆኑ የተዘነጋበት አስተያየት ሆኖ እናገኘዋለን።

<u>ምሳሌ 2፡-</u> «ብር ዛፍ ላይ ቢበቅል ኖሮ <u>ወንድ ልጅ</u> ጠጣ /ዝንጀሮ/ ያፈቅር ነበር።»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ነው። የተሰመረበት ሀረግ «ሴት ልጅ» በሚለው ሀረግም ተተክቶ መፃፉን ያስተዋልኩበት ሁኔታ አለ። ይህ አባባል ደግሞ ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ከእንስሳት ጋር ለማመሳሰል የሞከረ ነው። ሰዎች ከሰው ፍቅር ይልቅ አፍቅሮተ ንዋይ የሚያሸንፋቸው መሆኑን፣ ገንዘብ ካገኙ የሚመርጡት ነገር አለመኖሩን ሴቶቹንም ወንዶቹንም ተወቃሽ ያደረጉ በሁለቱም ፆታዎች የተፃፉት የግድግዳ ጽሁፎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ጽሁፍ የምንረዳው ሰዎች እርስ በርሳቸው ከየገጠመኞቻቸውና ከገሀዱ ዓለም እውናዊ አጋጣሚ በመነሳት የንዋይ ፍቅር የሚፈታተናቸውን ሰዎች ለመምከርና ለመገሰፅ እንዲሁም ለማስጠንቀቅ የተጠቀሙበት መሆኑን ነው።

<u>ምሳሌ 3፡-</u> «መለያየት ያለ ነው ያለመረሳሳት ግን ወሳኝ ነው።»

ይህ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍልም ከሴቶች መኝታ ቤትም ነው። በይዘቱም በአጋጣሚ ምክንያት የተለየችው/ያት/ጓደኛ ወይም ፍቅረኛ ሊኖር መቻሉንና የተለየው ሰው ግንኙነቱን የቀነሰበት /ችበት/ መሆኑን ይጠቁማል። ስለዚህም «ከአይን የራቀ ከልብ የራቀ ነው።» የሚለውን ብሂል እውነተኛነት እንዳታስመሰክሩ የሚል ይመስላል። ራቅን ብላችሁ ጓደኛችሁን አትርሱት። ለማስታወስ ጊዜ ይኑራችሁ የሚል ምክር ለጋሽ ዓይነት ጽሁፍ ነው።

<u>ምሳሌ 4፡-</u> "See three, choose two, love one."

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። የዚህን ጽሁፍ ይዘት ስንመለከት ማፍቀር አንድን ነው። በአንድ መወሰን ይበጃል። የሰው ልጅ ሲያፈቅር የሚገባው አንድ ሰው ብቻ ነው፣ ነገር ግን የሚያፈቅረውን አይቶና መዝኖ መምረጥ

አለበት የሚል አንድምታ ያለው ነው:: ሰዎች በዕድሜ አስገዳጅነት ምክንያት የተለያዩ ሰዎችን በፆታቸው ተቃራኒ መቅረብ ይሻሉ:: ብዙ ሊያዩ ይችላሉ፤ ቢሆንም ግን ሶስት ሰው እይ፣ ሁለት ምረጥ፣ ከሁለቱ ወደ አንዱ በማድላት አንድ አፍቅር:: በአንድ ተወሰን የሚል ምክር አዘል ተሞክሮውን በብዕሩ ለሌሎች ለማካፈል የተጠቀመበት መሆኑን እናያለን::

**ምሳሌ 5:-** በግጥም መልክ የቀረበና በመማሪያ ክፍላቸው የተገኘው

«ሰው ከሆንክ አፍቅር፣

ወፍ ከሆንክ ዘምር::» የሚለው ነው::

በዚህም ፀሀፊው/ዋ/ የሰው ሰውነቱ የሚለካው ወይም የሚታወቀው ማፍቀር በመቻሉ ነው ለማለት ያስበ/ች/ ይመስላል:: የማያፈቅርና የማይፈቀር ሰው መሠረታዊ ፍላጐቱ ያልተሟላለትና ከሰውነት ደረጃው ዝቅ ያለ ነው:: ሰውም ለማፍቀር፣ወፍም ለመዘመር የተፈጠሩ ናቸው የሚል አንድምታ አለው:: ስለዚህም እኔ በሄድኩበት መንገድ ተጓዙበት አይነት መልዕክት አለው:: ማፍቀርና መፈቀር ሊቀር የማይገባው ለፍጡራን የተሰጠ ፀጋ ነው በማለት ታዳሚውን ያበረታታል::

**ምሳሌ 6:-** ቀጣዮ ፀሀፊ ደግሞ ሀሳቡን በአፋዊ ግጥም እንዲህ ሲል ይገልፃል::

«አባትሽ ይሙቱ ኮሶ ጠጥተው፣

አሳድረውኛል ካንቺ ለይተው::»

ይህ ጽሁፍ የተገኘው ከወንዶች መኝታ ቤት ነው:: በይዘቱም ፀሀፊው የፍቅሩንሀያልነት ለመግለፅ ካንቺ ከምወድሽ ፍቅሬ ለአንድ ቀን ለይተው ያሳደሩኝ አባትሽ ቢሞቱ ደስተኛ ነኝ ይላል:: ምክንያቱንም ሲገልፅ በፍቅራችን መሀል ገብተው አንቺን እንዳጣ አድርገዋል:: ለዚህ በደላቸው ሞት ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ነው የሚል አይነት አስተሳሰብ ያንፀባርቃል:: ካንቺ የሚለየኝ ማንም ይሁን ማን ባይኖር እመርጣለሁ በማለት የፍቅሩን መሻት ለመግለፅ ሞክሯል:: የፍቅሩ ሀያልነት በአባትና በልጅ መሀል ሊኖር የሚችለውን ፍቅር ለማሰብ እንኳን እንዳላስቻለውና አስተውሎቱን እንደሰረቀበት ማየት ይቻላል:: በፍቅረኛው ዘንድ ሀሳቡ ተቀባይነት ይኑረው አይኑረው ለፀሀፊው ምኑም አይደል:: እሱ ውስጣዊ ስሜቱን ግን ተንፍሶ አባቷን በብዕሩ ተበቅሏል:: ፀሀፊው ሁኔታውን ለጓደኞቹ ማጫወት አልደፈረም፤ ለምን የሚል ጥያቄና ይሉኝታ እንዳይናገር ያደረጉት ይመስላል:: ይህም የግድግዳ ፀሀፊ በፊት ለፊት ለማለት የማይደፍረውን በሚስጥር ለመግለፅ የሚጠቀምበት ስንክናዊ ሀብቱ መሆኑን ያሳያል::

**ምሳሌ 7:** «ፍቅር ውሀ የማያጠፋው እሳት ነው::»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ነው:: ይዘቱም የፍቅርን ሀያልነት የሚያመላክት ነው:: ምንም ዓይነት ነገር ወይም ሀይል ሊያጠፋው የማይችል ከባድ ነው:: ማንም ሰው በውስጡ የሰረፀውን ፍቅር ሌላ ወገን ሊፍቀው በቀላሉ ሊያጠፋው

የማይችለው ነው። ፍቅር ውስጣዊ ደስታ፣ ስሜትና እርካታ ነው። ይህ ረቂቅ የሆነ ነገር ከልብ ጓዳ እስከ አዕምሮ አፅናፍ ድረስ ያለውን የሰው ልጆች ውስጣዊ ስሜትና ቀልብ የሚገዛ ነውና ራሱ ባለቤቱም ቢሆን እንኳ ሊያጠፋው በአንዱ ዕልም አድርጐ ሊገላገለው የማይችል ሀይል እንዳለው የገለፀበት ነው።

**ምሳሌ 8፡-** «L - Lake of sorrow

O - Ocean of tears

V - Valley of Death

E - End of life»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ነው። የጽሁፉ ይዘት የሚያመለክተው ፀሀፊው ለፍቅር ያለው አመለካከት አሉታዊ የሆነ መሆኑን ነው። አንዳንድ ሰዎች በአጠቃላይ ስለፍቅር ጨለምተኛ የሆነ pesimistic አመለካከት አላቸው። ነገሩን ገብተው ሳያዩት ገና በሩቅ የሚፈሩት ሰዎች መኖራቸውን የሚያመለክት ነው። ስለምንነቱ ምንም ሳያውቅ ይህም ፀሀፊ የሀዘን ሀይቅ፣ የእንባ ውቅያኖስ፣ የሞት ሸለቆነቱንና የህይወት መጨረሻ መሆኑን ገልጿል። ከዚህ የምንረዳው ሰዎች ስለፍቅር የተለያየ አመለካከት ያላቸው መሆኑን ነው።

**ምሳሌ 9፡-** «ፍቅር አማረኝ ሲል የመጀመሪያው ፀሀፊ

መላሽ ፆም ሲፈታ OK! »

ይህ ጽሁፍ የተገኘው ከላይኛው ቤተመጽሃፍት ነው። የጽሁፉን ይዘት በሁለት መልክ ማየት ይቻላል። ፀሀፊው/ዋ/ ፍቅረኛ የሌለው/ላት/ ሆኖ/ና/ ፍቅርና የፍቅር ጨዋታ ከፍቀረኛዬ ጋር ፈለግኩ ማለት ሊሆን ይችላል። መላሽ ግን በፌዝ ወይም ቀልድ በሚመስል ስሜት ምላሹን የሰጠው በሁለተኛው አማራጭ ሀሳብ ላይ ተንተርሶ ሲሆን የጊዜውን ምቹ አለመሆን በፆም ሰዓት ሰዎች አካላቸውን የሚያዳክሙበት ጊዜ በመሆኑ የፍቅር ጨዋታ ማድረግ እንደማይችሉ ያለውን እምነት በሚገልፅ መልኩ እሺ.ታውን ግን የፆሙ ጊዜ ሲያልቅ እንደሚከውኑት ይገልፃል። ይህም ጥበቡ የድብቅ ስሜቶች መግለጫ መሆኑንና በቀልድም ራስን የሚያዝናኑበት ከአዕምሮ ውጥረት ለመላቀቂያና ለመተራረብም ጥቅም ላይ ሲውል መቻሉን ያሳያል።

## 2.2. ትምህርት ነክ ጽሁፎች

እንደሚታወቀው ሁሉ ትምህርት የሰውን ልጅ የአካልና የአዕምሮ ተስጥኦ በማዳበርና በማበልፀግ በህይወት ውስጥ የሚያጋጥሙትን ችግሮች የማወቅና ችግሩን የመፍታት ችሎታ የሚያስጨብጥ፣ የተለያዩ ዕውቀቶች መገኛ ምንጭ ወይም መሣሪያ ነው። ይህ መሣሪያ ታዲያ እንደቀልድ ወይም እንደ ዘበት የሚገኝና የሚዘገን ሳይሆን

ከብዙ ልፋትና ድካም፤ እንዲሁም ጥረት በኋላ ሁለንተናዊና የተሟላ ሰብዕና በመስጠት በሰው ልጆች ላይ ትርጉም ያለው የባህሪ ለውጥ የሚከስት ተግባር ነው፡፡

በመሆኑም ይህን የማያልቅና የማይነጥፍ ሀብት የሰው ልጅ መደበኛና ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ ይቀስመዋል፡፡ በዚህ የመቅሰም ሂደት ውስጥ እንደየግል ዝንባሌውና ስሜቱ ያሉትን ትምህርት ነክ አስተያየቶች፣ ግንዛቤዎችና ሀሳቦች ሁሉ ማውጋት መተንፈሱ አይቀሬ ነውና በስዕሎቹ ወይ በጽሁፎቹ ሀሳቡን ይገልፃል፡፡

**ምሳሌ 1፡-** «ተምረህ አለቃህን ቀንስ»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ በይዘቱም መማር ማለት በልጦ መገኘት ነው፡፡ በመማርህ ከተከታይነት ተላቀህ ወደ መሪነት መድረስ ትችላለህ፡፡) ለዚህም ተግባር ዋናው ቁልፉ መማር ነው፡፡ ከታዛዥነት ወደ አዛዥነት ሽግግር፣ ቀዳሚነት የሚገኘው በመማር መሆኑን ተገንዝበህ በትምህርትህ ጠንክር የሚል መልዕክትን ያስተላለፈበት ጽሁፍ ነው፡፡ በተጨማሪም የትምህርትን ጠቃሚነት ለአንባቢው ሁሉ የሚያስገነዝብ ጽሁፍ ነው፡፡ የሚቀጥለውን ምሳሌ ስንመለከት ደግሞ በተቃራኒው ሀሳቡን ሲገልፅ እናያለን፡፡

**ምሳሌ 2፡-** "Learning is burning"

ይህ ጽሁፍ የተገኘው በወንዶች መኝታ ቤትና በመማሪያ ክፍልም ነው፡፡ በይዘቱም መማር መቃጠል ነው ይለናል፡፡ ከክብደቱ፣ ከብዛቱና ከስፋቱ አኳያ ሲታይ መማር አስቸጋሪ ስለሆነ፣ ከስነዘዴው አቀራረብና አካሄድ ጋር ያልተጣጣመ ተማሪ ፣ በመማር ሂደት የመቀበል ችግር ያጋጠመው ተማሪና የውጤት ማሽቆልቆል የታየበት ተማሪ ትምህርትን በዚህ አባባል ሊገልፀው የሚችልበትን ሁኔታ ያሳያል፡፡

**ምሳሌ 3፡-** «አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል፡፡»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ በይዘቱም ንግግር የአዕምሮ ብስለትን ወይም ጮርቃነትን ሊያሳይ የሚችል ሀይል አለው የሚል አስተሳሰብን አጉልቶ ያሳያል፡፡ ሰዎች በንግግራቸው ስለዓለም ያላቸውን አተያይ፣ ግንዛቤያቸውን፣ እምነታቸውንና ፍላጐታቸውን ይገልፃሉ፡፡ ከንግግራቸው የብስለት ደረጃቸውን ለመለካት አያዳግትም፤ ምክንያቱም ንግግር የውስጣዊ አስተሳሰብና ስሜት ነፀብራቅ ነውና፡፡ የሰው ልጅ ከድጋፍ ተቃውሞው አመለካከቱን፣ ከፍቅርና ጥላቻው እምነትና ፍላጐቱን፣ ከተለያዩ ገለፃዎቹ ልዩ ልዩ ግንዛቤዎቹን አውቆም ይሁን ሳያውቅ ለሌሎች ገሀድ ያወጣል፡፡ ስለዚህም ይህ ፀሀፊ ስትናገሩ አንተነትህን ወይም አንቺነትሽን ትገልፃለችሁና «ከመናገራችሁ በፊት ደጋግማችሁ አስቡ፡፡» የሚለውን ብሂል እውነተኛነት ለማሳየት የሞከረበት ነው፡፡

<u>ምሳሌ 4፡-</u> ይህ በምልልስ መልክ የቀረበ የግድግዳ ጽሁፍ ነው፤

«ፕረዘንቴሽን ስለቸኝ!»

መላሽ፡- «አይ አንተ! የት ልትደርስ?» አሊያ በ "D" ተንደር

ድረሽ ባንዲራሽን ሰቅለሽ ወደ አገርሽ መመለስ ነዋ !»

ይህ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ የዚህ ጽሁፍ ይዘት ንግግርንና ግለሰባዊ ተሳትፎን የሚጠይቁ ስራዎች ላይ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች የሚሰነዝሩት ዓይነት ጽሁፍ መምስሉ ነው፡፡ ይኸውም በተማሪዎች ፊት ወጥተው ደፍረው የመናገር ችግር ያለባቸው፣ በራስ ያለመተማመንና ፍራቻ ያለባቸው ተማሪዎች ሊሆኑ ይችላል፡፡ መላሽ ደግሞ «ፕሪዘንቴሽን» ከትምህርቱ ውስጥ አንዱና ሊተገበር የግድ የሆነ ክፍል መሆኑንና ያ ክፍል ከተጠላ የት ይደረሳል በሚል ሀሳቡን በጥያቄ ስንዘሮ የውጤቱን አስከፊነትም ይገልፃል፡፡ የምታልሙት ህልም እንዲሳካ፣ ውጤታማ እንድትሆኑና ራሳችሁንም ከ"F" ውጤት ለመታደግ ጠንክራችሁ መስራት አለባችሁ አለበለዚያ ትምህርቱን ትቶ ወደ ሀገር መግባት ነው፡፡ ስለዚህም «ፕሪዘንቴሽን» የማይቀር ነገር ነውና ከመባረር መስራት ይመረጣል የሚል ምክር አዘል የማስጠንቀቂያ መልዕክት ያስተላለፈበት መሆኑን እናያለን፡፡

<u>ምሳሌ 5፡-</u> «እባክህ ህፃን ይመስል ባገኘሽው ነገር ላይ አትፃፍ! እንደ ሰው አስብ»

ይህ ጽሁፍ የተገኘው ከመፀዳጃ ቤት ነው፡፡ የጽሁፉ ይዘት ስንመለከተው ከተገኘበት ቦታ አንፃር በፊት ለፊት ደፍሮ መናገር የማይቻለ ዓይነት ወሲብ ነክ ጽሁፎች የሚስተናገዱበትን ቦታ የሚይዘውን ሁሉ የሚቃወም ዓይነት ነው፡፡ ይህም ካደግንበት ወይም ከኖርንበት ማህበረሰብ ባህል ጋር የማይጣጣሙና ግልፅ ወሲባዊ ስሜቶችን የሚያንፀባርቁ ዓይነት ጽሁፎች መገኘታቸውን የሚኮንን ነው፤ እንደዚህም ግልፅ ፅሁፎችን የሚፅፍ ክፉውንና ደጉን መለየት ያልቻለ አፀያፊ ይሁን አሳፋሪ ማመዛዘን ያቃተው ህፃን ብቻ ነው የሚል ይመስላል፡፡ «እንደሰው» አስብ የሚለው ሀረግም እንደ አዋቂነት፣ እንደትልቅነትህ ማሰብ አለብህ እንጂ የህፃን ባህሪ መያዝ የለብህም የሚል ምክር አዘል ስነ-ምግባራዊ ሂስ ይዟል፡፡ ከትምህርትና ከስነቃል ወይም ከየግድግዳ ጽሁፍ አኳያ የጽሁፉን ይዘት ስናየው ደግሞ ባገኘው ነገርና ቦታ ባገኘው ጊዜ ስሜትን ወይም ሀሳብን መግለፅ ከሰውነት ባህሪ የወጣ ነው፤ ሰው የሆነና እንደሰው የሚያስብ ሁሉ ባገኘው አጋጣሚና ጊዜ ተጠቅሞ ያሰበውንና የተሰማውን ዝም ብሎ ያለገደብ አይፅፍም፤ አያሰፍርምና ይህን የፃፈው ሰው ከሰውነት ባህሪ የወጣ ነው የሚል ፀሀፊዎቹን የሚቃወም ሀሳብ ሲያንፀባርቅ እናያለን፡፡ ይህ ፀሀፊ ግን የሱን ሀሳብ በግድግዳ ጽሁፍ አማካይነት የተሰማውንና ትክክል መስሎ የታየውን ሲገልፅ ወይም ሲያስተላልፍ የሌላውን ሰው በግድግዳ ጽሁፍ አማካይነት በነፃ ሀሳብን የመግለፅ መብት ሲገድብ፣ ሲጋፋና ሲከለክል እናስተውላለን፡፡



ILS LIBRARY

ምሳሌ 6፡- የሚከተለው በግጥም መልክ የቀረበ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በወንዶች መኝታ ቤትና በክፍል ውስጥም ነው፡፡

«ግሬድ መለጠፉን ትላንትና ሰምታ፣
ስታስብ አደረች መባረሯን ፈርታ፡፡»

የዚህን የግድግዳ ጽሁፍ ይዘት በሁለት መልክ ማየት ይቻላል፡፡ በአንድ በኩል ማንኛውም ተማሪ ፈተና ተፈትኖ ውጤት ሲለጠፍ ለማየት በዝግጅት ላይ በሚሆንበት ጊዜ ሁለት ተቃራኒ ስሜቶች ይፈራረቁበታል፤ ማሰቡ አይቀርም፡፡ ውጤቴ ጥሩ ይሆን መጥፎ፤ መጥፎ ከሆነስ የሚከተለው ተግባር ምንድነው? ምን ይሆን ዕጣ ፋንታዬ እያለ መጨነቁ አይቀሬ ነው፡፡ «እሷ» ወይም ተጠቃሽዋ ሴት ሀሳብ ሲያስጨንቃት አድሯል ብሎ የሀዘኔታ ወይም የስሜት ተጋሪነቱን ለመግለፅ የተጠቀመበት/ችበት/ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ዓይነት ስሜት በሁለቱም ፆታ ላይ የሚስተዋል ችግር ሆኖ ሳለ የሴቲቱን ብቻ አጉልቶ ማሳየት ምናልባትም ሴቶች በአስተሳሰብም ሆነ በሞራል ወይም በማንኛውም ስራ ደካሞች ናቸው የሚል የትምክህተኝነትና የሹፈት ዓይነት ስሜት የሚያንፀባርቅ ወንድ ተማሪ የፃፈው እንደሆነ ለመገመት የሚያስችል ነው፡፡

ምሳሌ 7፡- ይህ በግጥምና በምልልስ መልክ የቀረበው የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከወንዶች መኝታ ቤት ነው፡፡ እንዲህ በማለትም ይነበባል፡፡

«እኔ መሄድ መሄድ መሄድ አይታክተኝ፣
ምን እግር አምጥቶ ኮተቤ ከተተኝ፡፡»

መላሽ፡-«ታይቶህ ይሆናላ ከኮተቤ ጀርባ፣
ያቺ ትንሽ ገንዘብ እኪስህ ስትገባ፡፡»

የዚህ የግድግዳ ጽሁፍ ይዘት ፀሀፊው የኮተቤ ኑሮውና ምግቡ፣ ወይም ደግሞ የትምህርቱ ክብደት አስመርሮታል፡፡ በሌላ አማራጭም ከአቅሙ በላይ የሆኑ ሊወጣቸው ያቃተው ችግር ገጥሞታል፡፡ ይህም ኮተቤ የመጣበትን ቀን የሚያስረግሙ ሁኔታዎች ውስጥ ከቶታል፡፡ ስለዚህም ውስጣዊ ስሜቱን ተንፍሶ ጊዜያዊ እፎይታ ለማግኘት የፃፈው ይመስላል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ መላሽ በተሳልቆ ወይም ፌዝ በሚመስል ምላሹን ስጥቶ እናያለን፡፡ በዚህም የፀሀፊውን ችግር የማይፈታ ወይም ችግሩን ለማየትና ለመፈተሽ ፍላጎት ከማጣት ይመስላል፤ ኮተቤን የመረጥከው ወይም ወደ ኮተቤ የገባኸው ያችው ትንሽ ደሞዝ ፍላጎት አሳድራብህ ነው፡፡ የትምህርቱ ወይም ወገንን የማስተማርና የመርዳት ምኞት አይደለም ወደዚህ ያመጣህ የሚል ዓይነት መልስ ሲሰጠው እናያለን፡፡ ይህ የግድግዳ ጽሁፍ ትምህርት የገቢ ምንጭ ሆኖ ማገልገሉን ያሳያል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የገቢ ምንጩ የደለበ ሳይሆን አነስተኛነቱ፣ አለማርካቱና አስደሳች አለመሆኑ የተገለፀበት ነው፡፡ ይህም ፊሊፕስ «የግድግዳ ጽሁፎች ጉዲ በተባለ ነገር ውስጥ ጠቃሚ የሆነ ነገር ... ሊያሳዩ የሚችሉ የፈጠራ ችሎታና ሀሳብ ያሳውቃሉ፡፡»[18] /1999፣351/ ያለችውን እውነታ ያሳያል፡፡ የመጀመሪያው ፀሀፊም በምሬት የገለፀውና ያስገነዘበው ነገር በትምህርት ዓለም

ሊያሌ የህይወት ስንክሳሮች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉና እዚህ ቦታ ባልተገኘሁ ነበር የሚያስብሉ ሁኔታዎች ሊኖሩ መቻላቸውን ነው።

ምሳሌ 8□- ከላይኛው ተቃራኒ የሆነ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በወንዶች መኝታ ቤት ነው። እንዲህ በማለትም ቀርቧል።

«ፍቅርን ከፈለክ ኮተቤ ፣
ማበድ ከፈለክ አራት ኪሎ።»

የዚህ ጽሁፍ ይዘት የሚያመለክተው ኮተቤ ከአራት ኪሎ ትምህርት ጋር ሲወዳደር ፋታ የሚሰጥ፣ ዕረፍት ያለው በመሆኑ ለፍቅር ጊዜ ይኖርሀል፤ በሌላ አገላለፅም ትምህርቱና የትምህርት አሰጣጥ ስልቱ በጣም የሚወደዱ፣ የማያስጨንቁ ናቸው የሚል አንድምታ ያለው ነው። በአንፃሩ ደግሞ የአራት ኪሎ ትምህርት ክብደቱና የትምህርት አሰጣጡ በቀላሉ የሚገመት እንዳልሆነና እስከማበድ ሊያደርስ የሚችል አስቸጋሪ ሁኔታ የበዛበት መሆኑን በመግለፅ የኮተቤ ኮሌጅን በማወደስ ወደዚህ ኑን ያበረታታል።

## 2.3. ማህበራዊ ጉዳይ ነክ ጽሁፎች

### ሀ.ጥቅል ማህበራዊ ጉዳይ ነክ ጽሁፎች

እንደሚታወቀው ሁሉ «ሰው ማህበራዊ እንስሳ ነው።» ይህም ሲባል ህይወቱን ለማቆየት በሚያካሂደው እንቅስቃሴ አንዱ ያለሌላው ድጋፍ መኖር ያለመቻሉና በአካባቢው ከሚገኝ ቁስአካልና ህይወት ካላቸው ነገሮች ጋር ጥብቅ ቁርኝትና ትስስር መፍጠሩ ነው። ዕለት በዕለት በሚያደርገው እንቅስቅሴ ውስጥም ሰው ከሰው፣ሰው ከእንስሳት፣ ሰው ከእፅዋት፣ ሰው ከአካባቢው መልክዐ-ምድር፣ሰው ህይወት ካላቸውና ከሌላቸው ማንኛውም ፍጥረታትና ሰው ከራሱ ጋር በሚኖረው መስተጋብር የሚያጋጥሙትን ምኞት ጉስቁልናውን፣ ሀዘን ደስታውን፣ ውድቀት ብልፅግናውን፣ ርሀብ ጥጋቡን፣ ፍቅር ጥላቻውን፣ እኩይና ሰናይ ድርጊቶቹንና ባህሪያቱን የየገጠመኞቹን ማንኛውም ክስተቶች በቃል በመናገር ወይም በጽሁፍ በማስፈር ይገልፃል። በዚህም የሚገጥሙትን የስሜት ውጥረቶች ያረግባል፤ ምናባዊ ፍስሀና እፎይታ ይጎናፀፋል። ከአዕምሮው ያፈለቀውንም ለመሰሎቹ በተለያዮ አውዶች በስራ፣ በፍቅር፣በኑሮ፣ በልደት፣ በሞት፣ በትምህርትና . . . በመሳሰሉት አጋጣሚዎች ከሚናገርባቸው፣ከሚፅፍባቸው ወይም ከሚደርስባቸው የስነቃል ዘርፎች አንዱ «የግድግዳ ጽሁፍ» ነው።

የሰው ልጅ በማህበራዊ ጉዳይ ነክ ጽሁፎቹ የማህበረሰቡን የኑሮ ልዩ ልዩ መልኮችና ገፅታዎች ባህሉን፣ ወጉን፣ ልማዱን፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አመለካከቱን በመግለፅ በየዘመኑ የነበረውን፣ ያለውንና የሚኖረውን ሁኔታ ሲያሳይ፣ ሲያስገነዝብና ሲተነብይ ይታያል። በዚህ ሂደቱም ሳያስበው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ስነቃሉን እየቀረሰ

ያስፍራል:: ለዚህም ነው ይህንኑ በተለያየ ቦታ የሚተነፍሳቸውንና የሚያስፍራቸውን የስነቃል ክፍሎች ወይም ንዑሳን ዘርፎቹን ሳይጠፉ ቀርሶ ማጥናት፣ መተንተንና መተርጐም ለልማትና ዕድገት እቅድ አነዳደፍ የሚሰጠው ሀሳብና ጠቀሜታ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ፈቃደ አዘዘ /1991፣49/ አጠንክረው የገለፁት::

በመሆኑም በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ ተፅፈው ከሚገኙት ማህበራዊ ጉዳይ ነክ ጽሁፎች ጥቂቶቹን እንመለከታለን::

<u>ምሳሌ 1፡-</u> «አንድ ሰው ሲጠላህ ብቻ ሳይሆን ሲወድህም ለምን በል!»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ነው:: የጽሁፉ ይዘት ሰው በባህሪው ጥሩም መጥፎም ሲሆን ስለሚችል ሲጠላህ ብቻ ሳይሆን እወድሀለሁ ሲልህም ራስህን ጠይቅ:: የፍቅሩን ሁኔታም ከምን አኳያ እንደሆነ መርምር የሚል የማስጠንቀቂያ መልዕክት ያዘለ ነው:: አብዛኛውን ጊዜ የአብዛኛው ሰው ትኩረት የሚጠላውን ሰው መከታተል እንጂ የሚወደውን ሰው መጠራጠር አይደለም:: ነገርግን ፍቅርንም ሆነ ጥላቻን እንዴትና ለምን፣በምን ሁኔታ፣መቼ እንደተከሰቱ ማጥናትና መመርመር ከሚደርስ ስህተት ወይም አደጋ ያድናል የሚል ዓይነት የምክርና የማስጠንቀቂያ መልዕክት ተላልፎበታል::

<u>ምሳሌ 2</u>፡- «በህይወትህ ትኖር ዘንድ መልካሙን እንጂ ክፉውን አትመኝ::»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከሴቶች መኝታ ቤት ነው:: የጽሁፉ ይዘት የሰው ልጅ ሰናይ ባህሪ መገለጫ የሆነውን መልካም ነገር ማሰብን አዘወትር እንጂ ክፉ ነገሮችን መመኘትና ማሰብ የለብህም የሚል በጐ ስነምግባር አስተማሪና ምክር ለጋሽ አስተያየት የተንፀባረቀበት ነው:: በሌላ በኩልም የመኖር መርህ መልካም ነገር ብቻ ማሰብ ነው የሚል አንድምታ አለው:: ነገር ግን የመልካምና የክፉ ነገር ክስተቶች አንፃራዊና እንደ አድራጊው እምነትና አመለካከት የተለያዩ ሲሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ አለ:: ይኸውም በአንዳንድ ሁኔታዎች አስገዳጅነት ሰዎች ክፉ ነገሮችንም የሚመኙበትና የሚያስቡበት አጋጣሚ ስለሚኖር ነው::

ምሳሌ 3፡- «ብዙ እንቡጦችን ለመቀንጠስ ስታሰብ ብዙ እሾሆች
ሊወጉህ እንደሚችሉ እወቅ!»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በወንዶች መኝታ ቤት ነው:: የጽሁፉ ይዘት የምክር ለጋሽነትና የማስጠንቀቂያ መልዕክት አስተላላፊነት ባህሪ ያለው ነው:: የብዙ ልጃገረዶችን ህይወት ለማበላሸት የተሰለፍክ ወይም የቅምክ ከሆነ አያሌ ጋሬጣዎች ተደቅነው እንደሚጠብቁህ ማሰብ አለብህ! ሴሰኛ ባህሪ ካለህ ታቀብ፤ ካልሆነ ግን ብዙ ችግሮች ሊገጥሙህ ይችላሉ:: ከችግሮችህም ብዛት ልትወድቅ ትችላለህና ተጠንቀቅ! ራስህን ከበሽታዎችና ከወንጀል ጠብቅ የሚል ምክር አዘል መልዕክት ተላልፎበት እናገኛለን::

<u>ምሳሌ 4</u>፡- «ተሻገረ ቢሉኝ ያ ቡና ነው ብዬ፣

ተሻገረ ቢሉኝ አበባው ነው ብዬ፣
ለካ ጤፉ ኖሯል ልምድ መድሀኒቴ፣
ባህል ቡቃያዬ፣
ለካ ሚቱ ኖሯል የአፍ ማሟሻዬ፡፡»

ይህ በግጥም መልክ የቀረበው የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በወንዶች መፀዳጃ ቤት ነው፡፡ የጽሁፉ ይዘት የሚያመለክተው ወቅታዊውን የኑሮ ውድነት ካለው ኢኮኖሚ ችግር ጋር በማገናዘብ የጤፉን ለውጭ ገበያ የመቅረብ ሁኔታ የሚኮንን ወይም የሚቃወም ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የቡናና የአበባው መላክ ያን ያህል አላሳሰበኝም፤ ጤፉ ግን የዕለት ከዕለት ልምዴና ባህላዊ ምግቤ ነው፡፡ «የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል»ና ይታሰብበት የሚል መልዕክት ያንፀባርቃል፡፡

<u>ምሳሌ 5</u>፡- «ሰው ማለት ሰው የሚሆን ነው ሰው የጠፋለት፡፡»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በመማሪያ ክፍሎች በብዙ ቦታዎች ላይ ነው፡፡ የጽሁፉ ይዘት የሰው ልጆች ደስታም ሆነ ሀዘን በየጊዜው እየተፈራረቁ የሚያጋጥሙአቸው፣ ህይወት አንዳንዴ ጥሩ በሌላ ጊዜ መጥፎ እየሆነች ተለዋዋጭ ባህሪዋን የምታሳያቸው ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን አጋጣሚ አንዳንዴ ለመቋቋም ብርታት የሚያጡበትና የመሰሎቻቸውን እርዳታ የሚሹበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ በደስታ ወቅት የሚከቡና የማይጠፉ ብዙ ጓደኞች በመከራና በችግር ላይገኙ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በእንደነዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች በተፈለገበት ሰዓት የተፈለገበት ቦታ ተገኝቶ አጋርነቱን የሚያሳይ ሰው ነው ልዩ ክብርና ቦታ ሊሰጠው የሚገባ ይለናል ፀሀፊው፡፡ ፀሀፊው አጋጣሚ ያስተማረውን ሀቅ ለሌሎች ለማስተላለፍ የተጠቀመበት ምክር አዘል አስተያየት መሆኑን እንረዳለን፡፡

<u>ምሳሌ 6</u>፡- «ሰካራም ሰው ባይሞትም አይን ያለው የሚቁለጨለጭ ሬሣ ነው፡፡»ና
«ሰካር በፈቃደኝነት የሚካሄድ እብደት ነው፡፡»

እነዚህ ሁለት የግድግዳ ጽሁፎች የተገኙት ከወንዶች መኝታ ቤት ነው፡፡ የጽሁፎቹ ይዘት ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ ስካር አስከፊ የሆነ ማንነትን የሚያስረሳ፣ ህሊናን ማዘዝ የማይቻልበት፣ ይሉኝታ አሳጥቶ አንጉል ድርጊቶችን ለመፈፀም የሚገፋፋ ሱስ መሆኑን ተማሪው አውቆ ድርጊቱን እንዳይፈፅም መካሪና አስተማሪ ጽሁፎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ትምህርት የነቃና የተረጋጋ አዕምሮ የሚፈልግ በመሆኑም ከስካር ተግባር ጋር ሊጣጣም እንደማይችል አሳይተውብታል፡፡ ይህ ሊወገዝ የሚገባው ማህበራዊ ችግር መሆኑንም ጭምር ለማስገንዘብ ነው ሁለቱ የግድግዳ ፀሀፊዎች የስካርን ጉጂነት ከሬሣና ከአዕምሮ መታወክ ጋር በማነፃፀር በፅኑ የኮነኑት፡፡

<u>ምሳሌ 7</u>፡- «ያገለገሉ ሴቶችን በጨረታ እንሸጣለን!»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። የግድግዳ ጽሁፉ ይዘት ሴቶችን አሳንሶ የሚያሳይና የሚያንቋሽሽ ሆኖ ለፌዝና ተሳልቆ የተፃፈ ይመስላል። በተጨማሪም የሴቶችን ሰብአዊ ፍጡርነት የዘነጋና እንደመገልገያ ቁስ በማየት ወይም በመቁጠር ለሽያጭ የሚቀርቡ ተደርጎ የተገለፀበት ጽሁፍ ነው። ይህ ጽሁፍ ጀብደኝነት ከሚያጠቃው በሴቶች ላይ ጤናማ ያልሆነ አመለካከት ካለው አዕምሮ የፈለቀ ኋላቀር አስተሳሰብን የሚያሳይ ነው። በሌላ በኩልም ለመሳቂያና ፌዝ መፍጠሪያ ሆን ተብሎ የተፃፈ መሆኑን እንረዳለን።

<u>ምሳሌ 8፡-</u> «ከምታማኝ ንገረኝ ከምታኮርፈኝ ምከረኝ»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ነው። የጽሁፉ ይዘት የሀሜትን መጥፎነት ማሳወቅ፣ የውይይትንና የመመካከርን አስፈላጊነት ማስተማርና መግለፅ ነው። ፀሀፊው አንድ ሰው በሌሎች ላይ ስህተት ሲፈፅም አይቶ መንገር እንጂ ያን ግለሰብ በሌለበት ማንሳት ተገቢ ያልሆነ ባህሪ ስለሆነ መወገዝ ያለበት ነው። መነጋገርና መመካከር ግን ችግሮችን የመፍቻ መንገድ ነውና እንተራረም የሚል መልዕክት አስተላልፎበታል። በተጨማሪም የተማረው ማህበረሰብ ሀሜት የሚባለውን ማህበራዊ ጠንቅ ማስወገድ እንደሚገባው አስተምሮበታል።

<u>ምሳሌ 9፡-</u> «ህይወትን አሸንፈው ለቁምነገር የበቁ እንደታላቅ ሳይንቲስት ይቆጠራሉ።»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከወንዶች መኝታ ቤት ነው። እንደሚታወቀው ሁሉ ህይወት አያሌ ጋሬጣዎች የተተከሉባት፣ ችግሮች የበዙባትና በፈተናዎች የተሞላች ናት። ፀሀፊውም ሊያስገነዝብ የፈለገው ይህን ሁሉ ችግር ተቋቁመው ከሚፈለገው የኑሮ እርከን ወይም ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎች እንደ አንድ ትልቅ ግኝት ባለቤት መቆጠር ያለባቸው መሆኑን ነው። ፀሀፊው የሁለቱም ጥረትና ትጋት የሚተናነስ አይደለም ይለናል። በዚህ ጽሁፉም እንጠንክር፤ አርአያነታቸው ጉልህ ነውና እንከተለው ዓይነት መልዕክት አስተላልፎበታል።

<u>ምሳሌ 10፡-</u> «መስራት የቻለ አሸናፊ ነው።»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። የጽሁፉ ይዘት የስራን ክቡርነት የሚገልፅ ነው። የሰው ልጅ በስራ የማያሸንፈው ነገር የለም ይላል ፀሀፊው። ድህነትን ፣ በሽታን፣ እርዛትን፣ድንቁርናን . . . ማሸነፍ የሚቻለው ጠንክሮ በመስራት እንደሆነ ገልጿል። በዚህ ምክር አዘል የግድግዳ ጽሁፍ ወጣቱን ወይም ተማሪውን ለስራ እንዲነሳሳ፣ እንዲበረታታ አስተምሮበታል።

**ምሳሌ 11፡-** «3 ነገሮችን ውደድ!

- ❖ እናትህን
- ❖ ፍቅረኛህን
- ❖ ሀገርህን፡፡»

«3 ነገሮችን ጥላ!

- ❖ ቅናት
- ❖ ምቀኝነት
- ❖ ሌብነት፡፡»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከቤተመፃህፍት ነው፡፡ የጽሁፉ ይዘት የሰው ልጅ ሁሉ እናቱን፣ ፍቅረኛውንና ሀገሩን መወደድ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ፀሀፊው ወይም ፀሀፊዋ፥ እናት ወላጅና በዚህ ምድር የመገኘታችን፥ የመኖራችን ምክንያት ነችና መወደድ አለባት ይለናል፡፡ ፍቅረኛም በህይወት ዘመናችን የደስታችን ምንጭ ነውና ወይም ናትና መወደድ አለባት ወይም አለበት፤ ሀገርም ያላትን ሁሉ የምትሰጥ የማንነታችን ሚስጥር ናትና መወደድ አለባት የሚል ሀሳብ አለው/አላት፡፡ በአንፃሩም የሰው ልጆች እኩይ ባህሪያት መገለጫዎች የሆኑትን ቅናት፣ ምቀኝነትና ሌብነት መጠላት ያለባቸው፣ ውጤታቸው አስከፊ የሆነ ማህበራዊ ችግሮች መሆናቸውን ይገልፃል፡፡ ሰዎች በቅናት ተነሳስተው ሲጠፋፉ፣ በምቀኝነት ለመጣጣል ሲጣላለፉ፣ በሌብነት ለመነጣጠቅ ሲሯሯጡ ማየት አስከፊ ነው ይለናል፡፡ ስለዚህም እነዚህን ነገሮች እናስወግድ የሚል መልዕክት አስተላላፊ ነው፡፡ ጥሩ ስነምግባር አስተማሪ ጽሁፍ መሆኑንም ማየት ይቻላል፡፡ በዚህም ለቤተሰቡ፣ ለወገኑና ለሀገሩ ፍቅር ያለው ዜጋ ወይም ትውልድ እንዲፈጠር ያለውን ፅኑ ምኞት ከመግለፁም ባሻገር ተማሪው ቆም ብሎ እንዲያስተውልና ራሱን እንዲፈትሽ ያበረታታል፡፡

**ምሳሌ 12፡-** «ጓደኛዬ በተሳካለት ቁጥር በውስጤ አንድ ነገር ይሞታል፡፡»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከሴቶች መኝታ ቤት ነው፡፡ የዚህን ጽሁፍ ይዘት በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያውና ጥሩው ይዘት በጣም ለሚወዱት ጓደኛ ጥሩ መመኘት፣ ስኬቱን የመስማት ጉጉት ይኖራል፡፡ ይሳካለት ይሆን ወይስ አይሳካ ይሆን እያሉ ጥርጣሬ ውስጥ የመግባት ሁኔታ ይታያል፡፡ ነገርግን ስኬቱን ሳይ ያ የጥርጣሬ ስሜቴ ይሞታል፡፡ እፎይታ አገኛለሁ የሚል ይመስላል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ለሚቀኑበት ወይም ለሚመቀኙት ጓደኛ ሁልጊዜ ጥሩ አይመኙለትም፡፡ ውድቀቱን የመስማት ጉጉት አለ፡፡ ውድቀትን የመሻት ስሜት ይኖራል፡፡ ሆኖም ግን የጓደኛዬን ስኬት ሳይ ያ ውድቀቱን የመስማት ተስፋዬ ይሞታል፡፡ ደስታዬ ይጠፋል፤ ይጨልማል፡፡ በውስጤ አንዳች ነገር እንደጐደለ እደነግጣለሁ የሚል ዓይነት መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ በዚህ ጽሁፍም ፀሀፊዋ

በጓደኝነት ውስጥ ሁለት ገፅታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አሳይታበታለች፤ አንድም መተሳሰብ በሌላ ጐኑም መመቀኛኘትና መጐዳዳት።

**ምሳሌ 13**፦ «ዘወትር ራስህን ሆነህ ተገኝ።»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። የግድግዳ ጽሁፉ ይዘት ሰው ሁሉ የራሱ የሆነ አቋም፣ አመለካከት፣ እምነትና የራሱ የሆነ የህይወት መርህ ሊኖረው ይገባል የሚል ነው። አንዳንድ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ መዘውሩ ወዳሽከረከራቸው በቀላሉ ሲዞሩ፣ ወደቀለበሱዋቸው በቀላሉ ሲቀለበሱ ይታያሉ። በመሆኑም ከየትኛውም ጋር ሳይግባቡ ከራሳቸው ጭምር ተጣልተው ይኖራሉ። ፀሀፊው የዚህ ዓይነት ሰዎችን ራሳቸውን ፈልገው እንዲያገኙና ራሳቸውንም ብቻ ሆነው እንዲኖሩ ይመክራል።

**ምሳሌ 14**፦ «አበባ ያለሽታ ውበት ያለቁምነገር ዋጋ የለውም።»

ሌላው ተመሳሳይ ጽሁፍም «ውበት ያለ ፀባይ ስኳር ውስጥ ያለ መርዝ» የሚል ነው። እነዚህ የይዘት ተመሳሳይነት የሚታዩባቸው የግድግዳ ጽሁፎች የተገኙት ከተለያዩ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ነው። የጽሁፎቹ ይዘት የሚያመለክተው ውበት ያለው ሰው ፀባይና ቁምነገር ከሌለው ውበቱን በአግባቡ ሳይዘው ይረግፋል፤ ዕድሜ አይኖረውም የሚል ነው። ጥሩ መዓዛ ያለው አበባ ይቀሰማል፤ ውጤትም ይገኝበታል። መድሀኒትነት ያለው ማር ይሠራበታል። ማሩም ጥቅም ላይ ይውላል። ውበት ያለው ሰውም እንደዛው ፀባይና ቁምነገር ካከለበት ውበቱ ከራሱ ጋር ይቆያል፤ ይጠበቃል፤ ለሌላውም የደስታ ምንጭ ይሆናል የሚል ነው። በዚህ ጽሁፉም ጥሩ ስነምግባር መያዝና ቁምነገር መስራት አስፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን አስተምሮበታል።

**ምሳሌ 15**፦ «እንዴት እንደምታነበው ከተረዳህ ሰው ሁሉ መጽሀፍ ነው።»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። የዚህ ጽሁፍ ይዘት ሰው ሁሉ ይነስም ይብዛ የራሱ የሆነ ታሪክ አለው። ይህ ታሪክ ደግሞ ሊገለፅ የሚችለው ዝም ብሎ ሳይሆን ዘዴውን ካወቅህና ከተረዳህ ብቻ ነው የሚል ነው። ይህም የሰው ልጅ በባህሪው ግልፅነትም ድብቅነትም ይታይበታል። የሰው ልጅ ሊነግርህ የሚችለው ምናልባትም ግማሹን ወይም ጥሩ ነው ብሎ የሚያስበውን ታሪክ ብቻ ሊሆን ይችላል። ነገርግን በተዘዋዋሪ መንገድ አውቆም ይሁን ሳያውቅ ማንነቱን የሚገልፅባቸው መንገዶች ይኖራሉ። ያንን መንገድ አውቀህ ከተከተልክ የመፅሀፍ ያህል ታሪክ፣ መጽሀፍ የያዘውን ያህል የህይወት ልምድ ምናልባትም የበለጠ እውነትና ህይወት ልታገኝበት የምትችልበት እምቅ ሚስጥራዊ ፍጡር ነው የሚል ይመስላል። ስለዚህም የሰው ስሜቱን፣ አመለካከቱን፣ አስተሳሰቡን፣ እምነቱንና ፍላጐቱን ለመረዳት ዘዴ ይኑርህ የሚል ምክር አዘል መልዕክት ተላልፎበታል። እግረ መንገዱንም መፃህፍት ተጨልፎ የማያልቅ የእውቀት ሀብት ምንጮች መሆናቸውን ሲያስገነዝብም እንደመፃህፍት ሁሉ ከሰው ልጆች



UNIVERSITY ILS LIBRARY

የህይወት ልምድም እውቀት መጨለፍ የሚቻለው ውስጡን የማንበብ ዘዴን ስንረዳ ነው ይለናል። ይህንኑ ሀሳብ ለማጠናከርም «መጽሀፍት የመንፈስ ምግብ ናቸው።» የሚለውን አባባል ማስተወስ መፃህፍት የብዙ እውቀቶች መገኛነታቸውን ያስረዳናል።

<u>ምሳሌ 16</u>፡- «ህይወት ጣፋጭ ናት ብለህ አትዋጣት መራራ ናት ብለህም አትትፋት።»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ነው። የጽሁፉ ይዘትም ህይወት ደስታና መከራ የሚፈራረቁባት ናትና እንደ አመጣጧ ተቀበላት። በጣፋጭነቱ ጊዜም ትንሽ ደስታ የሚያስፈነድቅህ፣ በመከራ ጊዜም ቶሎ የምትሸበር መሆን የለብህም። መንፈስ ጠንካራ መሆንና ችግርንም ሆነ ደስታን እንደ አመጣጡ መቀበል መቻል ይኖርብሀል በማለት ምክር አዘልና አስተማሪ መልዕክት አስተላልፎበታል።

<u>ምሳሌ 17</u>፡- «ሰው ሆይ ማህበራዊ ኑሮን መልመድ ሞኝነት አይደለም። /ቀብራራው ዶርም/»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከወንዶች መኝታ ቤት ነው። የጽሁፉ ይዘት እንደሚጠቁመው የተቋሙ መኝታ ቤት ውስጥ ከተለያየ ቦታ፣ በተለያየ አስተዳዳግ፣ በተለያየ የህይወት ልምድ፣ በተለያየ የኑሮ ደረጃ ውስጥ አልፈው የሚመጡ ተማሪዎች በአንድነት ይኖራሉ። በመሆኑም ይህን ሁሉ ልዩነቶቻቸውን አቻችለው በጤናማ ግንኙነት ጤናማ የአኗኗር ስልት ለመከተል አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ፀሀፊው አስቀድሞ ተረድቷል። ለዚህም ይመስላል በተማፅኖ ዓይነት እባካችሁ ማህበራዊ ኑሮን እንልመድ። ማህበራዊ ኑሮን ማወቅም ብልህነት ነው በማለት ምክር አዘል አስተያየቱን ያስፈረው። በዚህ ጽሁፉ ትምህርት ቤት የማህበራዊ አኗኗር ልምድ መቅሰሚያና የተግባራዊ ልምምዱ መጀመሪያ ቦታ መሆኑን ጭምር አሳይቶበታል፤ አስተምሮበታል።

### ለ. እምነት ተኮር ጽሁፎች

<u>ምሳሌ 1</u>፡- «ሁሉንም የምታውቅ ጌታ ሁሉን ታውቃለህ።»

መላሽ፡- «የሚሰማህ መኖሩን እርግጠኛ ሳትሆን አትፀልይ!» የሚል ምላሽ አስፍሯል።

እነዚህ በምልልስ መልክ የቀረቡ የግድግዳ ጽሁፎች የተገኙት ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። የጽሁፎቹ ይዘት ተቃራኒ አስተሳሰቦችን ከሚከተሉ ሁለት ሰዎች የመነጨ ነው። የመጀመሪያው ፀሀፊ አተያይ በዓለም ላይ ላሉ ነገሮችና ሁነቶች ክስተትና ኑረት ለአጠቃላዩ የዓለም ጣጣ ሁሉ መለኮታዊ ሀይል ያለው ጌታ ነው አዋቂው፤ ስለዚህ ሁሉንም ነገር ለእሱ ትቼአለሁ የሚል ይመስላል። በዚህም ጽሁፉ በአምላኩ መተማመኑን ገልጿል። መላሽ ደግሞ በተቃራኒው በአካል ለማታየው መኖሩን ጨብጠህ፣ ዳሰህ ወይም አይተህ ያላረጋገጥከው የሚሰማህ አካል በሌለበት ሆኔታ መፀለይ የለብህም የሚል ማቴሪያሊስት

አመለካከት የሚያንፀባርቅ ምላሽ በመስጠት በአምላክ መኖር ጥርጣሬ እንዳለው የገለፀበት ነው። ሁለቱም ፀሃፊዎች የየራሳቸውን ደጋፊ የሚሹ ሆነው በየአእምሮአቸው የሰረፀውን ሃሳብ አሳይተውበታል።

**ምሳሌ 2፡-** «እየሱስ አዳኝ ነው» ሲል የመጀመሪያው ፀሀፊ መላሽ «ነገር ግን አንተን አያድንህም! እናቱን ክደሀታልና!» በሚል ምላሹን የሰጠበት የግድግዳ ጽሑፍ የተገኘው በወንዶች መኝታ ቤት ነው። የጽሁፉ ይዘት ሀይማኖታዊ ሆኖ የሁለት ሀይማኖት ተከታዮችን የሀሳብ ተቃርኖ የሚያሳይ ነው። የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዩና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዩ ሁለቱም በእየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ሀይልና አዳኝነት ያምናሉ። ሆኖም ግን የማይግባቡበት ነጥብ በአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ላይ ያላቸው የእምነት ልዩነት በመሆኑ ይህንኑ ልዩነታቸውን የሚያንፀባርቅ አስተያየታቸውን በግድግዳዎቹ ላይ መግለፃቸውን እናያለን።

<u>**ምሳሌ 3**</u>፡- «መኖርም ሆነ አለመኖር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው።»

መላሽ፡- «Trust Allah Believe.» ይላል።

እነዚህ የግድግዳ ድሁፎች የተገኙት ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። የጽሁፉ ይዘት የመጀመሪያው ፀሀፊ ኑሮ የመረረው መቋቋም ያቃተው ይመስላል። ስለዚህም መኖርም ሆነ አለመኖር ተመሳሳይና ሁለት ገፅታ ያላቸው ናቸው። መኖርም ሆነ አለመኖር ትርጉም አልሰጥ ያሉት መሆናቸውን ይገልፃል። ሁለተኛው ፀሀፊ ደግሞ በምላሹ በማፅናናትና በእምነቱም ሁሉን ነገር ለአላህ መስጠት እንዳለበት ሲገልፅ አላህን እመን፤ ሁሉንም ለአላህ አደራ ስጥ በማለት የእምነቱን ፅናት በአላህ መተማመኑን ገልፆበታል።

<u>ምሳሌ 4፡-</u> «ኢየሱስ ጌታ ነው፤ ፍቅር ያስታግሳል»

ይህ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ነው። የጽሁፉ ይዘት እየሱስ ማንኛውንም ነገር ማድረግ ስለማይሳነው በጣም ረቂቅ የሆነውንም ፍቅር እንኳን ቢሆን በሀያል ሀይሉ ሊያስታግስ፣ በውስጣችን ሊያዳፍን መቻሉን ያሳየበት ነው። በዚህም ፀሀፊው የዕምነቱን ፅናትና ጥንካሬ ለሌሎች ለማጋባት፣ ስሜቱን ለማስተላለፍ ወይም ተንፍሶ እፎይታን ለማግኘት የተጠቀመበት መሆኑን ማየት ይቻላል። በሌላ መልኩም የትምህርት ስራ የተረጋጋ አዕምሮና ሰፊ ጊዜ ይፈልጋል። ፍቅርም ሰፊ የሆነ የራሱ ጊዜ ይፈልጋል። ስለዚህም ሁለቱን ነገሮች አንድ ላይ ማከናወን ቢቻልም እንኳን የትምህርት ጊዜን ሊሻማና በውጤት ላይ ጫና ሊያሳድር በመቻሉ ምናልባትም ፀሀፊው ሀይለኛ ፍቅር ገጥሞት የነበረና ጊዜዬንም ይሻማል የሚል ሁለት አስጨናቂ ሁኔታዎች ውስጥ የገባበት ሁኔታ መኖሩን ያመላክታል። ለዚህም ይመስላል «ፍቅር ያስታግሳል» የሚለውን በመጠቀም አምላክ እንድታገስ አድርገኝልና ምስጋና ይድረሰው ዓይነት ማወደሻ ጽሁፉን ያሰፈረው።

## 2.4. ፖለቲካ ነክ ጽሁፎች

ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚገልፁትን የግድግዳ ጽሁፍ ክፍሎች ከማየታችን በፊት ፖለቲካ ምንድነው? የሚለውን ስናይ ማርክሳዊ ሌኒናዊ መዝገበ ቃላት ፖለቲካን በሚከተለው ሁኔታ ይተነትነዋል።

> ፖለቲካ- «ፖሊቲ» ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን የጥንታዊት ግሪክ ትናንሽ መንግስታዊ ተቋሞች መጠሪያ ነበር። ፖለቲካ የህብረተሰብ አደረጃጀትን፣ የመንግስት ይዘትን፣ ዓይነትን፣ ቅርፅንና ተግባርን፣ መደቦችና የህብረተሰቡ ክፍሎች መሠረታዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የሚያደርጉትን ትግል፣ በመንግስታት መካከል የሚፈጥሩትን ግንኙነት ማለትም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲንም በሚመለከት የተወሰነ መደብ የሚኖረውን ንድፈ ሃሳባዊ ግንዛቤና እንቅስቃሴ ያጠቃልላል።[16] (1978፣508)

የሰው ልጅ አውቆም ይሁን ሳያውቅ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና የፖለቲካ መርሆዎችን ወይም ህጎችን ሲጥስ፣ ሲያበላሽ፣ ሲያዛባ ወይም በአላስፈላጊ መንገድ ሲተረጉም ወይም ሲተገብር ይታያል። በየጊዜው በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ የሚታዘባቸውን፣ የአፈፃፀም እንከኖችን፣ የአደረጃጀት መርሆዎችና የየድርጅቶችን የስራ አካሄዶችን፣ የመንግስታትን ጥንካሬ፣ ድክመት፣ እርምት የሚያሻውን ጉዳይና ሊበረታታ የሚገባውን አሠራር በመደገፍ፣ በመተቸት፣ በመቃወም አስተያየቶቹን ሁሉ በፖለቲካ የግድግዳ ጽሁፉ ሲገልፅ ኖሯል፤ አሁንና ወደፊትም ሲገልፅ ይኖራል።

**ምሳሌ 1፡-** «የአቶዎች ዘመን ይብቃ በዶክተሮች እንመራ!»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። የጽሁፉ ይዘት ያወቀ፣ የተማረ፣ የሰለጠነ ሰው ይምራን፤ ዕውቀት ያለውና ባለሙያ ቢያንስ ቢያንስ በአንድ ነገር ላይ ከፍተኛ ክህሎት ያገኘ በመሆኑ ፖለቲካውን ቢመራ የተሻለ ልማት፣ የተሻለ ሃገራዊ ዕድገት ሊያስገኝ ይችላል የሚል ዓይነት ስሜት የሚያንፀባርቅ ጽሁፍ ነው።

<u>ምሳሌ 2</u>፡- «የዘንድሮ ምርቃት ስልስት ነው»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። የጽሁፉ ይዘት እንደሚገልፀው የምርጫ 97 ውጤት አስመልክቶ በተቃዋሚ ድርጅቶችና በገዥው ፓርቲ መካከል ተከስቶ የነበረው አለመግባባት፣ የምርጫ ውጤት ላይ በነበረ ቅሬታ መነሻነት ተማሪዎች በየተቋማቱና በየትምህርት ቤቱ ያነሷቸው ተቃውሞዎች የነበሩ ሲሆን ተማሪዎቹ ይወስዷቸው በነበሩት ገንቢ ያልሆኑ እርምጃዎች መነሻነት ከፖሊስ ሃይል ጋር ግጭቶች ተፈጥረው እንደነበሩ ይታወሳል። በዛ ክስተት የታሰሩና የተጎዱ ተማሪዎች

ስለነበሩ ይመስላል ፀሃፊው ምርቃታቸው የደስታ ሳይሆን የሃዘን ድባብ ያጠላበት መሆኑን የገለፀው::

**ምሳሌ 3**፡- «ቅንጅት ያሸንፋል! እንደ አርሴናል ያለጦር መሣሪያ»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: የጽሁፉ ይዘት የሚያተኩረው በምርጫ 97 ቀርቦ በነበረው የተቃዋሚ ፓርቲ ላይ ባለው የድጋፍ ሀሳብ ላይ ነው:: ፓርቲው ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ ያልታጠቀ ነው፤ የትጥቅ ትግልም ሳያደርግ በፖለቲካው ጨዋታ አሸናፊ ይሆናል በማለት በጎ ምኞቱን የገለፀበት አስተያየት ነው:: ይህንንም ሲያብራራ በአውሮፓ ከሚገኝ አንድ ትልቅ ምርጥ ቡድን ጋር «እንደ» በሚለው የማወዳደሪያና ማነፃፀሪያ ቃል በመጠቀም ከፍተኛ የድጋፍ ስሜቱንና ሙገሳውን የገለፀበት የግድግዳ ጽሁፍ ነው::

**ምሳሌ 4**፡- «ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያሸንፋል!

- የእኩልነት
- የእውነት
- የሰላም

አባ ነው::

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: የጽሁፉ ይዘት አባ አስተማሪ አባት ነው፤ አባ ሰባኪ አባት ነው፤ የተጠቀሱትን ሶስት ነገሮች በስራ የተረጎመና ያስተማረ ነው:: ስለዚህም ፀሀፊው ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያሸንፋል የሚል ፅኑ ምኞቱን ያንፀባረቀበት ነው:: በዚህም ለገኘው ፓርቲ ያለውን የድጋፍ ስሜት የገለፀበት የግድግዳ ጽሁፍ መሆኑን ማየት ይቻላል:: ድጋፍ የተገለፀበት ሁኔታም እንደሚታወቀው ገዥው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫ 97 ዓ.ም ከፍተኛ ፉክክር ባደረጉበት የምርጫ ዘመቻ ጊዜ ነው::

**ምሳሌ 5**፡- «ቅንጅት ለአንድ ዘር ለዲሞክራሲ»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: የዚህን ጽሁፍ ይዘት በሁለት መልክ ማየት ይቻላል:: አንደኛው ሀሳብ ድርጅቱ የቆመው ወይም የሚወክለው አንድ ዘርን ብቻ ነው፤ የቆመውም ለዚሁ ዘር ጥቅምና ዲሞክራሲ ነው የሚል የተቃውሞ ሀሳብን ያዘለ እንደሆነ እንገነዘባለን:: ነገር ግን ያ የተጠቀሰ ዘር የትኛው እንደሆነ አይገልፅም:: በሌላ በኩልም ለጋራ አንድነትና ለዲሞክራሲ የቆመ ነው ሁሉም በጋራ ለዲሞክራሲ የሚቆምበትን ሁኔታ ለመፍጠር የቆመ ድርጅት መሆኑን ለመግለፅ የተጠቀመበት ይመስላል:: በዚህም ለድርጅቱ ያለውን ድጋፍ አሳይቷል::

**ምሳሌ 6:-** «ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ማለት ነፍስ ነው:: እሱ ባይኖር ማንም በሰላም አይኖርም!!»

በምላሹ ከስሩ ደግሞ:- «የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ደጋፊ የሆናችሁ ወዮላችሁ!

ዛሬ የተደሰታችሁ አንድ ቀን ታዝናላችሁ!» የሚል ይገኝበታል::

ይህ በምልልስ መልክ የቀረበ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከቤተመፃህፍት ነው የጽሁፉ ይዘትም ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሰላም ምሳሌ ነው፤ ሰላም ህይወት ነው:: ህይወታችን እንዲኖር ደግሞ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መኖር ወሳኝ ነው:: ያለሱ ሰላም አይታሰብም የሚል የድጋፍ ሀሳብ ያለው የግድግዳ ፀሀፊ ያስፈረው ጽሁፍ ነው:: መላሹም ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን የምትደግፉና የምታበረታቱ ሁሉ አሁን ብትደሰቱም ደስታችሁ ዘለቄታ የሌለው ጊዜያዊ ነው:: በኋላ የምታዝኑበት ቀን ይመጣል፤ ብሎ ተቃውሞውንና ተስፋውን የሚገልፅ ስሜት ያለው ፅሁፍ አስፍሯል:: ነገር ግን የተቃውሞውን ምክንያት ግልፅ አላደረገም:: ከዚህ ፅሁፍ የምንረዳው ጥበቡ የተለያዩ ሀሳቦችና መልዕክቶች መለዋወጫ፣ ግድግዳውም ምላሽ የሚሰጣጡበት መድረክ ዓይነት መሆኑን ነው::

**ምሳሌ 7:-** «NO PEACE WITHOUT CUD!»

መላሽ ደግሞ « CUD ለዘላለም ይኑር!::» ይላል::

ይህ በምልልስ ወይም በቅብብል የቀረበ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በቤተመጻህፍትና በክፍል ውስጥም በተደጋጋሚ ተፅፎ ነው:: የጽሁፉ ይዘትም ፀሀፊዎቹ ለድርጅቱ ያላቸውን ድጋፍ የገለፁበት ነው:: አንዱ ያለዚህ ድርጅት ሰላም አይኖርም፤ እሱ ከሌለ ሰላም አይታሰብም የሚል የድጋፍ ሀሳብን ሲገልፅበት ሌላውም ድርጅቱ ለዘላለም ይኑር የሚል መልካም ምኞቱን የገለፀበት ሆኖ እናገኘዋለን::

**ምሳሌ 8:-** «ቅንጅት ለእድገትና ለሰላም»

መላሽ «አዎ ቅንጅት የወጣቱ ተስፋ ነው!» ይላል::

ይህ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: የዚህ ጽሁፍ ይዘት የሚያመለክተው ቅንጅት የተባለው ተቃዋሚ ፓርቲ በምርጫ 97 የምርጫ ቅስቀሳ ባደረገበት ወቅት ከቀረበው የድርጅቱ ዓላማና ፕሮግራም በመነሳት ይመስላል፤ የድርጅቱ ደጋፊዎች ድርጅቱ የሚንቀሳቀሰው ለእድገትና ለሰላም ነው፤ በፕሮግራማቸው ለወጣቱ ብሩህ የሕይወት ተስፋ የሚሰጥ ነገር ይዘው ቀርበዋልና ድጋፋችን ለእነሱ ይሁን የሚል ዓይነት መልዕክት ያስተላለፉበት ነው::

**ምሳሌ 9:-** «እናውቃለን ግን ብንናገር እናልቃለን!»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: የጽሁፉ ይዘት እንደሚያመለክተው ፀሀፊው የተወሰኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች ለመናገር የሚፈልጉት ነገር

እንዳለ ነገር ግን በሚናገሩት ነገር መነሻነት ግን ክፉ ነገር እንደሚደርስባቸው መገመታቸውን ይገልፃል:: ከዚህ ጽሁፍ የምንረዳው ነገር መናገር እየፈለጉ መናገር ያልቻሉ ሰዎች መኖራቸውን፣ የመናገር ነፃነታቸውን የነፈጋቸው አካል እንዳለ ለመጠቆም የፈለጉ መሆናቸውን ነው:: ፀሀፊዎቹ መናገር እየፈለጉ የፈሩት ነገር እንዳለና ከዚህም የጭንቀት ስሜታቸው ጊዜያዊ እፎይታ ለማግኘት የፃፉት እንደሚመስል ለመረዳት አያዳግትም::

# ምዕራፍ ሶስት

## የግድግዳ ጽሁፎቹ አቀራረብ ዘዴ ትንተና

በዚህ ጥናት ውስጥ የግድግዳ ጽሁፎቹ አቀራረብ ዘዴዎች በአራት አበይት ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው:: እነሱም በምልልስ መልክ የቀረቡ፣ በመፈክር መልክ የቀረቡ፣ በማስታወቂያ መልክ የቀረቡና በግጥም መልክ የቀረቡ ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በስዕል መልክም ቀርበዋል:: ማንኛውንም መልዕክት በትክክል ለማስተላለፍ ወይም ለማቀበል የአቀራረብ ዘዴን በትክክል መምረጥ ክዋኔውንና አረዳድን የተቃና ያደርጋል:: ጽሁፉ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ሲናገር የፈለገውን ጉዳይ ለአንባቢው በተለያየ የአገላለፅ ስልት አማካይነት በመፈንተው የጋራ መግባባትን ይፈጥራል::

### 3.1 በምልልስ መልክ የቀረቡ

የምልልስ ዘዴ የፀሃፊውን ግላዊ ስሜት፣ ስነልቦናዊ መልክና አስተሳሰቡን፣ በነገሮች ላይ ያለውን ግላዊ አቋምና ለነገሮች የሚሰጠውን ግምት የማሳየት አቅም ያለው የአቀራረብ ዘዴ ነው:: የግድግዳ ላይ ጽሁፉን ባለቤት ስብዕናና ማንነትም ይገልፃል:: በዚህ በግድግዳ ጽሁፍ ጥበብ የሚታደሙት የሀሳብ ተለዋዋጮችም ሳይተያዩ ወይም ሳይገናኙ በድብቅ የየራሳቸውን አመለካከት በማንፀባረቅ ሲጠይቁ፣ ሲቃወሙ፣ ሲደግፉ፣ ሲነቅፉና ሲያመሰግኑ ይስተዋልበታል:: በእርግጥ በግድግዳ ጽሁፍ እውናዊ ምልልሱ በአካል ተቀራርቦ የሚካሄድ ስላልሆነ አንሰማውም፤ ነገር ግን እናነበዋለን:: ነፃ የሀሳብ መለዋወጫ መድረኩም ግድግዳውና መሰል መፃፊያ ቦታዎች ናቸው:: በዚህ መልክ ከቀረቡት የግድግዳ ጽሁፎች ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት::

<u>ምሳሌ 1፦</u> «ሰው ሽንት ቤት ከተቀመጠ በኋላ ዞር ብሎ ያያል ለምን
ይመስልሀል?»

መላሽ፦ «ሰው በወለደው ስለማይጨክን ነው::»

ሌላ ቦታ፦ «የወላድ አንጀት ሆኖበት ነው የራስ አካል አይደል::»

ይህ በምልልስ መልክ የቀረበ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከወንዶች መፀዳጃ ቤት ነው:: የዚህ ጽሁፍ ይዘት የሰው ልጅ መፀዳጃ ቤት ተቀምጦ ሲያበቃ አይነምድሩን ያያል፤ ያን የሚያደርገው እንደወለደው ልጅ ስለሚያየው ነው የሚል ፌዛዊ አባባል ነው:: ቆሻሻውን እንኳን ሲያስወግድ እየተጠራጠረ ነው የሚል ዓይነት ሀሳብ የሚያንፀባርቅ ፈገግታ ወይም (Fun) ደስታ መፍጠሪያ ጽሁፍ ሆኖ እናገኘዋለን::

<u>ምሳሌ 2፦</u> «በመኪና አደጋ የተለየችኝን ጓደኛዬን የምትመስል አየሁ፤ እዚህ ግቢ.
አየሁ! ምን ልበላት»

መላሽ፦ ከሲኦል እንዴት እንደመጣች ወይም እንዳመለጠች ጠይቃት!»

ሌላው መላሽ፦ «ሁለተኛ ዞር ላንተ እንዳይደርስ ሽሻት!»

ይህ በምልልስ የቀረበ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከትልቁ ቤተ መፃህፍት ነው:: የጽሁፉ ይዘት እንደሚያመለክተው ፀሀፊው በድንገተኛ አደጋ የተለየችውን ሴት የምትመስል ሰው ማየቱን ገልጿል:: ፅሁፉን ስናጤነው «. . . . አየሁ፤ እዚህ ግቢ አየሁ!» የሚለው የአረፍት ነገር ድግግሞሽ የአድናቆቱንና የመደንገጡን ሁኔታ አፅንኦት ለመስጠት የተጠቀመበትና በእውነተኛ ስሜት የፃፈው ያስመስለዋል:: በሌላ በኩልም በሹፈት ሀሳቡን ገልፆ ሌሎች በሚሰጡት ምላሽ ለመደሰት በማሰብ የፃፈውም ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል:: ይሁን እንጂ መላሾቹ በማሾፍና በመሳለቅ ዓይነት አሉታዊ ምላሽ ሰጥተውት እናያለን:: የሁለቱንም መላሾች አስተያየት በሁለት መልኩ ማየት ይቻላል:: እነዚህ መላሾች አንድም ስለ እውነተኛ ፍቅር ያላቸው ግምት አናሳ መሆኑን ያሳያሉ:: ያፈቀሩትን ማጣት ምን ያህል ከባድ፣ ትዝታውን ወይ ትውስታውን ከአዕምሮ ለማጥፋት በቀላሉ የማይቻል መሆኑን አለመረዳታቸውን ያሳያል:: በሌላ መልኩም ወንዶች በሴቶች ላይ ያላቸውን ንቀት፣ ዝቅተኛ አመለካከትና ጥላቻን የሚገልፅ ነው:: ይኸውም ወንዶች አብዛኛ ውን ጊዜ ልጃገረዶችን እንደ አሳሳች፣ ወንዱን ወደ መጥፎና የተሳሳተ የሕይወት አቅጣጫ መሪ፣ እንደ አጥፊና እንደርካሽ ዕቃ አድርገው የመመልከት ባህሪያቸውን ያሳያል:: ለዚህም ነው እንደ ጥፋተኛና አጥፊ «ከሲኦል እንዴት እንደመጣች ወይም እንዳመለጠች ጠይቃት!» የሚል ምላሽ ሰጥቶ የምናየው:: እንደሚታወቀው ሲኦል የሃጢያተኞችና በምድር ኑሮዋቸው ጥሩ ያልሆኑ ሰዎች መከማቻ ነው:: የመጀመሪያው መላሽ ሴቲቱ እዚያ ቦታ ውስጥ እንደነበረች በእርግጠኝነት ለመናገር ደፍሯል:: ሌላውም ከዛው ያልተሻለ ሀሳቡን «አጥፊህ ናትና ሸሻት!» በሚል ዓይነት ነው አስፍሮ የምናየው:: በዚህም መላሾቹ ሚዛናዊነት የጎደለው፣ ጤናማ ያልሆነ አመለካከታቸውን በማሾፍና በመሳለቅ ገልፀዋል::

<u>ምሳሌ 3</u>፡- «እንግሊዝኛ እንዴት ቢጠና ይገባል ፈቃደኛ ተባበር ምክርህን/ሽን/?»
መላሽ፡- «ችከላ + ውይይት ( 1 X 2/ day)»

ይህ ጽሁፍ የተገኘው ከትልቁ ቤተመጻህፍት ነው:: ፀሀፊው ወይም ፀሀፊዋ እንግሊዝኛ ትምህርት የከበደው/ዳት እና የማጥናት ዘዴው እንዴት ቢሆን ይገባኛል የሚል ምክር ጠያቂ ወይም ጋባዥ ሆኖ የጭንቀት ስሜት የተንፀባረቀበት ነው:: መላሽ ደግሞ እጥር ምጥን ያለ ምላሽ የሰጠበት/ችበት ነው:: ችከላ በተማሪው መግባቢያ ቋንቋ ጥልቅ ንባብ ወይም ጥናት ሲሆን ውይይት ወይም መነጋገር ከጓደኛና መሰል ተማሪ ጋር እንደሚያስፈልግ ዘዴውም በቀን ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ መሆን እንዳለበት ምክራቸውን ያካፈሉበት ምላሽ ሆኖ እናገኘዋለን::

<u>ምሳሌ 4</u>፡- «ከቅንጅት ጋር እስክመጨረሻው እንቆማለን!»
መላሽ፡- «ጊዜ ይፈጃል እንጂ አህያም የጅብ ናት::»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በተለምዶ ልዩ ስሙ «ቀዝቃዛው ክፍል» ወይም «Cold room» የሚባለው የተማሪዎች የማጥኛ ክፍል ውስጥ ነው:: የጽሁፉ ይዘት ከተጠቀሰው የፖለቲካ ድርጅት ጋር እስከ መጨረሻው ድረስ አንድነታችንን እንገልፃለን:: ከዓላማው ጋር አብረን እንጓዛለን የሚል የድጋፍ ሀሳቡ ፅኑና የማያወላውል መሆኑን ለመግለፅ የተጠቀመበት ነው:: መላሹም በተቃራኒው የሀሳቡ ተቃዋሚ ወይም የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ደጋፊነቱን የሚገልፅ ምላሽ የሰጠበት ነው:: ትግሉ ረጅም ጊዜ ይፈጅ ይሆናል እንጂ ቅንጅት በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ይዋጣል ወይም ይበላል ማለትም ይመታል የሚል ዓይነት መልዕክት ተላልፎበታል:: በዚህም መላሹ ለኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ማሸነፍ ያለውን ተስፋ የገለፀበትና ይህንኑ እምነቱን በእርግጠኝነት ስሜት የተናገረበት መሆኑን እናያለን::

**ምሳሌ 5፡-** «ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ» <«ቅንጅት»

መላሽ፡- «ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የምላስ ብስለት ቅንጅት የህሊና!»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው አሮጌው ህንፃ አካባቢ ካለ ሽንት ቤት ነው:: ይህ ጽሁፍ ሁለቱን የፖለቲካ ድርጅቶች በማወዳደር የተገለፀ ነው:: የግድግዳ ፀሃፊዎቹ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የተባለው ፓርቲ ደጋፊዎች ይመስላሉ:: ሌላውም መላሽ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ብስለት በቃላት ንግግር ላይ ብቻ ነው ይለናል:: በአንፃሩ ደግሞ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የአዕምሮ ብስለት ባለቤት እንደሆነ ገልጿል:: ሁለቱም ሀሳቦች ቅንጅትን በመደገፍ የቀረቡ ናቸው:: ይህ የግድግዳ ጽሁፍ ለምርጫ 97 ዝግጅት የፖለቲካ ድርጅቶች ፕሮግራማቸውን በመግለፅና በማስተዋወቅ ከፍተኛ የሚዲያ ሽፋን ባገኙበት ወቅት ይሰጧቸው ከነበሩት መግለጫዎች በኋላ የተፃፈ ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ይቻላል::

**ምሳሌ 6፡-** "I Love HIV B/c..... "

መላሽ፡- «You can I think you are carrier»

ሌላው፡- «ይህን የፃፈውን አድናቂው ነኝ!»

ይህኛው የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው መማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: ፀሀፊው ለፌዝ ያቀረበው ይመስላል:: «HIV» ቫይረስ በጣም ጎጂና ገዳይ የሆነ መሆኑ እየታወቀ አፈቅረዋለሁ ሊባል የሚችል ነገር ያለመሆኑ ጉዳይ ግርምታን ያጫረበት መላሽ በተራው ትችላለህ፤ እንደውም ቫይረሱን ያፈቀርክበት ምክንያት አንተ የቫይረሱ ሰለባ/ተጠቂ/ ስለሆንክ ይሆናል፤ እንደማስበው ሰለባ ነህ ፤ በማለት አባባሉን ነቅፎ ምላሹን ሰጥቷል:: ሌላውም «አድናቂህ ነኝ» በማለት የሹፈት መልሱን ሰጥቶ እናያለን:: በእርግጥ የሁለተኛ ውን መላሽ አስተያየት ከሁለት አቅጣጫ ማየት ይቻላል:: በአዎንታዊ ጎኑ የመጀመሪያውን ፀሀፊ ጥንካሬውንና ተስፋውን በማድነቅ የሰነዘረው አስተያየት ሊሆን ይችላል:: በአሉታዊ ጎኑ «አድናቂህ ነኝ» ብሎ ያቀረበው መልስ እንዴት ታፈቅረዋለህ? ገዳይ ቫይረስ ነው፤

ስለዚህም አንተ ጀብደኛ ነህ የሚል ሹፈት ወይም ፌዝ የተቀላቀለበትና የፀሀፊውን ሞራል የሚሰብር መልስ መሆኑን ማየት ይቻላል:: የመጀመሪያውን ፀሀፊ ሀሳብም በሁለት መልክ ማየት ይቻላል:: በአንድ በኩል ቫይረሱን ያፈቀረበት ምክንያት ቫይረሱ ከያዘም በኋላ ተጠንቅቆ ራስን ከተንከባከቡ positive living ወይም በጤናማ ሁኔታ አብሮ የመኖር ዕድል ስለሚፈጥር ሰዎችን ለህይወታቸው ጥንቁቅ ሊያደርግ መቻሉ ሊሆን ይችላል:: በሌላ አማራጭ ደግሞ ለሕይወታቸው ግምት ለማይሰጡና ራሳቸውን ለማይጠብቁ ሰዎች የአደጋ ምልክት ወይም አደገኛ ሆኖ እስከሞት የሚያደርስ ቫይረስ መሆኑን ለመግለፅና ጥሩ መቀጣጫ ነው ብሉ በማሰቡ ሊሆን ይችላል::

ከዚህ መገንዘብ የምንችለው የመጀመሪያው ፀሀፊ ሰዎች አንጉል ድርጊቶች ወይም ተግባሮችን በግዴለሽነት ሲፈፅሙ በማስተዋሉ ቫይረሱ በከፍተኛ ደረጃ የሰውን ልጅ በመፈታተን አምራች ዜጋ እያሳጣን ባለበት ሰዓት ላይ ሆኖ አንድም ለመምከርና ለማስተማር በሌላ ጎኑ ራሱ የችግሩ ተጎጂ ሆኖ ሳለ ራስን ለማፅናናት የፃፈው ሊሆን መቻሉን ነው:: ከዚህ በተጨማሪም በተማሪው ማህበረሰብ ውስጥም ስለቫይረሱ ያለው ግንዛቤና አመለካከት ሁለት ዓይነት መሆኑን ነው:: ግንዛቤውና አመለካከቱ ትክክለኛውን መስመር የያዘና ግንዛቤውን ከተግባር ጋር ለማቀናጀት የሚሠራው ክፍል እንዳለና የግንዛቤው እጥረት ሳይኖርበት በተግባር ለመለወጥና በስራ ላይ ለማዋል ያልቻለው ክፍል መኖሩን ነው:: ለዚህ ምስክሩ በምልልስ ከፃፏቸው የግድግዳ ጽሁፎች ግዴለሻዊ መላሾች ውስጥ የሚስተዋሉት ስሜት ጎጂና ፌዛዊ መልሶች በኤድስ/ቫይረስ/ መያዝ የህይወት የመጨረሻ ፅንፍ/ጫፍ/ ነው ብሎ የማሰብ አዝማሚያዎች ናቸው::

## 3.2. በመፈክር መልክ የቀረቡ

በመፈክር መልክ ሀሳብን መግለፅ ሀሳቡን ተቀብለን የጋራ እናድርገው የሚል አንድምታ አለው:: መፈክር የሚሹትን ነገር አፅንኦት ሰጥቶ ለመግለፅ የሚያስችል የአፃፃፍ ዘዴ ነው:: መፈክር ሀሳብ ያስለውጣል:: የመፈክሩ ይዘት አፍራሽም ይሁን ገንቢ÷ አጋር ይፈልጋል:: ህብረተሰቡንም የማነቃቃት ሀይልና ችሎታ አለው:: መፈክር ጠንካራ መልዕክት አስተላላፊም ነው:: አንዳንድ ጊዜ የግድግዳ ጽሁፍ ፀሀፊዎች ግድግዳዎችን እንደአስቂኝ የጨዋታ ቅብብል መድረክ ይጠቀሙባቸዋል ለፌዝና ደስታ መፍጠሪያ /Fun/ ግልጋሎት የሚጠቀሙባቸው መፈክር መሳይ ጽሁፎች ይስተዋላሉ:: ከዚህ በመቀጠል በሚቀርቡት ምሳሌዎች በመፈክር መልክ የቀረቡ የግድግዳ ጽሁፎችን እንመልከት::

<u>ምሳሌ 1፡-</u> «ኢትዮጵያ በልጆቿ ተጋድሎ ለዘላለም ትኖራለች!»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: ጽሁፉ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያነቷን ይዛ እንድትቀጥል ልጆቿ ዘወትር ተግተው ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት እንደሚከፍሉ በእርግጠኝነት ይናገራል:: ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያዊነትና

በሀገራቸው ላይ የሚቃጡ ጥቃቶችን በዝምታ የሚመለከት ልብ የሌላቸው ህዝቦች ናቸው:: ደማቸውን በማፍሰስና አጥንታቸውን በመከስከስ መስዋዕትነትን በመክፈልም ኢትዮጵያ ኢትዮጵያነቷ እንደተጠበቀ እንድትኖር ያላሰለሰ ትግል በማድረግም ይታወቃሉ:: በዚያም የተጋድሎ ታሪካቸው የታፈረችና የተከበረች ኢትዮጵያን ለአሁኑ ትውልድ በአኩሪ ሁኔታ አሸጋግረው አልፈዋል:: ይህንኑ ወኔያቸውንና ሀሞተ ኮስታራነታቸውን ያስመሰከሩ ልጆቿ ብዙ ናቸው ይላል:: በዚህም ፀሀፊው ኢትዮጵያ ሀገራችን በልጆቿ ተጋድሎና መስዋዕትነት አሁንም፣ ወደፊትም፣ ለዘላለም እንደምትኖር ያለውን ፅኑ ምኞትና ከፍተኛ ተስፋ በአፅንኦት ገልጿል::

<u>**ምሳሌ 2**</u>:- «LONG LIVE HENRY»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: ጽሁፉ ከእንግሊዝ ፕሪሜየርሊግ ክለቦች ውስጥ አንዱ በሆነው አርሴናል ውስጥ አጥቂና ታዋቂ አንበል የሆነውን «Thierry Henry»ን ለዘላለም ይኑር በሚል መልካም ምኞት፣ ለተጫዋቹ ያለውን አድናቆትና ክብር ለመግለፅ የተጠቀመበት ጽሁፍ ነው:: ፀሀፊው በሱ ልቦና ውስጥ የታተመውን ከፍተኛ ፍቅር ሁሉም ሰው የሱን ያህል እንዲሰማውና ለተጫዋቹ ረጅም ዕድሜን እንዲመኝ ይቀስቅሳል::

<u>**ምሳሌ 3**</u>:- «LONG LIVE CUD»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በቤተመፃሕፍት ውስጥ ነው:: ጽሁፉም ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የተባለው ፓርቲ ለዘላለም ይኑር የሚል መልካም ምኞቱን፣ ለፓርቲው ያለውን አድናቆትና ክብር ለመግለፅ የተጠቀመበት ነው:: ፀሀፊው ለፓርቲው ዘላለማዊነትን ሲመኝ ሌሎችም መፈክሩን እንዲጋሩት ምኞቱ መሆኑንም የገለፀበትና የቀሰቀሰበት ሆኖ እናገኘዋለን::

<u>**ምሳሌ 4**</u>:- «ከቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ጎን እስከ መጨረሻው
እንቆማለን!»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: የጽሁፉ ይዘትም ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የሚባለው ፓርቲ የሚያራምዳቸውን የፖለቲካ ዓላማ የሚደግፍ ነው:: ለፓርቲው ያለን ድጋፍ እስከመጨረሻው ይቀጥላል፤ አጋርነታችን እስከመጨረሻው አይለየውም የሚል ሀሳብ ያስተላልፋል:: ሁሉም ሀሳቡን የጋራ ያደርገው ዘንድም ይቀሰቅሳል::

<u>**ምሳሌ 5**</u>:- «Victory for ቅንጅት»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: ይዘቱ እንደሚጠቁመው በ1997 ዓ.ም ምርጫ ዘመቻ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ ከገዥው ፓርቲ ጋር በመወዳደር ላይ የነበረው የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ መሆኑ ይታወሳል::

ይህ ፓርቲ በተለይም በዚህ በመዲናችን የነበረው የህዝብ ድጋፍ ከፍተኛ የነበረ ሲሆን የዚህ የግድግዳ ፀሁፌም ከደጋፊዎቹ አንዱ መሆኑን ይገልፃል:: በጽሁፉም ፓርቲው እንዲያሸንፍ ከፍተኛ ፍላጎትና ምኞት እንዳለው የገለፀበት ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ፀሀፊው ሀሳቡን ተማሪው የጋራ ያደርገው ዘንድ የቀሰቀሰበት ሆኖ እናገኘዋለን:: የአፃፃፍ ዘዴውም በሁለት ቋንቋዎች የተደራጀ ወይም የተሰደረ ሆኖ እናገኘዋለን::

<u>ምሳሌ 6፡-</u> «የካቲት 16 ደረሰ ሁላችንም ለነፃነት እንታገል::»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው በመማሪያ ክፍል በብዙ ቦታዎች ነው:: የጽሁፉ ይዘት ተማሪው በዚህ በተገለፀው ዕለት የሚጠብቀው አንድ ምላሽ ነበር:: እሱም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ተማሪዎች በየተቋማቸው የመምረጥ መብታቸው የተጠበቀ እንዲሆን በጠየቁትና በታገሉት መሠረት የካቲት 16 ለዘጠኝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምርጫ በየተቋማቸው እንዲፈፅሙ መፈቀዱ የሚያስተዳድሯቸውን ወገኖች ለመምረጥ ዕድል ማግኘታቸው የሚታወቅበት ዕለት ስለነበርና የማይፈልጉትን የፖለቲካ ፓርቲ በድምፃቸው ለመቅጣት የሚያስችላቸውን ዕድል ማግኘታቸውንና ማጣታቸውን የሚያረጋግጡበት ቀን መሆኑን ለመግለፅ ተጠቅመውበታል:: ጉዳዩም የመኖርና ያለመኖር ውሳኔ የሚፈልግ እንደሆነ ተደርጎ በአፅንኦት የተገለፀበት መሆኑን እናያለን::

## 3.3. በማስታወቂያ መልክ የቀረቡ

የማስታወቂያ ጽሁፍ የማግባቢያ ጽሁፍ አካል ነው:: ማግባባት ደግሞ ልዩ ክህሎትን ይጠይቃል:: ይህን የማግባቢያ ጽሁፍ ምንነት እነ ዮናስ አድማሱ (231-234) እንደሚከተለው ገልፀውታል፤

> የማግባቢያ ጽሁፍ መጢቃ ጽሁፍ ነው:: ከመዘርዝራዊና ከኪነታዊ ጽሁፍ ከሁለቱም በቀጥታ ይፈልቃል:: የሚፃፈውም ለማግባባት፣ ዝንባሌ ለማስለወጥ ብሎም ወደ ድርጊት ለመምራት ነው:: ዕውቀትን ወደ ድርጊት የመለወጥ ዝንባሌ አለው:: ስብከት፣ ማስታወቂያ የቃልም ይሁን የጽሁፍ... በረቂቅ ስልት የተፃፈውም ሆነ እንደነገሩ የተጫጫረው የማግባቢያ ጽሁፍ ነው:: የማግባቢያ ጽሁፍ መለያ ጠባዩ ይኳሻል፣ ይሳለቃል፣ አንዳንድ ጊዜ ያጠይማል፣ አንዳንድ ጊዜ አርቆ ያጥራል፣ በጥቂት ፍሬ ነገር ተገንብቶ አንባቢና አድማጩን ለድርጊት ይገፋል::... የድርጊት ምላሹ ወዲያው ሊታይም ላይታይም የሚችልበት ሁኔታ አለ:: ዝምታም አንፃራዊ መገለጫው ሊሆን ይችላል::[17] ...

ይህም ማለት በአጭር መግለጫ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ማስተዋወቅና ጥበባዊ መስህብ ባለው ጽሁፍ ውህድ ውጤት ሊገለፅ የተፈለገውን ነገር አጋኖ፣ በብዕሩ ወይም በድምፁ አቆሽሾ፣ ያልሆነውን ነው ብሎ ወይም አግዝፎ መግለፅ የሚያስችል የጽሁፍ ወይም የቃል አቀራረብ ነው:: በማስታወቂያ መልክ ስለሚቀርቡ ጽሁፎች ይህን ካልኩ እስኪ በዚህ መልክ ከቀረቡት የግድግዳ ጽሁፎች ለአብነት ያህል ጥቂቱን እንመልከት::

**ምሳሌ1**፡- «የረገበ ጡት እንወጥራለን!»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ የጽሁፉ ይዘት ወንዶች ተማሪዎች ሴት ተማሪዎችን ለማብሸቅ፣ ፌዝና ሹፈት ለመሰንዘር የፃፉት ይመስላል፡፡ የልጃገረዶች ጡት በአብዛኛው ቀጥ ያለና የቆመ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ጡታቸው የሚወድቀው ከወለዱና ካጠቡ በኋላ ስለሚሆን አንዳንድ ልጃገረዶች ምንም እንኳን ባይወልዱም በአጋጣሚ ጡታቸው የወደቀ ሆኖ ሊታይ ይችላል፡፡ በዚህም ጊዜ ወንዶቹ እንደ ዕድሜ መለኪያነትና እንደወላድ ምልክት በመቁጠር ሊያሾፍባቸው ይሞክራሉ፡፡ ይህም ጽሁፍ ከዚሁ ሁኔታ የመነጨ ፌዝ አዘል መሆኑን መገመት ይቻላል፡፡

**ምሳሌ 2**፡- «ይህ ቦታ የሚፈቀድለት ለሚቅም ሰው ብቻ ነው!»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከአስተዳደር ቢሮ አካባቢ ከሚገኝ አንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ የጽሁፉ ይዘት እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ፀጥታን በመሻት በየክፍሉ እየገቡ ያጠናሉ፡፡ ይህም የሚሆነው በፈተና መቃረቢያ ወቅት ቤተመጻህፍት ስለሚጨናነቁ ነው፡፡ ይህ ፀሀፊም በዚሁ ሁኔታ ይመስላል ቦታውን ለጥናት የሚመርጠው ሆኖ፤ ነገር ግን ክፍሉ የተከለከለ እንደሆነና በመቃም ተግባር ለሚሳተፍ ሰው ብቻ እንደሆነ ለማስመሰል የተጠቀመበት እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ በተቋሙ ውስጥ መቃም የተከለከለ ነው፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ለደንቡ የማይገዙና ተግባሩን የሚፈፅሙ ሊኖሩ ይችላሉ፤ ቢሆንም ግን ያን ድርጊት የሚፈፅሙ ተማሪዎች እንኳን ቢሆኑ በግልፅ ያን ጽሁፍ አስፍረው ተግባሩን እዚያው ቦታ ለመፈፀም አይደፍሩም፡፡ በሌላ አማራጭ ግን ህገ-ወጥ የሆኑ ተማሪዎች መቃሙን የሚከውኑበት ቦታ ሆኖ ከጫቱ ምርቃና በኋላ ህሊናቸውን በትክክል ማዘዝ ባልቻሉበት ወቅት የፃፉትም ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ከጽሁፉ የምንረዳው አንድም በውሸት ለማስመሰልና ለጥሩ ነገር ጥቅም ለማዋል ወይም ሳያውቁ በድፍረት እውነቱን የገለፁበት መሆኑን እንረዳለን፡፡

**ምሳሌ 3**፡- «መድሀኒት ቀማሚ መስሪያ ቤት ቀብራራው ዶርም»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከወንዶች መኝታ ቤት ነው፡፡ ከጽሁፉ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው በዚያ የመኝታ ክፍል ውስጥ የነበሩ ተማሪዎች በባህሪያቸው አንድ አይነት የነበሩና ሁሉም ጫት የሚቅሙ ነበሩ፡፡ ሁልጊዜ ከራት በኋላ እዛ መኝታ ቤት ጫት ይቃማል፡፡ ታዲያ ለጉዳይ አንዱን ተማሪ ፈልጎ የሄደ ተማሪ አንድ ጉንጭ ጫት ሳይቅም /አፉ ሳያደርግ/ አይወጣም፡፡ በህብረት ሆነው እስኪ ቅመስ እኛ መኝታ ክፍል መጥቶ ሳይቀምስ የሚወጣ የለም ብለው በዚህም በዚያም አድርገው አሳምነው ምንም ጫት ቀምሶ የማያውቀውን ተማሪ በነሱ አጠራር አንድ ወይም ሁለት «ሉሉቀቻ» ያስደርጉታል፡፡ በመሆኑም ልምዱ የሌላቸው ተማሪዎች የተለየ ባህሪ ሲያሳዩ ወይም ራሳቸውን አመመን ሲሉ ይታያል፡፡ በዚህም መድሃኒት ቀማሚ መስሪያ ቤት የሚለው ስያሜ የተሰጣቸው መሆኑን ላረጋግጥ ችያለሁ፡፡ ከዚህም የምንረዳው ለመሳቅና ለማሾፍ

ሲሉ ያን ድርጊት መፈፀማቸውን ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ አንዳንድ ተማሪዎች በዛው ሱስ ተጠምደው የሚቀሩበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡

<u>ምሳሌ 4</u>፡- «ሽክማችሁ የከበደ ሁሉ ሽክማችሁ ይቀል ዘንድ ወደዚህ ኑ»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመፀዳጃ ቤት ነው፡፡ የጽሁፉ ይዘት እንደሚያመለክተው ይህንን ሀይማኖታዊ አባባል እንዳለ ወስዶ ሽንት ቤት ግድግዳ ላይ የፃፈው ለማሳቅ ይመስላል፡፡ በሀይማኖታዊው ጥቅስ «ሽክማችሁ የከበደ» የሚለው ሀረግ ሀጢአታችሁ የከበደ የሚለውን ትርጉም ይይዛል፡፡ በዚህ አውድ ግን «ሽክማችሁ የከበደ» ሲል የመፀዳዳት ፍላጎታችሁ ያደገ ሰዎች ለማለት ይመስላል፡፡ የሚወገደውን ቆሻሻ እንደ ሽክም በመቁጠር ሽክማችሁን ለማቅለል ወደዚህ ኑ ብሎ ሣቅ ለመፍጠር የፃፈው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

<u>ምሳለ 5</u>፡- «የሚከራይም የሚሸጥም ወንድና ሴት የለም፡፡»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው «ቀዝቃዛው ክፍል» «Cold room» ከሚባለው የማጥኛ ክፍል ነው፡፡ ጽሁፉ ለፌዝና ሣቅ ለመፍጠር የተፃፈ ይመስላል፡፡ ሰው ክቡር ፍጡር ነው፡፡ ሊሸጥም ሊከራይም የማይገባው ነው፤ ነገር ግን ይህን ጽሁፍ ፀሀፊው የፃፈበት ምክንያት በዚያ ጥናት ክፍል ውስጥ በጥናት ሰበብ ሴቶችና ወንዶች ተማሪዎች አላስፈላጊ ባህሪያትና ድርጊቶች ሲያሳዩ ስለሚስተዋል ያንኑ ለማመላከትና ለማፌዝ ይመስላል፡፡ ይህን ጽሁፍ ያየ ተማሪ ጠንቀቅ የሚልበት ሁኔታ እንዲፈጠርም ለማስተማርና ለማሳወቅ የተፃፈም ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ አለ፡፡ ከዚህ ላይ የምናስተውለው በእርግጥም ተገቢ ስራ በተገቢው ቦታ ካልተፈፀመ ድርጊቱ ለሽያጭ ከመቅረብ የማይተናነስ መሆኑን ነው፡፡

## 3.4. በግጥም መልክ የቀረቡ

ግጥም ከንግግርና ከፅሁፍ ጥበብ ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ግጥም በቋንቋ አማካይነት የሚበጅ ጥበብ ነው፡፡ ግጥም ቃላዊም ፅሁፋዊም አቀራረብ አለው፡፡ ይህ ጥበብ ለስሜት ቅርብ የሆነ፣ ገጣሚ ተሰምቶት የነበረውን ዓይነት ስሜት ሌሎች እንዲሰማቸውና ሀዘኑን ሀዘን ያደርጉት፣ ደስታውን ይዘምሩት፣ ቁጭቱን ይኖሩት ዘንድ አድማጩን ወይም አንባቢውን ከመቀስቀሱም በላይ የፀሀፊውን ስሜት እንዲጋሩ ዕድል ይሰጣል፡፡ በዜማ መነገሩና መፃፉ እንዲሁም የሙዚቃዊነት ባህሪው የሰው ልጅ ሰብአዊ ስሜቶችን እንዲያሰርፅ ታስቦ የሚበጅ መሆኑ አዕምሯዊ ምስል ከሳች ያደርገዋል፡፡ ስለዚህም ለመግለፅ የሚያስቸግሩ ሁነቶችንና ረቂቅ ስሜቶችን አጉልቶ የሚያሳይ፤ መስሎም የሚያቀርብ ኪናዊ ሀይልና ብቃት ያለው የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ በፅሁፍ ከመጠቀሙ በፊት በስነቃላዊ ግጥሞቹ ሀሳቡንና መልዕክቱን ሲያስተላልፍበት

ቆይቷል:: አሁንም በዘመናዊው የአማርኛ ግጥም ውስጥ ውስብስብ ሀሳቦች፣ ረቂት ስሜቶችና መልዕክቶች የሚተላለፉበት ስልታዊ መግባቢያ ነው::

በመቀጠል የምናያቸው የግድግዳ ጽሁፎች በግጥማዊ ያቀራረብ ዘዴ የቀረቡ ናቸው:: እነሱም:-

<u>ምሳሌ 1:-</u> «ጣውላው ተሰበረ ሳይረገጥ ጎኑ፣
አይዞሽ የናቴ ልጅ ያልፋልና ቀኑ፣
ችግርን መቋቋም እንልመድ ካሁኑ::»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከወንዶች መኝታ ቤት ነው:: ያቀራረብ ዘዴው በተምሳሌታዊ ዘይቤ የቀረበ ነው:: «ጣውላው ተሰበረ» የሚለው ሀረግ ሰውን ወክሎ የተቀመጠ ይመስላል:: በዚህም ገለፃ መሠረት አንድ የተጎዳ ወይም የሞተ ሰው እንደነበርና እንደዚህ ዓይነት ችግሮች ሲያጋጥሙ የሚችሉና የሚያልፉም ናቸውና እንጠንክር የሚል ይመስላል ፀሀፊው:: ፀሀፊው በዚህ የዘይቤ አፃፃፍ ለመፃፍ የመረጠበት ምክንያት በጽሁፉ ይዘት መግለፅ የፈለገውን መልዕክት ማለትም የገጠመውን ችግርና እሱን መሰል እንስትና ተባዕትም የሚደርስባቸውን ችግር በአሸናፊነት ለመውጣት ይችሉ ዘንድ ለማበረታታት ነው:: በስንኞቹም ሀሳቡን አጉልቶ በማሳየት በትዕግስት የችግሩን ማለፍ መጠበቅ እንዳለባቸው ገልጿል::

<u>ምሳሌ 2:-</u> «አንድ ማፍቀር ግድ ነው፣
ሁለት ማፍቀር ንግድ ነው::»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: ይህ በግጥማዊ አቀራረብ ዘዴ የቀረበ ግጥም በተጠቀመው ለዋጭ ዘይቤ አማካይነት የበለጠ ሀሳቡንና መልዕክቱን ለመግለፅ ችሏል:: አንድ ማፍቀር ወይም መውደድ ከሰው ልጅ ሰብአዊ ግዴታዎች ውስጥ ተጠቃሽ ነው:: ይህ ጽሁፍ አንድ ለአንድ ተገቢ መሆኑን አጠንክሮ ማሳያ ነው:: ፀሀፊው ሁለት ማፍቀርና የመውደድን መጥፎነት ለመግለፅ የተጠቀመው «ፍቅር» የሚለውን ቃል «ንግድ» በሚለው ለውጦ በማስገባት ነው:: ፍቅር ንግድ የሚሆንበትን አጋጣሚ ለማሳየት «ንግድ» የሚለው ቃል ከፍቅር ጋር የሚገናኝበትና የሚመሳሰልበት ነገር ባይኖርም ፀሀፊው ሀሳቡን አጉልቶበታል:: ንግድ ትርፍ እንዳለው ሁሉ ኪሳራም አለው:: ስለዚህ ሁለት የማፍቀር ሒደት ኪሳራነቱ የጎላ መሆኑን ለመግለፅ የተጠቀመበት ይመስላል::

<u>ምሳሌ 3:-</u> «ከእንግዲህ ነገሬን ከአፌ አለቅም፣
የሰው ዶሮ አለ ከአፍ የሚለቅም::»

ይህ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው:: ይህ በግጥማዊ አቀራረብ የተፃፈ ጽሁፍ በተለዋጭ ዘይቤ አማካይነት መልዕክቱ በጎላ ሁኔታ ለአንባቢው ደርሷል:: ከዚህ ጽሁፍ ውስጥ ፀሀፊው የዶሮን ባህሪ ለሰው ለውጦ በመስጠት ምስል እንዲታይ አድርጓል:: ይኸውም ወሬን ከአፍ እንደ ዶሮ የሚለቅም ሰው ስላለ ወሬኛውን

እጠነቀቃለሁ፡፡ ስለሆነም በወሬ መነሻ ችግር ውስጥ እንዳትገቡ ተጠንቀቁ የሚል ዓይነት መልዕክት አስተላልፎበታል፡፡

<u>ምሳሌ 4</u>፡- «ምነው ለመቃብር መክፈቻ ቢኖረው፣
ብሶቴን ችግሬን ለአባቴ እንድነግረው፡፡»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ የተገለፀበት ዘይቤ ሰውኛ ነው፡፡ ይኸውም በመቃብር ውስጥ ያለ ግዑዝ አካል የሰው አዕምሮአዊ ችሎታ የሆነውን የማዳመጥ ችሎታውን እንደሚያጣ ዕሙን ነው፡፡ ነገር ግን ፀሀፊው ነጋሪ ሲሆን አድማጩ ግዑዝ አካሉ እንደሚሆን በመገለፁ ህያው የሆነ የሰው ልጅ ባህሪን ለበድን አካል የሰጠና በድኑን አካል እርዳታ በመጠየቅ የደረሰበትን ችግር ያዋየው እንደነበር ገልጿል፡፡ ይህም ጽሁፍ ፀሀፊው ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዳለና ከችግሩ ብዛትም በውስጡ የተሰማውን ነገር ተንፍሶ ጊዜያዊ እፎይታ ለማግኘት የተጠቀመበት ይመስላል፡፡

<u>ምሳሌ 5</u>፡- «የሰው ፀባይ የአየር ፀባይ፣
አሁን ዝናብ አሁን ፀሀይ፡፡»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከሴቶች መኝታ ቤትና በክፍል ውስጥም ተፅፎ ነው፡፡ እነዚህ የግጥም ስንኞች በተለዋጭ ዘይቤ የተገለፁ ናቸው፡፡ የሰው ፀባይ በአየር ንብረት ባህሪ ተለውጧል፡፡ የአየር ንብረት ደግሞ ተለዋዋጭ ክስተት ነው፡፡ በመሆኑም ፀሀፊው የሰው ልጅ ባህሪም እንዲሁ ተለዋዋጭ እንደሆነበትና ሰውም በባህሪው ቋሚና ወጥ ቢሆን የተሻለ እንደሚሆን ለማሳሰብ በኢርቱዕ አገላለፅ የተጠቀመበት ይመስላል፡፡

<u>ምሳሌ 6</u>፡- «አክርማው ባይለዝም፣
ሰበዝ ባንመዝም፣
ወስፌንም ባንይዝም፣
ከማንም ሰፌድ ላይ ቆሎ እየዘገነ፣
ሊበላ ፊቅደናል ዲሞክራት ከሆነ፡፡»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ የተገኘው ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ ይህ ግጥም በአያዎ /paradox/ ዘይቤ የተፃፈ ነው፡፡ ፀሀፊዎቹ በግድግዳ ጽሁፉ ለመግለፅ የፈለጉት ሀሳብ ይዘት እያንዳንዳችን የእንጀራችንን፣ የየበኩላችንን ድርሻ በተገቢው ለማከናወን ወይም ለመፈፀም አልቻልንም፡፡ ሕይወታችንን ወደ እድገትና ወደ ተሻለ ኑሮ የሚያደርሰውን ተግባር የስራ እንቅስቃሴ አናደርግም፡፡ ዳቦ ጠግበን ለመብላት የሚያስችለንን ሁኔታ ስራን ማዕከል ያደረገ ተግባር አንፈፅምም፡፡ ሠራተኛና ስራውን ማገናኘት አቅቶናል፡፡ በዚያም ላይ ደግሞ ለሙሰኞች በር ከፍተናል፤ በላያችን ላይ ወይም በህልውናችን ላይ ቆመው ያልሆኑትን ነን ብለው ለሚያስመስሉቱ ለእኩይ ተግባራቸው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ህጋዊ ፈቃድ በመስጠት ተባባሪ ሆነናቸዋል፡፡ አንድን ዲሞክራት ዲሞክራት ሊያሰኙት የሚችሉትን



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

መመዘኛዎች ሳያሟሉ በዲሞክራት ስም ለሚነግዱ አስመሳይ ዲሞክራቶች ወይም የአፍ ሠራተኞች የተግባር ባዶዎች ተታለናል:: በእያንዳንዳችን ጉሮሮ ላይ ቆመው ጭነታችንን ሲያከብዱ፣ ለርሀብና ለእርዛት ሲዳርጉን በይሁንታ እያየናቸው ነው:: የእኩይ ተግባራቸው ሰለባ ሆነናል፤ ይሉናል:: በዚህም ሁለት ተቃራኒ ሀሳቦችን የያዙ ሀረጎች ከላይ በጥሬው ሲታይ እውነትነት የሌለው ከእውነታው ጋር የሚጣረስ ነገር የሚመስለው፤ ነገር ግን ጠለቅ ብለን ስናየው እውነትነት ያለው እንደሆነ የሚያሳይ ይመስላል:: በተለይም ሁለቱ ስንኞች «ከማንም ሰፌድ ላይ ቆሎ እየዘገነ!» ና «ሲበላ ፈቅደናል ዲሞክራት ከሆነ» የበለጠ ሀይል ያላቸው ናቸው:: በተጨማሪም «ባይለዝም»፣ «ባንመዝም»፣ «ባንይዝም» የሚሉ ድምፀቶች ለገለባው አጉይነትና አለማድረግን በተቃራኒው «ፈቅደናል»፣ «ዲሞክራት ከሆነ» የሚሉትን ስናይ «አይ» ና «አዎ» በህብረት የተገለፁበት መሆኑን እንረዳለን:: ፀሀፊዎቹ በዚህ ጽሁፋቸው አስመሳይ ዲሞክራቶችን ወይም ሙሰኞችን መዋጋት አለብን:: ይህን መሳይ እኩይ ተግባር የሚፈፅሙትን ከዚሁ ተግባራቸው ይታቀቡ ዘንድ አይሆንም፤ አይደረግም ልንላቸው ይገባናል የሚል ዓይነት መልዕክት አስተላልፈውበታል::

## 3.5 በስዕል መልክ የቀረቡ

ስዕል በንድፍና ቀለማት አማካይነት የሚገለፅ ጥበብ ነው:: ስዕል የሚያሳይና የሚነግር ጥበብ ነው:: በሚፈጥረው ምስል እንቅስቃሴ፣ ትካዜን፣ ደስታን፣ ሀዘንን... ወዘተ. ሊያሳይ ይችላል:: ይህን የኪነጥበብ ዘርፍ ከሌሎች የሚለየው ድንበር የለሽ መሆኑ ነው:: ይህም ሲባል አንድ ስዕል የአሳሳል ቴክኒኩና ደረጃው እንዲሁም ረቂቅነቱ ይለያይ እንጂ በየትኛውም ባህል ውስጥ ላደገ ወይም ለኖረ ሰው የሚሰጠው ትርጉምና ፍች ይኖረዋል:: ስለሆነም ሁለንተናዊ ስሜቶችን (universal feeling) የመፍጠር ሀይል አለው:: በተለይም ረቂቅ ስዕሎች ከሚኖራቸው ወይም ከሚገልፁት ጥልቅ ሀሳብ የተነሳ አተረጓጎሙ ከሰዎች ሰዎች ሊለያይ ይችላል:: በዚህ ሂደት ውስጥም የታሰበው ትርጉም ተዘሎ ለስዕሉ ያልታሰበና አዲስ ትርጓሜ ሊሰጥ ይችላል:: በመሆኑም የሰው ልጅ እጆቹን ለማፍታታት በጥንት ጊዜ በድንጋይ ላይ ቅርፅ ሠርቶ፣ ከቅጠላ ቅጠል ጭማቂ ቀለማትን ፈጥሮ፣ እንደዘበት ከሚጭራቸው ምስሎች እስከ አሁን ዘመን ረቂቅ ስዕሎቹ ድረስ ያሉት ትሩፋቶቹ የተለያዩ መልዕክቶችን ማስተላለፊያ በመሆን እያገለገሉት ይገኛሉ::

ስለ ስዕል ይህን ካልኩ በመቀጠል የምናየው በስዕላዊ አቀራረብ ዘዴ የቀረቡ የግድግዳ ጽሁፎችን ነው::

<u>ምሳሌ 1:-</u>



«እስኪ መስቀልህ ስር ሸክሜን ልጣለው::»

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ ከስዕል ጋር የቀረበው በቤተመፃህፍት ውስጥ ነው። ከላይና ከታች በምልልስ የቀረቡ የሁለት ጎራ የፖለቲካ ተረብና ብሽሽቆች ስር ተስሎና ከጎኑ ያለው መግለጫ ተፅፎ ተገኝቷል። ከስዕሉ መልዕክት እንደምንረዳው ከዚህ ሁሉ ንትርክና እሰጥ አገባ ኢየሱስ ክርስቶስ ባንተ ላይ ወይም በመስቀሉ ላይ ተስፋዬን ልጣል የሚል ስሜት ተላልፎበታል። እስኪ አንተው ታውቃለህ የሚል ዓይነት መልዕክት አለው።

**<u>ምሳሌ 2</u>፡-**



**2 Pac**

**ቅንጅት**

ይህ የግድግዳ ጽሁፍ ከስዕል ጋር የቀረበው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው። ምስሉ የግማሽ ፊት ቅርፅ የያዘ ነው። ይህን ስዕል በተለያየ መልኩ መግለፅ ይቻላል። በአንድ መልኩ የሚገልፀው ጥቁር አሜሪካዊው የራፕ ሙዚቃ አቀንቃኝ የነበረው 2 pac ስመ ገናና የሆነ፣ ሙዚቃዎቹ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች እስከ አሁን ድረስ በከፍተኛ ደረጃ የመደመጥ ዕድል ያገኙ ታዋቂ አቀንቃኝ ነበር። ይህ አቀንቃኝ ከሞተም በኋላ ተወዳጅነቱ ሳይቀንስ ዘመን ተሻግሮ በአሁኑ ወጣት ልብና አእምሮ ውስጥ ያለ አቀንቃኝ እንደመሆኑ ቅንጅትን ከዚህ ሰው ጋር ማያያዝ ምናልባትም የፈለገው ህያውነቱን ለመግለፅ በአብዛኛው ልቦና ውስጥ መግባቱን ለማሳየት ይመስላል። ከዚህ በተጨማሪም ደግሞ «2 pac» የሚለው ሀረግ ትርጉም ጭነት፣ ጥቅል ወይም እሽግ የሚለውን የእንግሊዝኛ አቻ ለመተካት የገባ ይመስላል። በዚህ አገላለፅ የተጠቀለለ ወይም የታሸገ ነገር ጭነት ደግሞ በቁጥር ብዛት ያለው ነው። መጠቅለሉ፣ መጫኑና መታሸጉ አንድነትን፣ መያያዝን ወይም መተሳሰርን ያመለክታል። አንድነት ደግሞ ሀይል ነው። ስለዚህም ቅንጅት አንድነት ነው፤ሀይል ነው፤ ባጠቃላይ የህዝቦች ውህድ ሀይል የትስስር ውጤት ነው ለማለት የተጠቀመበት ይመስላል።

**<u>ምሳሌ 3</u>፡-**




ይህ የግድግዳ ጽሁፍ ከስዕል ጋር የቀረበ ነው። የተገኘ ውም ከቤተመፃህፍት ውስጥ ነው። ይህም ስዕል ተስሎ የተገኘው የተለያዩ የፖለቲካ ልዩነት ስሜት ከሚንፀባረቅባቸውና በምልልስ ዘዴ ከቀረቡ የግድግዳ ጽሁፎች ስር ነው። ልዩነት ለመፍጠር አትጣጣሩ ለማለት ያስፈረው ይመስላል።

ፀሐፊው አምላኩን በተማፅኖ የህዝቦችን መለያየት አታምጣ፤ አታሳየን፤ ሁላችንንም አንድ ያርገን ፣ፍቅርን ይስጠን የሚል ምኞቱን ለመግለፅ የተጠቀመበት ነው።

**ምሳሌ 4፡-** I get my Business




ይህ የግድግዳ ጽሁፍና ስዕል የተገኘው በመኝታ ቤት ጥበት ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ እንደ ወንዶች መኝታ ቤት ያገለገለ ቀደም ሲል መማሪያ ክፍል የነበረ በር ላይ ነው። የጽሁፉ ይዘት እንደሚያስረዳው ፀሀፊው ጨካኝ የሆነና የሚቀናበት ጓደኛ ያለው ይመስላል። ጓደኛውም በሱ ማግኘት የሚናደድ ወይም ተደሳች ያልሆነ ሆኖ፤ ይህንኑ የጓደኛውን ጭካኔ ከናዚ ተግባር ጋር አወዳድሮ ለማሳየት ሞክሯል። እንደሚታወቀው ሁሉ በጀርመን ናዚዎች በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የተፈፀመው ተወዳዳሪ የሌለው በ6000,000 /ስድስት ሚሊየን/ አይሁዶች ላይ የተደረገው ጨካኝ ጭፍጨፋ በዓለም ላይ ከተከናወኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሁሉ በዋናነትና በከፍተኛነቱ የሚጠቀስ ነው። ይህ ፀሀፊም ጓደኛውን እንደ አንድ ናዚ በመቁጠር እኔስ አግኝቻለሁ፤ አንተን ደስ አይበልህ፤ ወይም ተናደድ የሚል ዓይነት መልዕክት አስተላልፎበታል። በዚህም በአዕምሮው ውስጥ የሚመላለሰውን የጓደኛውን ጭካኔ ተግባር ተንፍሶ የአዕምሮ ረፍት ለማግኘት የፃፈው እንደሆነ መገመት ይቻላል።

በአጠቃላይ ይህና ሌሎች የወሲብ የሰውነት ክፍሎችን ለይተው በመሣል ሀሳባቸውን የገለፁም አሉ። ስዕሎቹ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በተረጎመችው መልክ ብቻ ትርጉማቸው ላይሄድ ይችላል፤ ምክንያቱም ፀሀፊው ያሰበውና ተመልካቹ የሚገነዘበው የተለያየ የሚሆንበት አጋጣሚ ስላለ ነው።

## ማጠቃለያ

የግድግዳ ላይ ጽሁፍን የመመርመር ሂደት የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አቋም፣ አመለካከት፣ አተያይና ሁለንተናዊ የሰው ልጆችን መንፈሳዊና ቁሳዊ ባህል ማጥናት ነው፡፡ በዚህ ጥናቴም በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ በተፃፉ የግድግዳ ጽሁፎች ላይ በማተኮር በይዘቱና በአቀራረብ ዘዴው ተመርኩዤ ትንተና አድርጌአለሁ፡፡

በግድግዳ ጽሁፎቹ ውስጥ የታዩት ስሜቶችና አስተሳሰቦች እንደ ፀሀፊዎቹ መቼት፣ እንደፀሀፊዎች አተያይና እምነት፣ እንዳላቸው ማህበራዊ ደረጃና ቤተሰባዊ አመጣጥ፣ እንደዖታቸው፣ እንደሚፅፉበት ማህበራዊ አውድ፣ እንደሚደግፏቸውና እንደሚቃወሟቸው ርዕሰ ነገሮች /ጉዳዮች/ የተለያየ ገፅታ አላቸው፡፡ በሚፈነጥቋቸው ሀሳቦች በአብዛኛው ተመሳስሎ ቢታይባቸውም ልዩነቶችም ይስተዋሉባቸዋል፡፡ ከሚመሳሰሉባቸው ነጥቦች ውስጥ ጎልተው የሚታዩት አብዛኞቹ ጽሁፎቻቸው ያተኮሩት በወቅታዊ የፖለቲካ ትኩሳት ላይ፣ ወሲብ ነክ ጉዳዩች ላይና ማህበራዊ ጉዳዮችና ችግሮች ላይ መሆኑ ነው፡፡ በፖለቲካና ማህበራዊ ጉዳይ ነክ ጽሁፎቻቸው ውስጥ የሚታዩት ምሬቶች የማህበረሰቡን የኑሮ መሠረት መናጋት፣ ማህበራዊ ችግሮች ከዕለት ዕለት እየተባባሱ መምጣታቸውን የሚገልፁ ስሜቶችና አመለካከቶችን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ የወጣትነት የለውጥ ፈላጊነት ስሜቶች የጎሉባቸው መሆኑ ይታያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጽሁፎቻቸው አስተማሪ፣ አራሚና ምክር አዘል ሆነው ከችግሮቹ የመውጣት ምኞት፣ ህልምና ጉጉት የሚታዩባቸው ናቸው፡፡ የልዩነቶቻቸው ምክንያቶች የየፀሀፊዎቹ የዖታ ግንዛቤ፣ ፍላጎቶቻቸውና የአውዱ ምቹነት ናቸው፡፡ ልዩነቶቻቸው ደግሞ አስተዋይነትና ስሜታዊነት፣ ለሚያምኑባቸው ነገሮች ቀና የመሆን፣ ታማኝነትና ፅኑነት፣ ፌዝ ላይ ማተኮርና ቁምነገር ላይ ማተኮር ናቸው፡፡ በመሆኑም በምልልሳቸውና በጽሁፎቻቸው ታማኝ ድጋፋቸውና ፅኑ ተቃውሞአቸው ታይቷል፡፡ በዚህም የታዘቡትን ሁነት፣ ምኞትና ተስፋቸውን ገልፀዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር ጽሁፎቹ የማህበረሰባችንን ችግሮች የሚተነፍሱ፣ ብሶቱን አውጥተው የሚያጋልጡና የሚሄሱ እንደመሆናቸው መጠን የሙያ ዘርፉ ተመራማሪዎችና የስነጽሁፍ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ የስነሰብ ተመራማሪዎች፣ የህብረተሰብ ሳይንስ አጥኚዎችና ሌሎችም ቢያዩዋቸው፣ ቢጠቀሙባቸውና ቢመረምሯቸው የህብረተሰቡን ችግር ለይተውና ነቅሰው አውጥተው መፍትሔ ለሚሰጡ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ መልዕክት ማስተላለፍ ያስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም መፍትሔ በመሻቱና የማህበረሰቡን ዕድገት ለማፋጠን በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የተሳታፊነት ድርሻ እንዲያበረክቱ ከማስቻሉም በላይ እንደ አንድ አጋዥ መሳሪያ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ባጠቃላይ የግድግዳ ላይ ጽሁፍ በሰፊው መጠናት ያለበትና መበረታታት የሚገባው ማራኪ፣ መሳጭና ሳቢ የሆነ የጥናት ዘርፍ መሆኑ የዚህ ጥናት አድራጊ /አቅራቢ/ እምነት ነው፡፡ በሀገራችንም የግድግዳ ጽሁፎች ጥናት ማዕከል ራሱን ችሎ ተቋቁሞ እንዲህ ዓይነት ጽሁፎችን በቋሚነት እየተከታተለ ለአደሳና ዳግም ግንባታ

ከመበላሸታቸውና ከመጥፋታቸው በፊት በፎቶና በቪዲዮ ቀርፆ በቋንቋ ጥናት ሙዚየም ውስጥ ቢያስቀምጥና ለእይታ ቢያቀርብ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው። በየጊዜውም ዳሰሳ በማድረግ የየዘመኑን የህብረተሰብ አመለካከት ለመረዳትና ለማጤን ብሎም እርምት ለመስጠት ያለው ፋይዳ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ከታሪክነቱ ባሻገርም የህዝቡን የልብ ትርታ፣ ስሜትና ፍላጎት ተከትሎ የሀገር ዕድገት ርዕይን ለማስተካከል የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው እላለሁ። በተጨማሪም የመፃፉንም ሆነ የመቅረሱን ልምድ ማዳበር ለጥበቡ ዕድገትና መዳበር የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል ብዬ አምናለሁ።

# ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

[1]Lavatories and prison cells have a strong physical resemblance . . . the atmosphere is secret, confining, subterranean, and consipiratorial. They affect the human emotions in roughly the same way.

[2]Graffiti- the term comes from both the Greek term "Graphein" meaning "to write and the word 'graffiti' is plural of the Italian word "Graffito" meaning "scratch" and its history can be dated back to prehistoric cave man drawings, it can be seen as a human 'need' for communication "Graffiti represents man's desire to communicate"

[3]The word derieved from the Italian, "graffito" a scratching or scribbling from vulgar Latin "graphire" to write with a stylus," from the Greek "grapheion", to write. (1) As the words origin suggests, the action of writing or scratching letters on to a surface has been around for a very long time.

[4]For graffiti writers to get their work displayed to the public and especially to other 'writers' stated "other writers that's the only thing that matters"

[5]Ours was a world where acknowledgement from one's peers was the singularly ultimate grafitification. Never has there been an urgency to be accepted by the public or any one else.

[6]For older writers, it is a "way d of life, something that is part of their every day thinking and routine.

[7]The motives for graffiti are important issue he argues. "There are four major values in hip-hop Graffiti fame, artistic expression, power and rebellion.

[8]A desire for individual group recognition and rebellion against authority probably account for this phenomenon.

[9]"Popular graffiti" and "Community-based graffiti" differ in their content, authors, and intended audience. However it is important to note that though these types of graffiti differ on these particular domains, the inherent nature of graffiti is preserved in that they both share the same contextual arena-public space.

[10]First is the ever present "popular graffiti"- the everyday stuff. The witty commentary, Read 's "folk epigraphy," Dunde's "latrinalia," the phallic symbols, the Jokes, the "for a good time call X'S," the "eat me's," and "fuck you's," the love proclamations, and the

"so-and-so's were here," This type of graffiti is generally written in the national language so that everyone can understand it and, if they want to, participate in its humor of respond in kind.

[11]The second category is community based graffiti, in essence, is the graffiti that generally is viewed as a nuisance to a common citizen. Personally speaking, graffiti art classified under this heading were always the pictures spray-painted in exaggerated bubble letter and cartoonist style. These graffiti were the ones that I became enchanted by in the opening anecdote. There graffiti were the ones that appeared in vibrant pastels, vivacious characters, and a vicissitude of remote locations. There are many sub categories that fall under the aforementioned heading of community based graffiti. These are "hip-hop" graffiti and "Gang" graffiti. But primarily focus on hip-hop graffiti. "Hip-hop" graffiti was choosen due to its innate ability to both alienate and create a cohesive group that reflects contemporary social trends and issues. . . . Choosen due to the style, method. . . "Hip-hop" graffiti is a product of "hip-hop" culture, to refer to the type of graffiti that is a product of contemporary pop-culture. Hip-hop graffiti is a visual product of hip-hop culture, an off beat youth culture emerging in society, and thus is ingrained in music, clothes, dialect, and messages stemming from roots of the hip hop movement.

[12]This type of graffiti is spraycan art, tag art and aerosol art. Lining subway station walls, billboards, and building sides, "hip-hop graffiti" is what many would deem as the most intriguing and sophisticated style of writing. "hip-hop graffiti" has become a global art form, and through its illegal expressive medium, has come to gain greater attention in the media.

[13]Style is the most important thing: It defines who you are.

[14]When he writes for other writers, he uses wild style, and when we write for the public, he uses straight letters.

[15]Graffiti has provided me a special window into people's lives. This window has allowed me to see the positive in what is usually viewed as negative, to find morality in what is often considered depravity, and to discover a creativity and depth of history that makes me grateful to live in the time and place that I do.

[16]Historians are like deaf people who go on an answering questions that no one has asked them. I have learned that every man lives not through care of himself, but by love.

[17]Paradise is always where love dwells.

[18]Graffifi has provided me a special window into people's lives. This window has allowed me to see the positive in what is usually viewed as negative . . . and to discover creativity and depth of history. . . .

## ዋቢ ጽሑፎች


*ማርክሳዊ ሌኒናዊ መዝገበ ቃላት።* (1978 ዓ.ም.)። አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማ/ቤት።

ማይገነት አፈወርቅ። (1991 ዓ.ም.)። "በግራፊቲ ስለሴቶች ያለ አተያይ"። ዲግጽ። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቀረበ።

ዮሐናን ካሣ። (1996 ዓ.ም.)። *ምርጥና ወርቃማ አባባሎች።* አዲስ አበባ፣ አክሱም ማተሚያ ቤት።

ዮናስ አድማሱና ሌሎች። (1966 ዓ.ም.)። "አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ" (ያልታተመ)። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ፈቃደ አዘዘ። (1991 ዓ.ም.)። *የስነቃል መምሪያ።* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት።

***The Advanced Learner's Dictionary of Current English.*** (3rd Edition). (1974). Oxford: Oxford University press.

***The New Encyclopedia Brittanica.*** Volume VIl. (1976).

Reisner, Robert. (1971). ***Graffitti.*** New York: Cowless Book company, INC.


## የኢንተርኔት መረጃ


- Bradley J. Bartolomeo, B.S. Additional major in Anthropology. Anthpology Honors Theseis, union college, Schenectody.NY, USA, 2001.
- Dennant, Pamela,"urban Expression. . . Urban Assault . . . Urban wild style. . . New York City Graffiti; http://www. Graffiti.org/faq/pamdennant.html.Thames University, London, 1997.
- File://A/Graffiti % 20 is % 20% part % 20 of % 20 us. htm.7/17/2006.
- File://A:/Graffitit /Graffiti and urban space.htm.7/20/2006

# አባሪ

# የተሰበሰቡ የግድግዳ ጽሁፎች በፊደል ተራ

# በአማርኛ የተጻፉ

## «ሀ»

1. ሁሉንም የምታውቅ ጌታ ሁሉን ታውቃለህ
    - ❖ የሚሰማህ መኖሩን እርግጠኛ ሳትሆን አትፀልይ!
2. ሁሌ ጠዋት ስትነሳ እንዲህ ብለህ ፀልይ!
   «ጠላቶቼን እኔ እጠብቃቸዋለሁ ወዳጆቼን ግን አንተ ጠብቃቸው»
3. ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን እሺ!
4. ህይወትን አሸንፈው ለቁምነገር የበቁ እንደታላቅ ሳይንቲስት ይቆጠራሉ!
5. ህይወት ጣፋጭ ናት ብለህ አትዋጣት! መራራ ናት ብለህም
   አትትፋት! /ቀብራራው ዶርም/
6. ሆዳም ሲሸከም የበላ ይመስለዋል፡፡

## «ለ»

7. ለመኖር ብላ ለመብላት ግን አትኑር!
8. ለሚያልፍ ቀን የማያልፍ ቃል አትናገር!
9. ለምን ትኖራለህ? ለመሞት!

❖ አይ ሰቀቀን

10. ለምንድነው ደደብን «ደደብ» የማንለው

❖ የሰው ደደብ ስለሌለው

11. ለምን? የሚለው ቃል ወደ ምርምር ዓለም የሚያደርስ ፈረስ ነው፡፡
12. ለሰገራዎ ጥራት መልካም ምግብ መብላት!
13. ለተቀማጭ መነሳት ይከብዳል!
14. <u>ከ«ዳ» ሸሽት</u>

ለአንተ ለአዛውንቱ የቀለለችው <ዳ>

ለኔ ለወጣቱ እንደመርግ ከብዳ

እንዲህ ብዬ ፃፍኩኝ ስዳዳ ስዳዳ

«አይቶ የነዘረ

ያው አመነዘረ

ብሏልና ቄሱ መጣፉን ሲያስረዳ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሳይቀርልን ዕዳ

❖ ነይ በይ እንባ---------!!                                   ለስብሐት ገ/እግዚሀብሔር

15. ለኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. አንድነት እናሳብ ምክንያቱም ቅንጅት አንድ ነው::

16. ----------------- ሌባ!

«ሐ»

17. ሐሰተኛ ተረግጠህ ትወጣለህ

OK! ደግሞ አትጠራጠር እሺ ይቺ

ጥቃት እንዳትጠፋህ                  /ከሌላ ጽሁፍ ጋር/

«መ»

18. መለስ ብዬ ባየው ኑሮዬን ከጐኔ፣

ታምራት ሆነብኝ ሁሉ ነገር ሳይኔ፣

19. መለያየት ያለ ነው ያለመረሳሳት ግን ወሳኝ ነው::

20. መልካም በዓል ለሁላችን ከቆበዬዎች

21. መልክን ሳይሆን ፀባይን አይቶ ማፍቀር ዘለቄታ አለው::

22. መማር መብት ነው መመረቅ ግዴታ!

23. መስራት የቻለ አሸናፊ ነው::

24. መኖርም ሆነ አለመኖር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው::

25. መድሀኒት ቀማሚ መስሪያ ቤት /ቀብራራው ዶርም/

26. መጥፎ ውሀ ሰው ይዛ ትበራለች::

27. ሙቀት አትፈልግ ቀልጠህ ትሞታለህ እሺ!

28. ሚስቴ ውብት ውሸት ነው ደም ግባት ከንቱ !

29. ማለፍ ባንችልም መውደቅ መብታችን ነው!

30. ማስተዋል የጐደላት ቆንጆ ሴት ውበቷ አሳማ አፍንጫ

ላይ እንደተንጠለጠለ ጌጥ ነው::

31. ማታ ስትገባ ያደናቀፈህ ድንጋይ ጧትም ካደናቀፈህ ድንጋይ

እሱ ሳይሆን አንተ ነህ !

32. ምረጡኝ! አስተማሪ አይመረጥም ያለው ማነው?

33. ምነው ለመቃብር መክፈቻ ቢኖረው፣

ብሶቴን ችግሬን ለአባቴ እንድነግረው::

34. ምናለ ሞት ባይኖር?

❖ መውለድ አይኖርም ነበር

❖ መወለድ ከሌለ ደግሞ እንትን ማድረግ አይኖርም!!

35. መንፈሳዊ ኮሌጅ ወኔቢስ - ምን አባክ ታየኛለህ /ከሰው ምስል ጋር/

«ሠ»

36. ሠልጣጤ እወድሻለሁ

37. ሠራዊት ፍቅሬ ፈረስ ጋላቢ ነው

«ሙላለምስ» ተጋላቢ

«ሰ»

38. ሰካራም ሰው ባይሞትም አይን ያለው የሚቁለጨለጭ ሬሳ ነው!!

39. ሰካራም ሳይቀበር የሰነበተ ሬሣ እንጂ አዲስ ሙት አይደለም!

40. ሰካራምና ባዶ ጠርሙስ አንድ ናቸው::

ሁለቱም ጭንቅላትና ሆድ የላቸውም አትሰከሩ አጥኑ እሺ

41. ሰኔ 23 የማትረሳ የብርድና የtension ዕለት

42. ሰው ሆይ ማህበራዊ ኑሮን መልመድ ሞኝነት አይደለም::

43. ሰው ማለት ሰው የሚሆን ነው ሰው የጠፋለት::

44. ሰው ሽንት ቤት ከተቀመጠ በኋላ ዞር ብሎ ያያል! ለምን ይመስልሀል?

❖ ሰው በወለደው ስለማይጨከን ነዋ!

45. ሰው ሲያቅድ ለምን ይስቃል?

46. «ሰው አረም የበዛበት የመከራ ተክል ነው!»

47. ሰው እኮ . . .

48. ሰውን ለማስደሰት ከፈለክ በቅድሚያ ራስህ ተደሰት!

49. ሰው ከሆንክ + ታማኝ ሁን /ታማኝነት ጨምር/

× ፍቅር ይኑርህ /ፍቅርን አብዛ/

= አመለካከትህን እኩል አድርግ

÷ ያለህን አካፍል

50 ሰው ከሆንክ አፍቅር፣

ወፍ ከሆንክ ዘምር::

51. ሰዎቹ ይገላሉ! ሰዎች ይሞታሉ

52. ሱሪዬን አጥቤው ድንጋይ ላይ ባሰጣው፣

ወዳኝ ነው መሠለኝ ተራምዳው አለፈች::

53. ሳስተምር አጨበጭቡልኝ! ስሜ እምስ! በጄ!

54. ሳታይ አትጠጣ ሳታነብ አትፈርም!

55. ሴት ለማውጣት እፈልጋለሁ! ነገርግን HIV ይይዘኛል::

# አይ ጥፍራሙ

56. ሴት ማለት በውበት ያሸበረቀች የቀትር እባብ ናት!

57. ሴት እኮ . . .

ፈጣሪህም አጥፊህም ነች!

❖ 80% አጥፊ!!

58. ስካር በፈቃደኝነት የሚካሄድ እብደት ነው!

59. /ሶስት/ 3 ነገሮችን ውደድ

❖ እናትህን

❖ ፍቅረኛህን

❖ ሀገርህን

60. /ሶስት/ 3 ነገሮችን ጥላ

❖ ቅናት

❖ ምቀኝነት

❖ ሴብነት

«ሽ»

61. ሽክማችሁ የከበደ ሁሉ ሽክማችሁ ይቀል ዘንድ ወደዚህ ኑ /ከሽንት ቤት ግድግዳ/

62. ሽንት ቤት ሲገባ ሱሪ ይወለቃል!

«ደገለገ» አስራ አንድ መስልኩህ አውቃለሁ!

63. ሽንት ቤት ስትገባ ሱሪህ እንዳይሰረቅ

❖ ይኸው አልመጣማ

«ቀ»

❖ ያዲስ የልቤ ንጉስ

64. ቀመርሽ ለፍቅር ወይስ ለትምህርት

65. ቀኑ መቼ ነው?

66 ቀን አይቶ ከሚጠጋህ ጓደኛ ዘወትር የሚከተልህ ውሻ ይመረጣል!

67 ቅንጅት ለዕድገትና ለሰላም

68 ቅንጅት ለአንድነትና ለሰላም

69 ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ አባታችን ነው ምረጡት!

❖ እሺ አንመርጣለን::

70. ቅንጅት ለአንድ ዘር ለዲሞክራሲ!

71. ቅንጅት

❖ ለጥያቄህ መልስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው!

71 ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ያሸንፋል!

72. ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ያሸንፋል

❖ ብለሽ ብለሽ came to my eye.

73. ቅንጅት ሌባ ነው!

❖ አንተ ነህ ሌባው እሺ!

❖ ተበዱ ለምን ስደባችሁኝ እናንተ ቀማኞች

❖ ቀማኛ ብቻ!

❖ What about EPRDF (FDRE)?

74 ቅንጅት!

ላም አለኝ በሰማይ ሄጄ አመጣታለሁ::

75 ቅንጅትን ማን ይምረጠው! ማን? እኛ!

76 ቅንጅትን ምረጡ!

❖ እንመርጣለን

77 ቅንጅትን ምረጡ!

78 ቅንጅትን ምረጡ! እንመርጣለን!

❖ የወንበዴ ምልክት

❖ አይ ሰው ይህም ያልፋል!

79 ቅንጅት አሸንፏል!

❖ አዎ ግን ምን ዋጋ አለው ያለሙያው ገብቶ

80 ቅንጅት እንደሚያሸንፍ አልጠራጠርም

81 ቅንጅት የወጣቱ ተስፋ ነው!

82 ቅንጅት ያሸንፋል! እንደ አርሴናል ያለ ጦር መሣሪያ

## «በ»

83. በህይወት ትኖር ዘንድ መልካሙን እንጂ ክፉውን አትመኝ::

84 በመኪና አደጋ የተለየችንን ጓደኛዬን የምትመስል አየሁ እዚህ ግቢ. አየሁ ምን ልበላት?

❖ ከሲኦል እንዴት እንደመጣች /እንዳመለጠች/ ጠይቃት?

❖ ሁለተኛው ዙር ላንተ እንዳይደርስ ሽሻት!

85. በራሱ ላይ የዘመተ የራሱ አጥፊ ነው::

86 በሰዎች መካከል ስትኖር መወደድ እንዳለ ሁሉ መጠላትም አለ::

87. በሴት ያበደ ይፀድቃል!

88 በሽንት ቤት ስሜቱን የሚገልፅ ሁሉ ሸባ ማሰብን የተሳነው ጊዜውን በከንቱ የሚያባክን የዘመን ገልቱ ነው::

89 በበግ ጊዜ ፍየል በፍየል ጊዜ በግ አትሁን!

90 በአፏ ማር የያዘች በሆዷ መርዝ መያዟን አትዘንጋ!

91 በእኔ የደረሰ ሁላ ይድረስባችሁ!

❖ እኛ አንተን አይደለንማ

92 «በእውነት መለስን እወደዋለሁ;»

❖ አብረህ ተበዳ

93 በእውቀት የበለጠህን በእውቀት ትደርስበታለህ በቁመት የበለጠህን ግን መቼም አትደርስበትም::

94 በእጅ የያዙት ወርቅ ለችግር ይሸጣል::

95 በዘርህ አትመካ

❖ የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ

**አምላኬ ለዘላለም አይለያየን**

96 በዚች ዓለም የከበደ ነገር ቢኖር ሰው ለመረዳት መሞከር ነው::

97 በዚች ዓለም የከበደ ነገር ቢኖር ሰውን ለማስረዳት መጣር ነው

98 በደካማነትህ ብቻ ሰው ማንነትህን /ንብን/ ለማወቅ . . . /ቂል!!/

99 በድህነትህ አትፈር የሚያሳፍር ነገር ቢኖር የአዕምሮ ድህነት ነው::

100 በጉብዝናህ ወራት እግዚአብሔርን አስብ!

101 በግንቦት ዝንብ እንጂ ንብ አናውቅም

102 በግን ያረባ ጥሩ ሴት ያገባ፣
ሲደሰት ይኖራል ገነት እንደገባ::

103 ባንደኛው ክ/ጊዜ የገባው ማን ነው?
ቲቸር----------

104 ብልጥ ፀጉር ደደብ ጭንቅላት ላይ አይበቅልም::

105 ብር ዛፍ ላይ ቢበቅል ኖሮ ወንድ ልጅ ጦጣ/ዝንጀሮ/ ያፈቅር ነበር::

106 ብር ዛፍ ላይ ቢበቅል ኖሮ ሴት ልጅ ጦጣ/ዝንጀሮ/ ታፈቅር ነበር::

107 ብቸኝነት የሀሳብ ገመድ ነው::

108 ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት እኔ በደንብ አርጌ እቀንሳችኋለሁ HIV!!

109 ብዙ እንቡጦችን ለመቀንጠስ ስታሰብ ብዙ እሾሆዎች ሊወጉህ እንደሚችሉ እወቅ

110 ብዳታም ሰው ቁላው ይጣመማል::

111 በየሽንት ቤቱና በመማሪያ ክፍል ግድግዳ ላይ የምትፅፉ ተማሪዎች ፈተና ደርሷልና ብታጠኑ ይሻላል የኮሌጅ አስተማሪዎች ቀይ ብዕራችውን እንዴ መምዘዝ ከጀመሩ ወደኋላ አይሉም እሺ! የኛ ፈላስፎች

❖ አንተ ፍየል አንተ ምን እያደረግህ ይመስልሀል? የኛ መካሪ ቀበጥ ነህ!

«ተ»

112. ተሜ! ሰው ሳትሆን ሰው አትፍጠር!

113. ተሜ! ቁምነገር ያልተሠራበት ህይወት ከሞት አይሻልምና /አይለይምና/

በርትተህ ትምህርትህን ቸክል!

114. ተሜ! ተኮራረጅ ከሰው የደበቁት የበለጠ ያማል!

115. ተሜ! ተኮራረጅ ጠማማ ልብ ያለው አያስኮርጅም::

116. ተምረህ አለቃህን ቀንስ!

117. ተራዎ አስኪደርስ በፈስዎ ይዝናኑ::

118. ተራዎ እስኪደርሰ On በተደረገው በጓደኛዎ ፈሰ ይዝናኑ::

119. ተሰቀለ ቢሉኝ ካፖርቱ ነው ብዬ፣
ተሰቀለ ቢሉኝ ቦላሌው ነው በዬ፣
ለካስ ፊሹ ኖሯል ያ ደርቲ ሰውዬ::

120. ተሻገረ ቢሉኝ አበባው ነው ብዬ፣
ተሻገረ ቢሉኝ ያ ቡና ነው ብዬ፣
ለካስ ጤፉ ኖሯል ባህል፣ መድሀኒቴ ልምድ ቡቃያዬ፣
ለካ ሚቱ ኖሯል የአፍ ማሟሻዬ::

121. ተበዱ ለምን ሰደባችሁኝ እናንተ ቀማኞች /ከሌላ ጽሁፍ ጋር በምልልስ/

121.ተው አትናደድ የሚገነፍል ድስት ራሱን ነው የሚያቆሽሸው::

122. ታማኝና ጨዋ ጠፋ

123. ታይቶህ ይሆናላ ከኮተቤ ጀርባ፣
ያቺ ትንሽ ገንዘብ እኪስህ ስትገባ:: /ከሌላ ጽሁፍ ጋር በምልልስ/

124. ትልቅ ሁልጊዜም ትልቅ ነው::

125. ትምህርት የዕድገት መሠረት ነው::

126. ትልቅ ፈጣሪ ነው የሰው ትልቅ የለም
ኢህአዲግ ግን ራሱን እንደትልቅ ያረጋል::

127. ትምህርትን የጀመረው ማነው? አስተማሪ

128. ትንሽ ምላጭ በራ ሄደች::

## «ቸ»

129. ችግርማ ያልፋል ሠርቶ በማግኘት፣
በደል ግን አያልፍም ከቆረጠ አንጀት::

## «ነ»

130. ነገርን ሁሉ ውብ አድርጎ ሠራው::

መክበብ 3÷11

## «አ»

131. አላህ አንድ ነው::

132. አላማ የሌላትን ንብ አፍነህ ግደላት::

133. አምላኬ ሆይ ችግርና መከራን አታሳየኝ አልልም
ይህን የምችልበትን ትዕግስትንና ፅናትን ስጠኝ::

134. አራም
ሰውን አራም ብለህ አትሳደብ የአንተ ቂጥ ማያ ነው::

135. አራቱ የ «መ» ህጐች

መ - መታቀብ

መ - መወሰን 1996 Bio II

መ - መጠቀም

136. አርቆ አሳቢ የምንለው ብዙ ስህተት የማይሠራውንና ከስህተቱ
የሚማረውን ነው::

137. አስር ለመኖር ሀያ መጨነቅ አያስፈልግም::

138. አስተውለው የሚራመዱት $M^2$ እና $M^1$ ብቻ ናቸው::

139. አበባ ያለሽታ ውበት ያለቁምነገር ዋጋ የለውም::

140. አባትሽ ይሙቱ ኮሶ ጠጥተው
አሳድረውኛል ካንቺ ለይተው /ከሌላ ምልልስ ጋር የቀረበ/

141. አባይ ማደሪያ የሰው አልቤርጐ ይከራያል::

142. አቤት የዘመኑ ሴቶች እንብዳቸው ልክ ነህ ግን በካልሲ

143. . . . . . . ኤርትራዊ ነው ሌባ ነው
ወርቅ ዘር ከወርቆች የተገኘ የሰው ዘርነው ::

144. አብሮ መኖሩ ካላለልን
እስቲ እንሞክረው ደግሞ ተነጣጥለን::

145. አብዮቱ የሚፈነዳው ፍሬሽ ሲገባ ነው::

146. አብዮታዊ እናት ሀገር ወይም ሞት
❖ ልብ ካለህ ናና ሙትላት!

147. አትነሳም ወይ፣
አትነሳም ወይ፣
የፈሰሰው ደም ያንተ አይደለም ወይ?

148. አቶ-------------------- ፎንቃ አጡዟቸው
ወ/ሮ ገነት ከች አሉላቸው
ወ/ሮ ---------------- ኮምኘሌክሷ ቢንጫጫ
ወደ------------------- ያዘች ሩጫ

149. አንመካም በጥይታችን እግዚሀብሔር ነው የእኛ መመኪያችን::

150. አንመላስም በጠመንጃ እግዚሀብሔር ነውና የእኛ መመኪያ

151. አንቀፅ 39 ጠላታችን ነው::

152. አንተ ነህ ሌባው እሺ! /ከሌላ ምልልስ ጋር የቀረበ/

153. አንተ አራም ቁጭ ብለህ አታራም፡፡
154. አንተ ጉረኛ እንደ ገበያ ፍየል መልቀምቀም ነው የምታውቀው
155. አንድ ማፍቀር ግድ ነው፡፡
ሁለት ማፍቀር ንግድ ነው፡፡
156. አንድ ሰው በፍቅር ቢወድቅ የመሬት ስበት አይደለም፡፡
157. አንድን ሰው ሲጠላህ ብቻ ሳይሆን ሲወድህም ለምን በል?
158. አጣሁ ብለህ አትዘን አገኘሁ ብለህም አትኩራራ ልታጣው ትችላለህና!
❖ ልምከርህ አትዘን ይልቅስ ብትሞት ይሻልሀል ስታገኝ ትነሳለህ!
159. አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል፡፡
160. ኧረ ነይ ግቢ ግቢ ኧረ ነይ ግቢ ግቢ
አለ ዘፋኙ
❖ የት ነው የምትገባውን?
❖ እጄ ውስጥ ነዋ፡፡
161. ኧረ ወንዶች ተጠንቀቁ፣
ኤድስ መጣ ከምስራቁ፡፡
162. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሌባ፣ አጭበርባሪ ፣ አቤት ውሸት ሞት ነው!
163. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግና መስሎቹ ይውደሙ!
164. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ማለት ነፍስ ነው እሱ ባይኖር ማንም በሰላም አይኖርም!
165. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ማለት አባቴ ማለት ነው፡፡
166. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስለሸነፈ በካውንስልነት እግ/ር ይመስገን
❖ ባያሸንፍም እግ/ር ይመስገን ለበጐ ነውና
167. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን ብትመርጥ ዋ!
168. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ.አይገዛንም
169. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ከሞተ «ዓመቱ ነው» ለመበስበስ አምስት ዓመት ያቀተዋል
170. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የምላስ ብስለት ቅንጅት የህሊና!
171. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያለፌደራል ጥርስ የሌለው አንበሳ ነው፡፡
172. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያሸንፋል!
❖ የእኩልነት
❖ የእውነት
❖ የሰላም
አባ ነው
173. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ < ቅንጅት
174. ኢትዮጵያ በልጆቿ ተጋድሎ ለዘላለም ትኖራለች!
175. ኢትዮጵያና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ቢጣሉስ ማን ያሸንፋል?
«ኢትዮጵያ» ግን ምን ላይ ይቆማሉ?

176. ኢትዮጵያን እግዚሀብሔር ይምራታል /ሥላሴ/

177. ኢትዮጵያዊ ነበርኩ በቅንነት ወደ አረማዊ ተቀየርኩ
ደደብ ሁላችሁም አይገባችሁም አይደል?

178. ኢትዮጵያ የሚሏት ጋለሞታ ልጆችዋን አስፈጀች ትግሬ ባል አግብታ

179. ኤርትራና ኢትዮጵያ ቢጣሉ ማን ያሸንፋል?

- ❖ አሀያ ሳሀያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም::

180 . ኤርትራን ትወዳታለህ?
አይ የመንን
ወርቅ ዘር ከወርቆች የተገኘ የሰው ዘር ነው::

181. እመቤታችን አማላጃችን ናት::

- ❖ አቃታለሁ ዘፈን Lang III
- ❖ ትወዳታለህ?
- ❖ አዎ
- ❖ ለምን ?
- ❖ አሌታ ነች::

182. እማምዬ እንጃራ!

183 . እስኪ መስቀልህ ስር ሽክሜን ልጣለው::
/የመስቀል ስዕል ጋር ከሌላ ምልልስ ጋር የተገኘ/

184. እቀድም ብላ ገቢና ገባች አሉ

185. እባክህ ህፃን ይመስል ባገኘሽው ነገር ላይ አትፃፍ! እንደ ሰው አስብ!

186. እባክህ ወገኔ መማር ማለት ሀጢአት ነው::

187. እባካችሁ ምንም ነገር አትፃፉ ከፃፋችሁም ስለፍቅር ብቻ::

188. እባካችሁ ከተጠቀማችሁ በኋላ ውሀ ድፉበት ውሀው የተሠራው ለዚህ ነው::

189. እኔ መሄድ መሄድ መሄድ አይታክተኝ
ምን አግር አምጥቶ ኮተቤ ከተተኝ::

- ❖ ታይቶህ ይሆናላ ከኮተቤ ጀርባ
  ያቺ ትንሽ ገንዘብ እኪስህ ስትገባ

190. እኔ ማነኝ አንተ አንተ ነህ

191. እኔማ በገዛ ገንዘቤ ተሰቃየሁ

- ❖ ተዋ ትግሬ

192. እኔን የሚያናድደኝ ነገር ቢኖር ሁለት ዓመት Prepartory ተምሬ
እንደገና 10+3 መማሬ ነው::

- ❖ እደግፈዋለሁ ብሶትህን በግድግዳ ላይ ተወጣ!

193. እኔን የገረመኝ የኩራቷ ጣጣ፣
ለዥዋዥዌ ጡት አላምጣ ባላንጣ::

**194.** እናውቃለን ግን ብንናገር እናልቃለን!!

**195.** እንትን ተቀብቷል እንዳትነኩት

**196.** እንደ ሰው የሚያስብ አህያ ባይኖርም

እንደ አህያ የሚያስብ ሰው ግን አይጠፋም::

❖ ...... .. .... ነው::  «እውነት ነው»

**197.** እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም::

**198.** I Love HIV B/C . . . you can I think you are carrier

እንደዚህ ብሎ የፃፈውን አድናቂው ነኝ::

**199.** እንዴት እንደምታነበው ከተረዳህ ሰው ሁሉ መጽሀፍ ነው::

**200.** እንግሊዝኛ እንዴት ቢጠና ይገባል  ፈቃደኛ ተባበር ምክርህን/ሽን/

❖ ውይይት + ችከላ (**1**×**2**/day)

**201.** እኛ ሴቶች ለናት ሀገራችን፣

በየወሩ ይፈሳል ደማችን::

**202.** እወድሽ ነበረ እንደ ከረሜላ፣

ታዲያ ምን ያደርጋል ሱቃችን ተዘጋ::

❖ ሱቃችሁ ቢዘጋ እኔ ምን አገባኝ፣

እንገናኛለን አንተ ከጠራኸኝ::

**203.** እዚህ ሀገር እውቀት ሳይሆን ድፍረት ነው የሚያስፈልገው::

204. እዚህ ግድግዳ ላይ የሚፅፍ ደደብ ነው::

205. እየሱስ አዳኝ ነው!

❖ ነገር ግን አንተን አያድንህም እናቱን ክደሀታልና!

206. እየሱስ ጌታ ነው! ከሀሰት አማንያን ያድነን::

❖ የሰይጣን ፈረሶች አባባል

207. እየሱስ ጌታ ነው ፍቅር ያስታግሳል

208. እጅህን ወደ ባህር ስደድ ካገኘህ አሳ አውጣ ከአጣህ እድል የለህም!

209. እግዚአብሔር መልካም ነው በመከራ ቀን መሸሸጊያ ነው! ቅንጅትን ምረጡ!

**210.** እግዚአብሔር ዘምሩ እንጂ ዝፈኑ አላለም::

**211.** እንጠፍጥፋት! እሺ!

## «ከ»

**212.** ከማራትዎ በፊት በፊሶ ይዝናኑ

**213.** ከማንበብዎት በፊት መጽሀፉን ይሳሙ

❖ ያለማወቁን የሚያውቅ አዋቂ ነው::

214. ከማየት ያለፈ ቅብጠት ሞትን በፉጨት እንደመጥራት ይቆጠራል!

❖ ከHIV ጠንቀቅ ነዋ!

215. ከምታማኝ ንገረኝ ከምታኮርፈኝ ምከረኝ

216. ከቅንጅት ጋር እስከ መጨረሻው እንቆማለን::

❖ ጊዜ ይፈጃል እንጂ አህያም የጅብ ናት!

217. ከበሽታ ተላላፊ

ከመንገደኛ ተላካፊ

218. ከተናዳፊዋ ይሰውረን

አሜን!!

219. ከተጠቀማችሁ በኋላ ውሀ መድፋት አትርሱ::

220. ከናንተ ሠፈር ቆዳም ማነው?

❖ አህያ

221.ከእንግዲህ ነገሬን ከአፌ አለቅም

የሰው ዶሮ አለ ከአፍ የሚለቅም

222. ከድውይ መንግስት እግዚአብሔር ይሰውረን!

❖ እጅ ባጕረሰ ተነከሰ

223. ከዶሮ ስጋና ከበሬ ስጋ የቱን ትወዳለህ?

«የበግ»

224. ካልሆንኩ ነህ ቢሉኝ አልደነቅም ነገርግን አለመሆኔን ለማሳመን ጥረት አደርጋለሁ::

225. ካካሀን ስትካካ አስተውለህ ካካ

ሰምና ወርቁን አውጣ!

226 ካፍቃሪና ከተፈቃሪ ማን ይጠቀማል

ከሁለት አንዱ

227. ኮሌጅ መግባት ማለት መፈንዳት------------ ?

## «ወ»

228. ወሬ ጠላን!!

❖ ልጆችዬ እሺ! ልጆችዬ እንጫወት

229. ወ/ሮ ገነት አቶ------------ አስገድደው ደፍረውኛል ሲሉ ለቅንጅት አመለከቱ::

230. ውብት ያለ ፀባይ ስኳር ውስጥ ያለ መርዝ

231. ወንበዴ Interhamoey ያሸንፋል

ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ይበዳ!

232. ወንድን ወንድ የሚያደርገው ትልቅነት ነው!

233. ወንድን ወንድ የሚያደርገው ቁላው ነው

❖ አስተሳሰብ አትሳሳቺ!

234. «ወንድን ያመነ ጉም የዘገነ»

235. ወያኔ የመሀይም ጥርቅም ነው!

236. ወያኔ ባልተፈጠርኩኝ ኖሮ

237. ወይ እምስ ሱሪ ቀዶ ሊወጣ ነው::

238. ውይይት + ችኩላ (1×2/day) (ከሌላ ተያያዥ ጽሁፍ ጋር)

239. ውይ እኛ ሴቶች ስንባል የዋሆች ነን::

«በምን» /ምን በመስጠት/

240. ወገን እንነሳ

241. ወጣት አለቀ በሀገሩ መኖር ተከለከለ::

242. ወገኔ ከAIDS ራስህን ጠብቅ በለሷን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላልና!

## «ዐ»

243. ዓለም እያንዳንዱ ሰው ገፀ ባህሪ ተላብሶ የሚጫወትበት አስቂኝ መድረክ ናት::

## «ዘ»

244..ዘመኑ የቸቸብ ነው ከቸቸብ በስተጀርባ ርሀብ

አድፍጧል ካፌ መግባት ተከልክሏል፤ስለዚህ ማመፅ ነው::

245. ዘወትር ራስህን ሆነህ ተገኝ::

246.ዝምታው ይሰበር ለታሰሩት እንጩህላቸው::

## «የ»

247. የሀይማኖት መሪዎች ለኢትዮጵያ ምንም አልሠሩም!

❖ የወያኔ አቃጣሪዎች

248. የህይወት መስመር የሚጀምረው ከት/ቤት ነው::

249 የልጅቷ ሽንት ስለያዘኝ ሽንት ቤት ገባሁ ካላመናችሁ ሂዱና አሬን እዩት!

250 የሚስማህ መኖሩን እርግጠኛ ሳትሆን አትፀልይ!

251 የሚሰራ ጭንቅላት እያለን አነጣጥሮ ማራት እንዴት አቃተን::

252 የሚከራይም የሚሸጥም ወንድና ሴት የለም!

253. የማንነት ጥያቄ በሌላ ስጠየቅ ምን ልስራ ምን ልፍጠር?

254. የምታውቀው ነገር ቢኖርህ አለማወቅ ሊሆን ይችላል::

255. የረገበ ጡት እንወጥራለን!

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

256. የራስህን እንጀራ ለመጋገር ስትሯሯጥ የሰው ቂጣ እንዳትረግጥ ተጠንቀቅ!

257. የሰውን ልጅ ስለምን ታሰቃዩታላችሁ!

❖ There is no great crime than killing.

258. የሰው ፀባይ የአየር ፀባይ
አሁን ዝናብ አሁን ፀሀይ

259. የሴክስ ተጠቃሚው ማነው

❖ ሁለቱም ከላይም ከታችም ያለው ሰው
«በይበልጥ ከታች የሚሆነው»

260. የበረከት ስምኦን ተጠባባቂ አንዱ ነኝ::

❖ እኮ ለምን ይዋሻል!

261. የበታችነት ከተሰማህ ዛፍ ላይ ውጣ!

262. የተመኘሽውን ካጣህ ያገኘሽውን ሁሉ ብዳ!

263. የተማረ ሰው ምንጊዜም ዕውቀቱ ከራሱ ጋር ነው

264. የነቶሎ ቶሎ ቤት ግርግዳው ወርቅ ነው!

265. የአቶዎች ዘመን ይብቃ በዶክተሮች እንመራ!

266. የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ደጋፊ የሆናችሁ ወዮላችሁ!
ዛሬ የተደሰታችሁ አንድ ቀን ታዝናላችሁ በተለይ ............

❖ ሐሰተኛ ተረግጠህ ትወጣለህ! OK! ደግሞ
አትጠራጠር ይቺ ጥቃት እንደተጠፋህ!

267. የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ካድሬዎች ይለይላችሁ!

268. የነ መለስ ድመት በጣም ሰልጥናለች
እንግዳ ሲመጣ አይጥ ታቀርባለች

269. የካቲት 16 በደም ላይ ቀልድ ይቆምና በነፃነት መኖር ይጀመራል!

270. የካቲት 16 ደረሰ ሁላችንም ለነፃነት እንታገል!

271. የካቲት 16 ደረሰ ምን ይሻላል ወይ ሞት ወይ መኖር

❖ ይህ የሰራፊቶች አባባል ነው::

272. የካድሬዎች ኑሮ ይለያል ዘንድሮ!

273. የዘንድሮ ምርቃት ሰልስት ነው::

274. የዘንድሮ ፍቅር በጣም የተንዛዛ?
ትልቁም ትንሹም መልከስከስ አበዛ::

275. የዘፈን ዳርዳሩ በራኘ ይታጀባል!

276. የዚህ ት/ቤት ተማሪ ሁሉ ብርዳም ቢጤ ናቸው!

277. የደደብ ሰው ጭንቅላት መብሰሉ ላይቀር ማገዶ ይፈጃል::

278. የገነት ልጆች ዶርም!

Dormants Dorm – GAPLESS Dorm

279. የገነት ዘውዴ የውበት ሳሎን ይበዛበታል! /ከሽንት ቤት/

280. የጥበብ መጀመሪያ ቀይ ጥለት ነው!

281. የጥበብ መጀመሪያ እግዚሀብሔርን መፍራት ነው!

❖ እምነት የመልካም ስራ መገለጫ ነው::

282. የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ይኖራል!

❖ ግን መጀመሪያስ ማን ይሠራላቸዋል?

283. የፍቅር መድሀኒቱ የአልጋ ላይ ብድ ብቻ ነው!

284. የፍቅር ዓይነቶች የበግ ፍቅር፣ የፍየል ፍቅር፣ የላም ፍቅር፣ የኮርማ ፍቅር

❖ እና የትኛው ነው ያንተ?

285. ያልታደለ ቆዳ የመምህር ጫማ ይሆናል

286. ያልጠፉነወ ከምህረቱ የተነሳ ነው::

287. ያንን አትይ!

ለምን እንጻልህ?

288. ያገለገሉ ሴቶችን በጨረታ እንሸጣለን::

289. ይለያል ዘንድሮ የወያኔ ኑሮ!

290. ይህ ቦታ የሚፈቀድለት ለሚቅም ሰው ብቻ ነው!

291. ይቺም ቂጥ ሆና ሽንት አማራት

292. ይቺም እንጀራ ሆና ሚጥሚጣ . . .

«ደ»

293. ደሀ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ ደርቆ ይቀር ነበር::

294. ደደብ የእግር ያህል ጥቅም የሌለውን ጭንቅላትህን አሠራው! /ከሌላ ጽሀፍ ጋር በመልስነት የተፃፈ/

295. ደከመኝ ተኛሁ!

296. ዲሞክራሲ የካቲት 16 ይጀመራል!

297. ድል ለማንችስተር!

298. ድል ለአርሴናል!

299. ድሮ ልጆች ሳለን ከንፈር ሳያውቅ ከንፈር፣

ቢደራርቅ እንኳን በውሀ ይርስ ነበር::

ዛሬ ከንፈር ለምዶ ከንፈር እንደዋዛ፣

እንኳንስ በውሀ በቅባት አይወዛ::

300. ድብቅነት የአመለካከት ችግር ነው /ከሌላ ጽሁፍ ጋር/

301. ድንግልን ተስፋ አድርግ በርታ ልብህም ይፅና

302. «ድንግልን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም!»

ለምን? አሌታ ነች

## «ጀ»

303. ጀግናው የቅንጅት ደጋፊ ጦር ሜዳ ሄዶ ይዋጋል!

304. ጆሮ ቢያድግ ከጭንቅላት አይበልጥም!

## «ገ»

305. ግልፅነት እራሱ የቆረጠውን መልሶ የሚሰይፍ ነው!

306. ግልፅነት የጀግንነት ምንጭ ነው፡፡

307. ግሬድ መለጠፉን ትላንትና ስምታ፣

ስታሰብ አደረች መባረሯን ፈርታ፡፡

308. ግንቦት 29/1997 ቀውጢ ቀን

309. ጉሽ ለልጇ ስትል ቦርሳ ገዛች፡፡

310. ጉበዝ ! የማያነብ ሰው በፈተና ወቅት የሚመልሰው ያጣል፡፡

311. ጓደኛህ ማር ቢሆን ጨርሰህ አትላሰው

312. ግድግዳዎች የሀሳብ መስጫ ሳጥን አይደሉምና ግድግዳ ላይ አትፃፍ!

313. ጓደኛዬ በተሳካለት ቁጥር በውስጤ አንድ ነገር ይሞታል፡፡

## «ጠ»

314. ጣውላው ተሰበረ ሳይረገጥ ጉኑ፣

አይዞሽ የናቴ ልጅ ያልፋልና ቀኑ፣

ችግርን መቋቋም እንልመድ ካሁኑ፡፡

315. ጥቅምት «22» ና «23» የጀግኖች ቀን!!

## «ጨ»

316. ጨቋኝ አምባገነን መንግስት ነው ያለን በናታችሁ

ቅንጅትን ምረጡ እሺ እንመርጣለን!

## «ፊ»

317. ፊረስ ለልጇ ስትል ኮርቻ ገዛች፡፡

ለምን? ልታዝላት!

318. ፊሳምን በፊሳምነቱ ማበረታታት!

319. ፈገግታ የንዴት ማብረጃ የውበት መግለጫ ናት፡፡

320. ፍሬሽ ጦጣው ዛሬም እማራለሁ ብለህ እያስብክ ግባ::

321. ፍቅርን መቼም ቢሆን ሚስጥር ማድረግ አይቻልም::

322. ፍቅር ነው ብላችሁ ሰዎች አትዝለሉ፣
ወይ ያልፍላትና ትዝብት ነው ትርፉ::

323. ፍቅር ነፍጉኛል
❖ ፍርድ ቤት ክሰሺው

324. ፍቅር አማረኝ!
ያም ሲፈታ OK!

325. ፍቅርን ከፈለክ ኮተቤ፣
ማበድ ከፈለክ 4 ኪሎ::

326. ፍቅር ውሀ የማያጠፋው እሳት ነው!

327. ፍየልን ያረባ መጥፎ ሴት ያገባ
ሲቃጠል ይኖራል እሳት እንደገባ

328. ፍቅር ይዞኛል!
❖ ሁሉም ያልፋል ጨክነህ ስራ

329. ፍፁም ሰላምና ደስታ የሚገኘው በእየሱስ ነው::

«T»

330. ኘረዘንቴሽን ሰለቸኝ!
አይአንተ የት ልትደርስ?
አለዚያ በ "D" ተንደርድረሽ ባንዲራሽን
ሰቅለሽ ሀገርሽ መግባት ነው::

## በእንግሊዝኛ የተፃፉ

## "A"

1. Arsenal is the best team
2. Avoid sex without condom.

## "C"

3. Colourfull dream of the year.
4. CUD is Love!
5. CUD
   - Life
   - Love

- Peace
- Democrat
- Union.

## "D"

6. Die for Truth! Not for not truth!
7. Donkey greater than man
8. Don't do sex without condom.
   - ባጭሩ አይቀንዝርብህ

## "E"

9. E.P.R.D.F dictatorial Gov't
10. E.P.R.D.F
    - Parasite
    - Disease
    - HIV/AIDS
    - Killer
    - Undemocrat
    - Dectator
    - Rude
11. Every body do the best
    Oh! God will do the best.

## "F"

12. Feb 16, The down fall of E.P.R.D.F.
13. Fuck of K.C.T.E. girls
    - Certifi Class.

## "G"

14. GAPLESS DORM
15. "God is proposal"
    Man is disposal

## "I"

16. "I Love HIV b/c . . ."

You can I think you are carrier.

**"J"**

17. Jesus is Lord.
18. Jesus is LORD SAVER

**"K"**

19. K.C.T.E. means knowledge, garden doesn't it? Yes, it does.
20. Keep smileing . . .

**"L"**

21. L – Lake of Sorrow.

    O – Ocean of tears.

    V – Valley of death.

    E – End of life. (Maths II B)
22. Learning is Burnning
23. Let's mind for others.
24. Life is difficult without Islam.
25. Long Live Henry
26. Long Live all Ethhiopian People Except the leader of EPRDF.

**"M"**

27. Manchester is the best team.
28. M – Migrant

    L – Lowly

    S – Sinful

**"N"**

29. No, peace without CUD.
30. Nothing is impossible for Gay.
31. No, true love in K.C.T.E SO. . .

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

**"O"**

32. One love is nature but two Love is future.

33. ONALOO

LIWA

CARIO

DOLIMA

34. One day I will be ama.

❖ That day is not far.

## "P"

35. People killing people dieing.
36. Please make sure that the penis
    Is yours before you go to the toilet.
37. Please make sure that the penis
    is your special than other thing.

## "S"

38. See three, choose two,Love one.

## "T"

39. The came

    N.W.A

    The Black Wall Street.
40. There is no great crime than killing
41. Think as a man.
42. Think before Ask!
43. "Trust Allah Believe"
44. The battle of freedom.

## "W"

45. We are victorious through God /Allah/
46. We Ethiopians are under the gun of E.P.R.D.F.
47. "Wedding came cut BerBerie."
48. What about E.P.R.D.F. /ከሌላ ጸሁፍ ጋር/
49. Who else would B.C
50. "Whom much is given much expected

## “Y”

51. You don’t have to be E.P.R.D.F.

## በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቅልቅል የተፃፉ

1. CUD ለዘላለም ይኑር!
2. CUD ቆማጣ!
   ቆማጣ ከየት መጣ!
   ❖ አቢሲኒያ!
   ❖ ወዬልሽ አንቺ በቀቀን!
3. H.P.E ተማሪዎችን አምላክ ሆይ የሚሠሩትን
   አያውቁምና ይቅር በላቸው
4. I get My Business




5. I Love you ትዝብት → CUD is Love
6. Long Live CUD (የሰው ምስል ከጐኑ ተስሎ)
   ❖ ምናባክ ታየኛለህ?
7. የK.C.T.E. ፍቅር እጅጉን ተንዛዛ፣
   ተማሪው በሙሉ በግ ተራ አበዛ::
8. ONDR / CUD / ABO } ለዘላለም ይኑር
9. ሰላማዊ ቦንብ እስኪታይ
   ❖ Don’t forget your study.
10. I.C. Maths ተማሪዎች አትቸኩሉ ተባብረንእንመረቅ!
11. Love is አደገኛ Some times ጉረኛ
12. This group all fuck Except One Gay
    ❖ ካድሬዎች
13. 2 Pac ቅንጅት
14. Victory for ቅንጅት ሁለት ጣት /ምልክት/

አክርማው ባይለዝም
ሰበዝ ባንጠዝም
ወሰሌንም ባንደዝም
በማንም ሠሌዳ ላይ ቆሎ ቈየዘገገ
ሊበገ ፊ ቅዳናብ ደ ምክሬች ከሆነ

ሺ ኖ ዋ ዩ ዓ
በሰዩዜ ተጋዩሎ
ለዘላለም ትኖሬለኅ

በሠ ተገሠ ምድርንም ዉጦኛ

ዳህ ነ ሊያርጎ እቶንሣኙሢኩሠ

ጼዐ ኀ—

ሕ፦ ኦወ ፳

የ ዋጓ ሌ ኂ

የገቲኀ 16

ፋቨ ወር ሌ ሏ

[illegible]

[illegible]



ኢሁኸዩሴዐ
ኤዌገዟኋዋ

[illegible] ዝንጀሮ

[illegible] ጉሮ!!


SH

ኋ ገኝ ካ ከ ም ው ሟ

ካ ኟ ኳ ከ ም ው ሟ

ዩ ቤ ሉ ከ ው ጹ ሟ

ዩ ገኝ ተ ሟ ጸ ሐ ም

ው ሟ ፡፡

저에게 오빠가

[illegible]

[illegible]


Fueck of KCT


Feb 16 The downfall of EPRDF
Who else would

የገሬት

16

በየምለዩ

ቀለዩ—

ዋቆምና

በገቁገ

መዮር

ተዷመ፡ሁለ



L - lake of Sorrow
O - ocean of tears
V - valy of ~~dark~~ death
E - End of life

Matth II B

ወመንፈ ከለቆ
በሀኀሣ መሠረት ተኪ

"ከተቀዐባኙ፡ ዐሀሩላት፡ ይጠጡሿ"

ሂ ኍ ውዉ ዯ ፀ

በወለጀ ቷ ተጋደሎ

ለዘለከም ቶ ዩ ሁለ



ቡሥ ተገዛ ጥድርጎም ጋዐኘ

ዷ ሀና ኢዷርጌ እቀንሣኘሃከሀ

ጱሮ ኘኊ

ሕፔ ኢወ ፫

የምንገሁኪ

የገቲና 16

ቁጸወርለ

[illegible]

[illegible]



지난겨울에
저희가캠핑





« እንኔሰ ግሙ ወያ
ኣንናሰ ግሞ ወይ
የቤሳሰ ው ጸግ
የእንት ጎዩ ጸሐሞ
ወያ »

저에게 오셔서
주신
[illegible] 에서 [illegible]


Fucck of KCT
Sills
Ceri
Clast
Bich


are
Through
Feb 16 The downfall
of EPRDF
Who else
would

ዓገቷን

16

በዓም ነዓ

ቀበዓ

ዓቆ905

በንዓኘን

መዓሪ

ፋሺመሁብ



L - Lake of Sorrow
O - Ocean of tears
V - Valley of dark death
E - End of life.

Math II B

THIS GROUP
All FUCK
EXCEPT
ONE GUY.

[illegible]

Victory
for

YOU don't have
to be EPRIDE


EPRDF
HIV/AIDS
Killer

[illegible] Past Homes
And Masters From
Come Life [illegible]

JESUS IS - LORD
· SAVER.

ከዷ፡ አሽን

ለእንተ ለአዛወንቱ የቀለለቸው'ዳ
ለሌለወጣቱ እንዴወርግ ከበዳ
እንዴህ ከዩ ፀፅከኝ ለዳዳ ለዳዩ
"ኸደዩ የናዘ_
ዩው ኸመገዘሊ"
ከ፯ወና ቄሉ መጣቱን ሊያገለቱ
ገደቀረወን ዐዳ
ኗዩ ብዩ እንጂ___

[illegible] [illegible]!!